CECOE

Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Election

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

# የምርጫ ትዝብት ሪፖርት

## የኢትዮጵያ ስድስተኛው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ





www.cecoe.org

ግንቦት 2014

ይህ ሪፖርት ሊሳካ የቻለው እና የታተመው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (USAID) ከአሜሪካ ሕዝብ በተበረከተ ቸር እገዛ ሲሆን ይዘቱ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ሕብረት ለምርጫ (ሕብረት ለምርጫ) ኃላፊነት እንጂ የUSAID፣ የአሜሪካ መንግስት ወይም ሌሎች አጋር ድርጅቶችን አቋም ወይም ምልከታ የሚያንፀባርቅ አይደለም።

# ማውጫ


ምስጋና ........................................ 1

የምህጻረ ቃላት ዝርዝር ........................................ 2

የምርጫ ትዝብት ግኝቶች ማጠቃለያና ምክረ ሐሳቦች ........................................ 4

- መግቢያ ........................................ 5
- አበይት የትዝብት ግኝቶች ........................................ 5
  - የመራጮች ምዝገባና የቅድመ ምርጫ ሁኔታ ........................................ 5
  - የድምፅ መስጫ ዕለት ግኝቶች ........................................ 6
  - ድኅረ ምርጫ ........................................ 7
- ዋና ዋና ምክረ ሐሳቦች ........................................ 8
  - ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ........................................ 8
  - ለባለድርሻ አካላት የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች ........................................ 9

ምዕራፍ ፩፦ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ ........................................ 10

- ድኅረ 2010 ዓ.ም ፖለቲካዊ ምህዳር ........................................ 10
- ቀደምት ምርጫዎች ........................................ 10
- የግንቦት 2012ቱ አጠቃላይ ምርጫ መተላለፍ ........................................ 11
- ስድስተኛው ብሐራዊና ክልላዊ ምርጫ እና የደህንነት ችግሮች ........................................ 11
- በኢትዮጵያ ምርጫዎች ላይ የሲቪል ማኅበረሰብ ተሳትፎ ........................................ 12

ምዕራፍ ፪፦ ስድስተኛው የኢትዮጵያ አገር አቀፍ ምርጫ፦ የምርጫ ደንቦች ጠቅላላ ምልከታ ........................................ 14

- የ1987ቱ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ........................................ 14
- አዋጅ ቁጥር 1133/2011 ........................................ 14
- አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ........................................ 15
- ሌሎች የምርጫ ሕጎች ........................................ 15
  - የተሻሻለው የሲቪክል ማህበራት ድርጅቶች አዋጅ ........................................ 15
  - ከስድስተኛው ምርጫ የምርጫ ደንቦች ጋር በተያያዘ የሕብረት ለምርጫ ........................................ 16
  - (CECOE) ምልከታዎች ........................................ 16

ምዕራፍ ፫፦ የምርጫ ቅሬታዎች አሰማም  እና የአለመግባባት አፈታት ሥርዓት ........................................ 18

- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቅሬታ አሰማም ሥነ ሥርዓቶች ........................................ 18
- በመራጮች ምዝገባ ወቅት የቀረቡ ቅሬታዎች ........................................ 18
- በምርጫ ቀን የቀረቡ ቅሬታዎች ........................................ 19
- ለፌዴራልና ለክልል ፍርድ ቤቶች የቀረቡ የምርጫ ቅሬታዎች ........................................ 19
  - ሀ) የሐሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ........................................ 19
  - ለ) ባልደራስ  ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ እና እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ........................................ 20

ምዕራፍ ፬፦ የምርጫ ትዝብት ዘዴ እና ውሱንነት ........................................ 22

- የድምጽ መስጫ ምርጫ ቀን ትዝብት ዘዴ (Methodology) ........................................ 22
  - ቋሚ ታዛቢዎችን ተመጣጣኝ በሆነ ስምሪት በማሰማራት የሚካሄድ ትዝብት (Proportional Stationary .. 22
  - Observation) ........................................ 22

አመቺነትን መሰረት ባደረገ የቋሚ ታዛቢዎች ስምሪት የሚደረግ ትዝብት (Convenient observation)........22
ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት የሚደረግ ትዝብት (Mobile observation)........23
የሕብረቱ የምርጫ ትዝብት ዘዴዎች ውሱንነት ........24
የቅድመ- ምርጫ ትዝብት ........24
የድምጽ መስጫ ቀን ምልከታ (ትዝብት) ........24
ድኅረ- ምርጫ ምልክታ........25

ምዕራፍ ፫፡ የሕብረቱ የምርጫ ትዝብት ግኝቶች ........27
የቅድመ ምርጫ ትዝብት ........27
መግቢያ ........27
የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ........27
የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የዕጩ ተፎካካሪዎች ምዝገባ........28
የመራጮች ምዝገባ ........29
የቅድመ ምርጫ ድባብ ........33
የድምፅ መስጫ ቀን ትዝብት ........38
መግቢያ ........38
ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች የደረሱበት ሰዓት ........38
የድምፅ አሰጣጥ ሂደት........43
የድምፅ ቆጠራው ሂደት........45
ሌሎች የትዝብት ግኝቶች ........46
የድኅረ - ምርጫ ትዝብት ........47
መግቢያ ........47
የምርጫ ውጤት አገላለጽ እና የኅብረተሰቡ ምላሽ........48
የድኅረ ምርጫ ድባብ ........48
በምርጫው ውጤት ላይ የህብረተሰቡ ግምት........49
የሲቪክ ምህዳር ........49
በድኅረ ምርጫ የቀረቡ ቅሬታዎች ........49

መደምደሚያና ምክረ- ሐሳቦች ........52
መደምደሚያ........52
ምክረ- ሐሳቦች ........52
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ (ኢብምቦ)........52
ለተወካዮች ምክር ቤትና የመንግሥት ሚኒስቴሮች ........56
የሲቪል ማኅበረሰብ ተዋንያን ........56
መገናኛ ብዙኀን........57
የፖለቲካ ተዋናዮች፡ ........57

ሕብረት ለምርጫን የተመለከተ መረጃ........59
የሕብረት ለምርጫ ተሞክሮዎች እና ልዩ ልዩ ተግባራት ........59
የሲዳማ የክልልነት ሕዝበ- ውሳኔ........59
የህብረቱ አባል ድርጅቶችን አዐቅም መገንባት ........59
በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የቀረቡ ዌቢናሮች (የበይነመረብ ቪዲዮ ውይይቶች) ........60
የመገናኛ ብዙኀን ዳሰሳ ክትትል ........60
የመራጮች ትምህርት ........60

# ምስጋና

በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ / CECOE) ተግባራዊ የተደረገው የምርጫ መታዘብ ፕሮጀክት ከፍተኛ ሥራና ቁርጠኝነትን ይጠይቅ የነበረ በመሆኑም ለትግበራው ኀብረት ለምርጫ የተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶችን ድጋፍ ባያገኝ ኖሮ መሳካቱ በጣም አስቸጋሪ ነበር። ስለሆነም ለሁሉም እነዚህ አካላት ጥልቅ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን።

ኀብረት ለምርጫ በመጀመሪያ ደረጃ በምርጫ ሂደቱ ላይ በመሳተፍ ለዲሞክራሲያዊ እሴቶች ጠንካራ ቁርጠኝነቱን ያሳየውን የኢትዮጵያ ሕዝብን ያመሰግናል። ቀጥሎም ለፕሮግራሙ ስኬታማ መሆን ውድ ጊዜያቸውን በመስጠት ላሳዩት ትጋት እና ላበረከቷቸው አስተዋፅዖዎች የኀብረት ለምርጫ ቦርድን፣ አባል ድርጅቶችን፣ ሠራተኞችን፣ ታዛቢዎችን፣ የህብረቱ የክልል ተወካዮችን (RFPS)፣ የዞን አስተባባሪዎችን እና በጎ ፍቃደኞችን ከልብ ያመሰግናል።

ከሁሉም በላይ ለዩናይትድ ስቴትስ የዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት (ዩኤስ-ኤአይዲ / USAID)፣ የአውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል (ECES)፣ የዴንማርክ ኤምባሲ፣ የፈረንሳይ ኤምባሲ እና ለአየርላንድ ኤምባሲ ለኀብረት ለምርጫ የምርጫ መታዘብ እና የቁጥጥር ፕሮጀክት ላበረከቱት የገንዘብ ድጋፍ እናመሰግናቸዋለን። ከዚህ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የሪፐብሊክ ተቋምን (IRI) የመራጭ ትምህርት ለመስጠት ላዘጋጀናቸው የተለያዩ የሚዲያ ቅስቀሳ መድረኮች ላደረገልን ድጋፍ ምስጋናችንን እንገልጻን።

ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም (NDI) ላደረገልን የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ፤ በተለይም የNDI ባልደረቦች ለፕሮጀክቱ ትግበራ ስለሰጡን አስፈላጊ የስራ ድጋፍ ሁሉ እናመሰግናለን። የላቀ የዕውቀት፣ የክህሎት እና የተሞክሮ አስተዋጽኦ እንዲሁም ያልተቆጠበ ድጋፍ ባይደረግልን ኖሮ ፕሮጀክቱን ለማሳካት እንቸገር ነበር።

በመጨረሻም ለክርስትያን የበጎ አድራጎት ማህበራትጥምረትና ልማት ማኅበር (CCRDA) እና ECES ስለ ሕብረት ለምርጫ የገንዘብና ሌሎች ድጋፎቻቸው ልባዊ ምስጋናችንን ማቅረብ እንወዳለን።

# የምህጻረ ቃላት ዝርዝር

| | |
|---|---|
| ADP - | የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አዴፓ) |
| ANDP - | የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ANDP) |
| BGPDUF - | የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲዊ አንድነት ግንባር |
| CDHRA - | የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ኅብረት ጉባዔ |
| CECOE - | የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ሕብረት ለምርጫ) |
| CETU- | የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) |
| CSOs - | የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች |
| CVEA - | የሥነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት ማኅበር |
| EHRCO - | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) |
| EPRDF - | የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) |
| ESPDP - | የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢሶሕዴፓ) |
| EWLA - | የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (ኢውላ) |
| EZEMA - | የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) |
| FDRE - | የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) |
| FEAPD - | የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራትፌደሬሽን |
| GHC - | የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ |
| GPDM - | የጋምቤላ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋሕዴን) |
| HNL - | የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ (ሀብሊን) |
| LTOs - | የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች |
| NAMA - | የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) |
| NEBE - | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ |
| ODF - | የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር |
| ODP - | የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዴፓ) |
| OFC - | የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) |
| OLF - | የኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር (ኦነግ) |
| ONLF - | የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) |
| PP - | ብልጽግና ፓርቲ |
| RFPs - | የኅብረቱ የክልል ተወካዮች |
| SEPDM - | የደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ዴሕዴን) |
| TPLF - | የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር (ሕውሓት/ትሕነግ) |




“ ወርቂቱ ሞላ፣ የCECOE የምርጫ ቀን ታዛቢ ከመካነ ሰላም፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ አማራ ክልል፣ ከሁለት አመት ልጇ ቅድስት ውባለም ጋር።

# የምርጫ ትዝብት ግኝቶች ማጠቃለያና ምክረ ሐሳቦች

### የሰኔ ምርጫ




### የመስከረም ምርጫ






# መግቢያ

በ2013 ዓ.ም የተካሄደው የኢትዮጵያ ስድስተኛው አገር አቀፍ እና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በአገሪቱ ከ2010 ዓ.ም አንስቶ የሚታዩትን ዲሞክራሲያዊ ጅማሮዎች ለማስቀጠል ወሳኝ መሰረትን ጥሏል። በአዲስ መልክ የተቀረፀው የምርጫ ህግና የቁጥጥር ማዕቀፍ ምርጫው ይበልጥ ንቁ የፖለቲካ ፉክክር እንዲታይበት፣ የዳኝነት አካሉ በምርጫ ሂደቱ ወሳኝ ሚናን እንዲጫወት እና ፣ ለሲቪል ማህበረሰቡ ተሳትፎ ሰፋ ያለ ምህዳር እንዲኖር አስችሏል። በተጨማሪም በ2013 ዓ.ም የተከናወነው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ የሲቪል ማኅበራት በምርጫ ታዛቢነት እንዲሳተፉ በማስቻል በምርጫ ሂደቱ ላይ ትርጉም ያላቸው ግምገማዎችን እንዲያደርጉ ያስቻለ ምርጫ ሆኖ አልፏል። ከእነዚህ ለውጦች ጋር በተያያዘ ምርጫው የኢትዮጵያ ዜጎችን ጨምሮ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በሲቪል ማኅበራት እና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ዘንድ ካለፉት ምርጫዎች ይልቅ የበለጠ አካታች፣ ተጠያቂነትና ግልጽነት የሰፈነበት ይሆናል ተብሎ እንዲጠበቅ አድርጎታል። ምንም እንኳን በቅድመ ምርጫ፣ የድምፅ መስጫ ቀንና በድኅረ ምርጫ ሂደቶች ወቅት በግልጽ ጉድለቶች ቢስተዋሉም፤ በምርጫው ሂደት ህብረቱ የታዘባቸው ትርጉም ያላቸው መሻሻሎች አገሪቱ በቀጣይ ለምታደርጋቸው ምርጫዎች መሠረት ጥሎ አልፏል።

ሆኖም ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መከሰት በተጨማሪ በምርጫው ሂደት የታዩ አስተዳደራዊና የሎጅስቲክስ ችግሮች፣ ከፍተኛ የፖለቲካ ውጥረቶች፣ በምርጫ ዙሪያ የነበሩ ክሶችና ቅሬታዎች እና የተለያዩ ግጭቶች በአገሪቱ መቀስቀሳቸው ምርጫውን ከማካሄድ ጋር በተያያዘ ጉልህ መዘግየቶችና ፈታኝ ተግዳሮቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። ምንም እንኳን የትግራይ ክልልን ሳይጨምር ምርጫው በመላው አገሪቱ በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ለማካሄድ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በሐረሪ ክልል እና በሶማሌ ክልል ሙሉ በሙሉ እንዲሁም በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት (ደብብሕክመ) በከፊል ወደ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም እንዲተላለፍ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ ምርጫው በትግራይ ክልላዊ መንግሥት ሙሉ በሙሉ፣ በአብዛኞቹ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት እንዲሁም በአፋር፣ አማራ እና ኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥታት የሚገኙ ውስን ስፍራዎች የሚገኙ ዜጎች አሁንም ድምፅ የመስጠት እድል አለማግኘታቸውን እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በክልል መንግሥታት ምክር ቤቶች ውስጥ አለመወከላቸው አሳሳቢ ከመሆኑም በተጨማሪ የምርጫ ዑደቱ አሁንም መደምደሚያ አለማግኘቱን ያሳያል ብሎ ያምናል።

በ2011 ዓ.ም የተመሠረተው ከ175 በላይ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት የሆነው ሕብረት ለምርጫ በመላው አገሪቱ የተካሄዱትን ምርጫዎች እንዲታዘቡ እና የምርጫ ሂደቱን ጥራት እንዲገመግሙ በሺዎች የሚቆጠሩ በጎ ፍቃደኛ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን አሠማርቷል። የሲቪክ ምህዳሩ መከፈት እና የተሻለ የቁጥጥር መዋቅሮች መዘጋጀት የፈጠረውን እድል በመጠቀም ህብረቱ ምርጫው በተካሄደባቸው በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የነበረውን የቅድመ ምርጫ፣ የድምፅ መስጫ ዕለት እና የድኅረ ምርጫ ሂደት ከተለያዩ መስፈርቶች አንፃር ታዝቧል። የምርጫ ታዛቢነት ሥራውን በማከናወን ረገድ ህብረቱ የዜጎችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በማሳደግ የምርጫ ሂደቱን አሳታፊነት፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና አጠቃላይ ታማኝነት ለመቆጣጠር እና ለመገምገም ጥረት አድርጓል። ህብረቱ በአባል ድርጅቶቹ በኩል ከተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች መልምሎ ያሰለጠናቸውን ዜጎች በመጠቀም ያከናወነው የትዝብት ስራ ለዜጎች፣ ፖለቲካ ፓርቲዎችና ተወዳደሪዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ምርጫ ቦርድና የተለያዩ የመንግሥት ባለሥልጣናት በምርጫው ዙርያ ከፖለቲካ ወገንተኝነት የፀዳ መረጃን በማቅረብ ስለምርጫው የራሳቸውን መደምደምያ እንዲሰጡ የሚያስችል ነው።

የህብረቱ የምርጫ ትዝብት ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይፋ በተደረገው የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በምርጫ ሂደቱ የተከናወኑ ዋና ዋና የምርጫ ስራዎችን ለመገምገም ምርጫው በተካሄደባቸው የአገሪቱ ክፍሎች ሁሉ ታዛቢዎችን በማሰማራት ላይ ያተኮረ ነበር። ህብረቱ በምርጫው ዙሪያ ከመጋቢት 2013 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 2014 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት መካከል በተለያዩ መለኪያዎች በታዛቢዎቹ አማካኝነት የሰበሰባቸው ሪፖርቶች በቅድመ ምርጫ፣ የድምፅ መስጫ ዕለት እና ድህረ ምርጫ ወቅቶች ምርጫው በአጠቃላይ በምርጫ ህጉ ውስጥ የተቀመጡትን ስርዓቶች በተከተለ መልኩ እንደተከናወነ ያሳያሉ። ነገር ግን በምርጫው ዙሪያ ከተወዳዳሪነት ውስንነት፣ በአገሪቱ ውስጥ እየጨመረ ከመጣው የፀጥታ ችግር እንዲሁም ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ ችግሮች መከሰታቸው ለጊዜ ሰሌዳው አለመከበር እና ትንሽ በማይባል የአገሪቱ ክፍል ምርጫው ላለመካሄዱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። የእነዚህ ተግዳሮቶች ማጋጠም እንዳለ ሆኖ ግን የደኅንነት ስጋት ከነበረባቸው ቦታዎች ውጭ ምርጫ በተከናወነባቸው ስፍራዎች ሂደቱ በአጠቃላይ ሰላማዊ እና በቅድመ ምርጫ፣ የድምፅ መስጫ ዕለት እና በድኅረ ምርጫ ዙሮች ሂደቶች ወቅት ጉልህ የሚባሉ ከምርጫ ጋር የተያያዙ የብጥብጥ ወይም ግጭት ክስተቶች ያልታዩበት ነበር።

# አበይት የትዝብት ግኝቶች

## የመራጮች ምዝገባና የቅድመ ምርጫ ሁኔታ

በቅድመ ምርጫ ጊዜ ውስጥ ህብረቱ በመጋቢት 2013 እና ግንቦት 2013 ዓ.ም መካከል በብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የተካሄደውን የመራጮች ምዝገባ ሂደት ታዝቧል። በዚህ ወቅት ህብረቱ በምዝገባ ጣቢያዎች ከመከፈቻ አንስቶ እስከ መዝጊያ ድረስ በመቆየት የሙሉ ቀን የምዝገባ ሂደቱን የሚታዘቡ 117 ታዛቢዎችን አሠማርቶ ሂደቱን ገምግሟል።

በጠቅላላው ህብረቱ ታዛቢዎችን ከ1,200 በላይ በሚሆኑ የተለያዩ የምዝገባ ጣቢያዎችን በማሰማራት በሂደቱ ዙሪያ የተለያዩ ሪፖርቶችን ሰብስቧል። የመራጮች ምዝገባ ሂደቱ ላይ በተደጋጋሚ የተስተዋሉ መዘግየቶች፣ የጊዜ ሰሌዳ ለውጦች እና መሰረዞች በምዝገባ ሂደቱ ላይ ከተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች አንዱ ነበር።

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጊዜ ሰሌዳው ላይ ያደረጋቸውን ማሻሻያዎች አስቀድሞ በወቅቱ አለማሳወቁ በተመዝጋቢ ዜጎች ዘንድ እንዲሁም በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በምርጫው ዙሪያ በሚሰሩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ዘንድ ግራ መጋባትን በመጠኑ የፈጠረ ሲሆን ይህም መራጮች መቼ እና የት መመዝገብ እንደሚችሉ በግልፅ እንዳያውቁ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሲቪል ማህበራት ሂደቱን በአግባቡ እንዳይከታተሉ ችግሮችን ፈጥሯል ብሎ ህብረቱ ያምናል። ነገር ግን የመራጮች ምዝገባ መከናወን ከጀመረ በኋላ የህብረቱ ታዛቢዎች የምዝገባ ሂደቱ የምርጫ ህግና ስርዓትን እንዲሁም የምርጫ ቦርድን ደንቦች ባከበረ መልኩ እንደተከናወነ ሪፖርት አድርገዋል። በተጨማሪም የህብረቱ ታዛቢዎች በታዘቡባቸው ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ ሂደቱ አካታች፣ ተጠያቂና ግልጽ በሆነ መልኩ መከናወኑን በተለያዩ መስፈርቶች ታዝበው ሪፖርት አድርገዋል።

የህብረቱ ታዛቢዎች አብዛኞቹ የምዝገባ ጣቢያዎች ተደራሽ በሆኑ ስፍራዎች እንደሚገኙ ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን በአንፃሩ በአንዳንድ አጋጣሚዎች እንደፖሊስ ጣቢያ፣ የግል መኖሪያ ቤትና የፖለቲካ ፓርቲ ህንፃዎችን በመሳሰሉ በምርጫ ህጉ በተከለከሉ ስፍራዎች ምዝገባ እንደተከናወነ ሪፖርት አድርገዋል። በተጨማሪም ታዛቢዎች በተገኙባቸው ጣቢያዎች የምዝገባ ቁሳቁሶች በአብዛኛው ተሟልተው እንደነበር ሪፖርት ያደረጉ ቢሆንም በአንዳንድ አጋጣሚዎች ግን የጣት አሻራ ማንሻ፣ የምዝገባ ጣቢያ መዝገብ እና የሶስተኛ ወገን (ምስክርነት) ምዝገባ ቅፆች አለመሟላታቸው ተስተውሏል። በተጨማሪም የህብረቱ ታዛቢዎች በምዝገባ ማዕከል ኃላፊነት ከሚያገለግሉ ሴቶች ብዛትና የመራጭ ምዝገባ ቦታዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ከመሆን ጋር በተያያዘ ውሱን ተግዳሮቶች እንዳጋጠሙ ገልጸዋል።

በምዝገባ ሂደቱ ላይ በቀረቡ ቅሬታዎች፣ የፍርድ ቤት ክርክሮችና በተለያዩ የሎጂስቲክስና የፀጥታ ችግሮች ምክንያት በሰኔ ወር ምርጫ ባላካሄዱት የሐረሪና ሶማሊ ክልሎች እንዲሁም አንዳንድ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውስጥ የሚገኙ ስፍራዎች በመስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም ከተከናወነው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት አስቀድሞ ህብረቱ በነሀሴ 2013 ዓም 51 የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችን (LTOs) በማሰማራት ሂደቱን ታዝቧል። ህብረቱ ከእነዚህ 51 ታዛቢዎች 283 የትዝብት ሪፖርቶች ደርሰውታል። የህብረቱ ታዛቢዎች ከመስከረም 20 2014 ዓ.ም የድምፅ መስጫ ቀን አስቀድሞ የነበረውን የሲቪክ ምህዳር፣ የምረጡኝ ቅስቀሳ ሂደት፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዝግጅት፣ የመራጮች ትምህርት ሂደት እንዲሁም የደህንነትና ፀጥታ ምህዳር በተመለከተ መረጃዎችን ሰብስበዋል።

የህብረቱ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ስፍራዎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያደርጓቸው የምረጡኝ ቅስቀሳዎች አናሳ እንደነበሩ ሪፖርት ቢያደርጉም ቅስቀሳዎች በተከናወኑባቸው ወቅቶች ሰላማዊ እንደነበሩ ከትዝብት ሪፖርቶች መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም አብዛኛዎቹ የትዝብት ሪፖርቶች የምረጡኝ ቅስቀሳዎች በተከናወኑባቸው ወቅቶች በፀጥታ ሀይሎች የተደረገ ጣልቃ ገብነት አናሳ እንደነበር ሪፖርት አድርገዋል። በመጨረሻም ታዛቢዎቹ የምርጫ ቅስቀሳ በተካሄደባቸው ቦታዎች ወይም የምርጫ ትምህርት በተሰጠባቸው ቦታዎች የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል መወሰድ የነበረባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዳልተከበሩ ሪፖርት አድርገዋል። ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የሚታየው ክፍተት ከቅድመ ምርጫ ወቅት በተጨማሪ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ወቅት በአብዛኛው የተስተዋለ ችግር እንደነበር ህብረቱ አስተውሏል።

# የድምፅ መስጫ ዕለት ግኝቶች

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ በምርጫ ቀን የድምፅ አሰጣጥና አቆጣጠር ሂደቱን ለመታዘብ እንዲያስችለው ለሰኔ 14፣ 2013 ዓ.ም ምርጫ 2,050 ታዛቢዎችን ያሰማራ ሲሆን ለመስከረም 20 2014 ምርጫ ደግሞ 941 ታዛቢዎችን አሰማርቷል። የህብረቱ ታዛቢዎች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በተካሄደባቸው ሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕዝበ ውሳኔ ድምፅ በሰጡ ማኅበረሰቦች፣ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ ድምፅ በተሰጠባቸው የአዲስ አበባና ድሬዳዋ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች እና በሶማሊ ክልል በሚገኘው የቆሎጂ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች (IDP) ጊዜያዊ ማቆያ ጣቢያ በተቋቋሙ ጣቢያዎች ተሰማርተው ሂደቱን ታዝበዋል። በህብረቱ ከተሰማሩት የምርጫ ቀን ታዛቢዎች አብዛኛዎቹ ለመታዘብ እንደተፈቀደላቸው ለህብረቱ ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን ከእውቅና አሰጣጥ መዘግየት እና በአንዳንድ አስፈፃሚዎች ከተደረጉ ክልከላዎች ከፈጠሩት መስተጓጎል በስተቀር ህብረቱ ምርጫ ቦርድ ለታዛቢዎች የእውቅና ባጅን በመስጠቱ እንዲሁም የምርጫ አስፈጻሚዎች በአብዛኛው እውቅና የተሰጣቸው ታዛቢዎች ያላቸውን ምርጫ ጣቢያ ውስጥ የመግባት መብት ማክበራቸውን እውቅና ሊሰጥ ይወዳል። ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች አወቃቀር፣ አከፋፈት እና አዘጋግ ዙሪያ እንዲሁም በድምፅ አሰጣጥ እና አቆጣጠር ዙሪያ የድምፅ መስጫ ዕለት መረጃዎችን ወደ ህብረቱ ሪፖርት አድርገዋል።

እንደህብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት በሰኔ እና በመስከረም የተደረገው የድምፅ አሰጣጥ እና አቆጣጠር ሂደት የምርጫ ህጉን እንዲሁም በምርጫ ቦርድ የወጡ ደንቦችን ባከበረ መልኩ የተከናወነ ነበር። ጥቂት ቢሆኑም በአንዳንድ አጋጣሚዎች የምርጫ ጣቢያዎች እንደ ፖሊስ ጣቢያ፣ የወታደር ካምፕ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ጽሕፈት ቤት በመሳሰሉ በምርጫ ህጉ በተከለከሉ ቦታዎች የተመሰረቱባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። በአብዛኛው ምርጫ ጣቢያዎች በወቅቱ የተከፈቱ ሲሆን ህጉ በሚጠይቀው መሰረት የህብረቱ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች ከድምፅ አሰጣጥ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች በግልፅ በሚታዩ ቦታ ተቀምጠው እንደነበር ሪፖርት አድርገዋል።

በተጨማሪም በድምፅ አሰጣጥ ወቅት በአብዛኛው የሂደቱ ምስጢራዊነት መከበሩን እና አስፈፃሚዎች የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት የምርጫ ቦርድን ማህተም ሲያደርጉ እንደነበር ሪፖርት ተደርጓል። ቆጠራን በተመለከተ የድምፅ ቆጠራው በአብዛኛው የህብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው ጣቢያዎች ያለምንም መስተጓጎል እንደተከናወነ ታዛቢዎች ገልፀዋል። ነገር ግን የህብረቱ ታዛቢዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች በመራጮች ጣት ላይ የማይጠፋ ቀለም ያልተደረገበቸው እና የውጤት እና ማስታረቅያ ቅፆች ከቆጠራ በኋላ ያልተለጠፈባቸው የምርጫ ጣቢያዎች እንደነበሩ ገልፀዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ምንም እንኳን በመስከረሙ ምርጫ በአብዛኛው የተስተካከሉ ቢሆኑም በሰኔው የምርጫ ቀን የተስተዋሉ የተለያዩ መሰረታዊ ችግሮች ነበሩ። ከእነዚህ ጉድለቶች መካከል እጅግ ጎልቶ የታየው የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን፣ የድምፅ መስጫ ሣጥኖችን፣ የመራጭ ጥቅሎችና የማይለቅ ቀለምን ጨምሮ የተለያዩ የምርጫ ማስፈጸሚያ ቁሳቁሶች አለመኖር ወይም በበቂ ሁኔታ አለመገኘት ነው። ይህም ጉድለት የድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደቱ እንዲዘገይ እና በአንዳንድ ቦታዎች እስከ ቀጣዩ ቀን ድረስ እንዲራዘም አስገድዶ ነበር። በተጨማሪም በሰኔ ወር በተካሄደው ምርጫ የተሳተፉ ታዛቢዎች ከምርጫ ህጉ በተቃራኒ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ወይም በጣቢያዎች 200 ሜትር አካባቢ የምርጫ ቅስቀሳና ቁሳቁሶች እንደነበሩ ሪፖርት ማድረጋቸውና ጣቢያዎች የአካል ጉዳት ወይም የመንቀሳቀስ ውስንነት ላላቸው መራጮች ምቹ እንዳልነበሩ ገልፅዋል።

የታዛቢዎች ሪፖርቶች በተጨማሪም የምርጫ ቀን ሂደቱ አሳታፊነት ደረጃን ከፍ ለማድረግ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተደረጉ ጥረቶችን መዝነዋል። በሁለቱም ምርጫዎች ወቅት ምርጫ የተካሄደባቸው አብዛኞቹ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ የነበሩ ሲሆን ታዛቢዎች ከተገኙባቸው ጣቢያዎች በአብዛኛዎቹ አካል ጉዳተኞች ወይም የመንቀሳቀስ ውስንነት ያለባቸው መራጮች በሰልፍ ላይ ቅድሚያ እንደተሰጣቸው ሪፖርት አድርገዋል። በተጨማሪም በአብዛኛው እገዛ የሚያስፈልጋቸው መራጮች እገዛ በሚያስፈልጋቸው ወቅት በመረጡት ሰው እገዛ እንዲያገኙ መደረጉን ሪፖርት አድርገዋል። በአንድ አራተኛ ያክሉ ህብረቱ በታዘባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የምርጫ ቁሳቁሶች ከአማርኛ ውጭ በሌሎች ቋንቋዎች ቀርበዋል። በተጨማሪም ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች ከተገኙ አስፈፃሚዎች መካከል የሴቶች ድርሻ ከአንድ ሶስተኛ በላይ ሲሆን በተጨማሪም ውስን ቢሆኑም በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች አስፈፃሚዎች ሙሉ በሙሉ ሴቶች የነበሩበት አጋጣሚ እንደነበር ህብረቱ ታዝቧል። ነገር ግን ሴቶች በምርጫ ጣቢያ ኃላፊነት ያገለገሉባቸው የምርጫ ጣቢያዎች አንድ አራተኛ ብቻ መሆኑ የሴቶችን ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንፃር በምርጫ ቦርዱ ተጨማሪ ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው አሳይቷል።

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተጨማሪም ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር ተያያዥ የሆኑ ስጋቶችን ማቅለያ ቅድመ እርምጃዎችን ወስዷል። አብዛኞቹ ምልከታ የተካሄደባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የተዘጋጁት በጣቢያዎቹ ውስጥ ማኅበራዊ ርቀትን ለመጠበቅ በሚያስችል መልኩ ነበር። ሆኖም በአንፃሩ ማህበራዊ ርቀትን መራጮች ወደ ጣቢያዎቹ ለመግባት በሚሰለፉባቸው ቦታዎች ማረጋገጥ አስቸጋሪ እንደነበር ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪም የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች በምርጫው ቀን ሙሉ በሙሉ ወይም በተወሰነ መልኩ የፊት እና የአፍንጫ ጭምብሎችን (FaceMask) ለብሰው ሲሰሩ የነበረ ቢሆንም በመራጮች ዘንድ ጭምብልን ከማድረግ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ክፍተቶች ታይተዋል። በተጨማሪም የምርጫ ቦርድ መመሪያ ከሚያዘው በተቃራኒ ፊታቸውን ቢሸፍኑም መደበኛውን የፊት ጭምብል ባለማድረጋቸው እንዳይመርጡ የተከለከሉ መራጮች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።

## ድኅረ ምርጫ

ሁለቱንም የምርጫ ቀናትን ተከትሎ በነበሩት የድኅረ ምርጫ ጊዜያት ህብረቱ ለምርጫው ውጤት ህዝቡ ባሳየው ምላሽ፣ በሲቪክ ምህዳሩ ላይ በነበሩ ውሱንነቶች ወይም ክልከላዎች፣ የምርጫ አለመግባባቶች በሚስተናገዱባቸው አሠራሮችን እና በፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታው ዙሪያ መረጃን የሚሰበስቡ 97 የድህረ ምርጫ ታዛቢዎችን ለሰኔው ምርጫ እንዱሁም 49 የድህረ ምርጫ ታዛቢዎችን ለመስከረሙ ምርጫ አሰማርቶ 568 (ሰኔ) እና 282 (መስከረም) ሪፕርቶችን ሰብስቧል። በአጠቃላይ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው የአገሪቱ ክፍሎች በድኅረ ምርጫ ወቅት የተከሰቱ የግጭት፣ ዐመፅ እና ተቃውሞ ክስተቶች ወይም በእንቅስቃሴ ላይ የተጣሉ እገዳዎች እንዳልነበሩ ሪፖርት አድርገዋል።

ሆኖም መራጮችና የፖለቲካ ፓርቲዎች በተገለጹት ውጤቶች ላይ እምነት እንደሌላቸው ቅሬታ ያነሱባቸው አንዳንድ ክስተቶች ነበሩ። ህብረቱ በተጨማሪም ከቅሬታ አሰማም ስርዓቱ ጋር በተያያዘ በምርጫ ህጉ እና በምርጫ ቦርድ መመሪያዎች ላይ በተቀመጠው መልኩ አለመከናወኑን የታዘበ ሲሆን፤ ምንም እንኳን ህጉ በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች እንደሚቋቋሙና አቤቱታ በምርጫ ክልል ደረጃ እንደሚሰማ በግልፅ ቢደነግግም ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአንፃሩ የቅሬታ እርከኖችን ወደጎን በመተው ሁሉንም ቅሬታዎች በአዲስ አበባ ባደረገው የቅሬታ አሰማም ስርዓት ማየቱን ህብረቱ ታዝቧል።

ከስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ የድኅረ ምርጫ ወቅት ከተነሱ ቅሬታዎች መካከል ከቆጠራና በሠንጠረዥ ማስቀመጥ ወጥነት አለመኖር ጋር ተያያዥ የሆኑ ቅሬታዎችን፤ የፓርቲ ተወካዩች ወደምርጫ ጣቢያዎች እንዳይገቡ መከልከልን የተመለከቱ ቅሬታዎችን፤ የፓርቲ ተወካዮች የቆጠራ ሂደቱን እንዳይታዘቡ መባረራቸውን የተመለከቱ ቅሬታዎችን፤ በመራጮች ላይ የተደረጉ ማስፈራራቶችን፤ በስልጣን ላይ ባለው ፓርቲ የተደረጉ ጣልቃ ገብነቶችን እና በመንግሥት ባለሥልጣናት በተጣሉ መደበኛና ኢ-መደበኛ ገደቦች የተነሣ በመንቀሳቀስ መታዘብ/መቆጣጠር አለመቻልን የተመለከቱ ቅሬታዎችን ይጠቀሳሉ።

ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሕግ ክፍል ህብረቱ የሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው የሰኔውን ምርጫ ተከትሎ 31

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ስድስት የግል ዕጩዎች በ212 የምርጫ ክልሎች ላይ ቅሬታዎችን ያቀረቡ ሲሆን በመስከረም ወር ደግሞ ስድስት ፓርቲዎች እና 24 የግል ተወዳዳሪዎች በ25 የምርጫ ክልሎች ላይ ቅሬታ አቅርበዋል። ሆኖም አብዛኞቹ ቅሬታዎች በቂ ማስረጃ አልቀረበባቸውም በሚል መነሻ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውድቅ የተደረጉ መሆናቸው ልብ ሊባል ይገባል። በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውድቅ የማድረግ ውሳኔ ያልተደሰቱ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ተወዳዳሪዎች ለፍርድ ቤቶች ይግባኝ ያስገቡ የነበረ ቢሆንም ለፍርድ ቤት ከቀረቡት ይግባኞች ውስጥ አብዛኞቹ በምርጫ ሕጉ ሥር የተደነገገውን ቅሬታ የማቅረቢያ ቀነ ገደብ ባለማክበራቸው ምክንያት ውድቅ ተደርገዋል።

# ዋና ዋና ምክረ ሐሳቦች

ከላይ እንደተመለከተው ስድስተኛው አገር አቀፍ እና የክልል ምርጫዎች ጫና በበዛበት እና ሁኔታዎች በተከታታይ በሚቀያየሩበት ሁኔታ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሁለት ዙሮች ተካሂደዋል። ስለሆነም ህብረቱ ይህን ዕድል በመጠቀም የተከሰቱበትን የሎጅስቲክስ፣ የፀጥታ እና ሌሎች ተግዳሮቶችን በመቋቋም አገሪቱ በፖለቲካ ሽግግሮችን በምታከናውንበት እና የተለያዩ የለውጥ ውጥኖች በምትፈፅምበት ወቅት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ምርጫውን በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች ማካሄድ በመቻሉ እውቅናን ይሰጣል። በተጨማሪም ህብረቱ በቅድመ ምርጫው ወቅት፣ በምርጫው ቀን እና በድኅረ ምርጫ ወቅት በተሰበሰበው መረጃ ላይ ተመሥርቶ የኢትዮጵያ ምርጫ ላይ ጉልህ ሚናዎችን ለተጫወቱት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን ምክረ ሐሳቦች ይሰጣል።

## ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስድስተኛው የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫ በሰኔ 2013 እና በመስከረም 2014 ዓም የሚካሄዱበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ ጥንካሬና ቁርጠኝነቱን አሳይቷል። ሆኖም የስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ አፈፃፀም በአዲስ መልኩ የተዋቀረው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ሊያጤናቸው የሚገቡ የተለያዩ አስተዳደራዊና ተቋማዊ ክፍተቶች እንዳሉበት አሳይቶ አልፏል ብሎ ኅብረቱ ያምናል። በአጠቃላይ ምርጫው የተከናወነበትን ሁኔታ ስንመለከት ምንም እንኳን ምርጫው በተከናወነበት ወቅት የተለያዩ ከቦርዱ አቅም በላይ የነበሩ ችግሮች ቢኖሩም በተቻለው መጠን ምርጫ ቦርድ የድምፅ መስጠት ስርዓቱን በተቀራረጠ መልኩ ማከናወንን በማስቀረት ምርጫን በተመሳሳይ ቀን ማካሄድ ይኖርበታል። በተጨማሪም የምርጫ ቦርድ ከምርጫ ሂደቱ መጀመር አስቀድሞ ግልፅ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳን እንዲሁም በምርጫ ሂደቱ ላይ ስራ ላይ የሚውሉ መመርያዎችን አስቀድሞ በማውጣት መራጮች፣ ተወዳዳሪዎች፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገቢውን ዝግጅት እና ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተጨማሪ ምክረ ሀሳቦች በምርጫው ዙሪያ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ በመመስረት ህብረቱ ለብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የሰጣቸው ናቸው፡

- ቦርዱ የምዝገባ ቦታዎችን እና የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን በተቻለ መጠን ለሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የእንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ዜጎች (ሕፃናት የሚይዙ ሴቶች፣ አረጋውያን፣ ወዘተ) እና ለሁሉም የማኅበረሰብ አባላት ተደራሽ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማዘጋጀት አለበት። በተጨማሪም ቦርዱ የምዝገባና ድምፅ መስጫ ቦታዎችን በሚያቋቁምበት ወቅት በሙሉ የዜጎችን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን፣ የታዛቢዎችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮችን እና የምርጫ ተፎካካሪዎችን ደኅንነት ለማረጋገጥ በሚያስችል ከአካባቢ ለማዋቀር ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት ይጠበቅበታል።

- የሎጅስቲክስ ቅንጅት ችግሮች በስድስተኛው ምርጫ በምርጫ ቦርድ ላይ ከተስተዋሉ ክፍተቶች አንዱ ነው። ኅብረቱ ቦርዱ በቀጣይ በሚካሄዳቸው ምርጫዎች ትክክለኛ የምርጫ ቁሳቁሶች ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ለማሠራጨት የተሻሉ የድርጊት ዕቅዶች መቅረጽ እንዳለበት በእጅጉ ያምናል።

- ህብረቱ በተጨማሪም ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በግጭት ምክንያት ከመኖሪያ ቦታቸው የተፈናቀሉ እና በሰኔና በመስከረም ወር በተለያዩ ምክንያቶች ድምፅ ባልተሰጠባቸው ስፍራዎች የሚኖሩ ዜጎችን ጨምሮ በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ላይ መሳተፍ ያልቻሉ ዜጎችን የመምረጥ መብት ለማስጠበቅ ምርጫውን ማካሄዱን ጨምሮ የተለያዩ ስራዎችን ሊያከናውን ይገባል።

- በቅርብ በተካሄዱት ምርጫዎች ላይ የነበረው የሴቶች ተሳትፎ የሚበረታታ ቢሆንም አሁንም የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ ዘርፈብዙ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል። ህብረቱ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሴቶች በምዝገባና ድምፅ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ መወከላቸውን በማረጋገጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የመሪነት ሚና መጫወት እንዳለበት ህብረቱ ያምናል። በተጨማሪም ህብረቱ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አካል ጉዳተኞች በምርጫ ሂደት ላይ እና በተለያዩ ዲሞክራሲያዊ ሂደቶች ላይ የበለጠ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሊሰራ ይገባል።

በስድስተኛው አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ወቅት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ከተቸገረባቸው ጉዳዮች አንዱ የመራጮች ምዝገባ ሂደቱ ነበር። ከሎጅስቲክስ ጋር ከተያያዙ ተግዳሮቶች በተጨማሪ ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በአገሪቷ የምርጫ ህግ ላይ የተቀመጡት የመራጮች ምዝገባ አሰራሮች እና የመራጮች ማንነት ማጣሪያ መስፈርቶች የሚስተዋልባቸውን ክፍተቶች በግልፅ አሳይቷል። በቀጣይ ቦርዱ የተመዘገቡ መራጮ ዝርዝርን ከመጠቃለሉ በፊት በገለልተኛ አካላት እና ተወዳዳሪዎች መመርመር እንዲችል የአሰራር ግልጽነት መዘርጋት እና ከድምፅ መስጫ እለት አስቀድሞ የመራጮችን ዝርዝር ይፋ ማድረግ አለበት። በተጨማሪም መሰረታዊ የአሰራር ግድፈቶችን ለማስተካከል እና በመራጮች መዝገብ ላይ ያለውን ተዓማኒነት ለማሳደግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የመራጮች ምዝገባ አሰራሮችን በማጤን የአሰራር ለውጥ ሊያደርግ ይገባል ብሎ ህብረቱ ያምናል።

በምርጫው ቀን ሥነ ሥርዓቶችን ከመከተል ጋር በተያያዘ የህብረቱ አጠቃላይ ትዝብት ስድስተኛው የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫ የምርጫ ህጉን በተከተለ መልኩ እንደተከናወነ ያሳያል። ሆኖም በምርጫው ቀን በመራጮች ጣት ላይ ድምፅ እንደሰጡ የሚያሳይ የማይለቅ የጣት ቀለም ካለማድረግ፣ ለመምረጥ የተመዘገቡና ራሳቸውን የሚገልፅ መረጃ ያላቸው መራጮችን እንዳይመርጡ ከማድረግ እና በመራጮች መዝገብ ላይ የሌሉ ዜጎች እንዲመርጡ ከመፍቃድ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ክፍተቶች ተስተውለዋል። ይህም ቦርዱ ሊያስተካክላቸው ከሚገቡ የአሰራር ግድፈቶች መካከል አንዱ እንደሆነ ህብረቱ ያምናል።

በምርጫ ሂደቱ ወቅት የሚነሱ ቅሬታዎችን መመልከትና ተገቢውን ውሳኔ ማሳለፍ ከቦርዱ ዋና ዋና ተግባራት መካከል አንዱ ነው። በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ምንም እንኳን በህግ የተደነገጉ የተለያዩ የአቤቱታ መስሚያ ኮሚቴዎች በአወቃቀሩ ስር ቢኖሩም ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች፣ በምርጫ ክልሎች እና በክልል ደረጃዎች የሚገኙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች መጠቀም አልቻለም ነበር። ህብረቱ ቦርዱ የምርጫ ቅሬታዎችን እና አለመግባባቶችን የሚፈቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች (GHCs) በሁሉም ደረጃዎች መቋቋማቸውን እና በአግባቡ መሥራታቸውን ማረጋገጥ አለበት ብሎ የሚያምን ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ቦርዱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አሰራር አሁን በሚገኝበት አወቃቀር አቋም በግልፅ ከታዩት የአስረአር ተግዳሮቶች ባሉበት የፖለቲካ ተግዳሮቶች አንፃር ሊመረምርና የተሻሉ የአሰራር ዘዴዎችን ሊያጤን እንደሚገባው ህብረቱ ያምናል የተነሣ የወቅቱን የቅሬታ መስሚያ ሥነ ሥርዓቶች መርምሮ ማሻሻያ ስለማድረግ ማጤን አለበት።

## ለባለድርሻ አካላት የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች

ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ በአገሪቱ የምርጫ ህግ ላይ የሚስተዋሉ የህግ ክፍተቶችን አሳይቶ አልፏል። ህብረቱ የሚመለከታቸው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች እና የመንግሥት ሚኒስቴሮችን ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የምርጫ ኃላፊዎች፣ የሲቪል ማህበራት ተወካዮች፣ ታዛቢዎች፣ ምሁራን፣ ባለሙያዎች እና ዜጎች ጋር በመወያየት የምርጫ ህጉ ውስጥ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ሊሰሩ ይገባል ብሊ ያምናል።

ህብረቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ሂደቱ የሚያጋጥሟቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች እንዳሉ ቢያምንም በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ሂደት ላይ ሙሉ ለሙሉ እንዲሳተፉ ምክረ ሀሳቡን ያቀርባል። ቀጣይነት ያለው የፓርቲዎች ተሳትፎ በአገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚሰሩ ስራዎች ይደግፋል ብሎ ህብረቱ ያምናል። ከዚህ በተጨማሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በወደፊት በሚሳተፉባቸው ምርጫዎች ላይ የሴት እጩዎችን ቁጥር በማሳደግ የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ ተገቢውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባቸዋል። በመጨረሻም ህብረቱ በአገሪቱ የሚደረጉ ምርጫዎችን ተዓማኒነትና ግልፅነት ለማረጋገጥ ፓርቲዎችን በምዝገባ እና ምርጫ ጣቢያዎች የፓርቲ ተወካዮችን በበለጠ ሊያሰማሩ እንደሚገባ ህብረቱ ያስታውሳል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በተለያዩ ደረጃዎች በስድስተኛው የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች ላይ ተሳትፈዋል። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በቀጣይ ምርጫዎች ላይ በአገሪቱ እየተከፈተ የመጣውን አስቻይ የሲቪክ ምህዳር በመጠቀም በንቃት ተገቢውን ሚና መጫወታቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው ብሎ ህብረቱ ያምናል። በተጨማሪም አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚገጥማቸውን የገንዘብ፣ የእውቀት እና የክህሎት እጥረት ከግምት ውስጥ በማስገባት አጋሮችና ለጋሽ ድርጅቶች የበለጠ ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ የመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) ለመራጮች ትምህርት፣ ለምርጫ ቅሰቀሳ እና ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የክርክር መድረኮችን በማመቻቸት ከሚጫወቱት ቁልፍ ሚና ባሻገር በምርጫ ወቅት ይበልጥ ንቁ የሆነ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ጥሪውን ኅብረቱ ያቀርባል። በተጓዳኝ መገናኛ ብዙኃን የሚጠበቅባቸውን ሚና በመጫወት እና በምርጫ እና ሌሎች አገራዊ ጉዳዮች ስራዎችን በሚሰሩበት ወቅት ሙያዊ ስነምግባርን ባከበረ መልኩ ሊከወን ይገባል ብሎ ህብረቱ ያምናል።

# ምዕራፍ ፩፡ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ

## ድኅረ 2010 ዓ.ም ፖለቲካዊ ምህዳር

ከ2007 ዓ.ም አንስቶ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየተስፋፋ የመጣውን መጠነ ሰፊ ተቃውሞ ተከትሎ የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አስተዳደር በመጋቢት 2010 ዓም ወደ ስልጣን ከመጣ ወዲህ ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ ፖለቲካዊ ታሪክ ያልተለመዱ ወሳኝ ለውጦችን አስተናግዳለች። በትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር (ትሕነግ) በሚመራው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲዊ ግንባርን (ኢሕአዴግ) ፖለቲካዊ የበላይነት እንዲያበቃ ያስቻለው የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አስተዳደር በአገሪቱ የተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የማሻሻያ (ሪፎርም) አጀንዳዎችን በማስተዋወቅ ስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ የሚካሄድበትን ምህዳር ቅርፅ በማስያዝ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። የፖለቲካ እስረኞች መፈታት እና በውጭ አገር የነበሩ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ወደየአገራቸው እንዲመመለሱ መጋበዛቸው ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በ1997 ዓ.ም ከተካሄደው ምርጫ ቀጥሎ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ፉክክር ይታይበታል ተብሎ እንዲጠበቅ አድርጐታል። ይህን ጥሪ በመቀበል የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ አስተዳደር ወደ ሥልጣን ከመጣ አንስቶ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በውጭ አገር ከነበሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል አርበኞች ግንቦት 7፣ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)፣ እና የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ከመከናወኑ በፊት ከተከሰቱ ወሳኝ ፖለቲካዊ ለውጦች ሌላኛው የኢሕአዴግ በህዳር 21 ቀን 2012 ዓ.ም መክሰም ነበር። በአንድ ወቅት የአገሪቱን ፖለቲካ ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ተቆጣጥሮ የነበረው ከተለያዩ በዘር ላይ የተመሰረቱ ፓርቲዎች ህብረት የነበረው ኢህአዴግ በህዳር 21፣ 2012 ከስሞ በአዲሱ የብልፅግና ፓርቲ መተካቱ ይታወሳል። ነገር ግን ከመሰል የግንባሩ አባል ፓርቲዎች በተቃራኒው በፓርቲው ውስጥ የጐላ ተፅዕኖ የነበረው የትግራይ ህዝቦች ነፃ አውጪ ግንባር (ትህነግ/ህወሃት) በፓርቲው ውስጥ ላለመቀጠል መወሰኑ ፓርቲው ምንም እንኳን በወቅቱ የትግራይ ክልልን እያስተዳደረ የነበረ ቢሆንም ከምርጫው አስቀድሞ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጎራ እንዲቀላቀል አድርጎታል። በአንፃሩ ብልፅግና ፓርቲ ***የአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አዴፓ)፣ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዴፓ)*** እና ***የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢሕዴን)*** መዋሀድ ተከትሎ በኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ተመዝግቦ ህጋዊ እውቅናን አግኝቷል። ከእነዚህ ፓርቲዎች በተጨማሪም ***የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አብዴፓ)፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (ቤጉህዴአግ)፣ የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢሶሕዴፓ)፣ የጋምቤላ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋሕዴን)*** እና ***የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ (ሀብሊን)*** ውህደቱን መቀላቀላቸውን ተከትሎ ፓርቲው በአገሪቱ ትልቁ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲሆን አስችሎታል። ሆኖም አዲስ የተመሰረተው የብልፅግና ፓርቲ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደሙ ባይሆንም በክልል ላይ የተመሰረተ አደረጃጀትን ከኢህአዴግ እንደወረሰ ማስታወስ ያስፈልጋል።

## ቀደምት ምርጫዎች

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) ሕገ መንግሥት ከጸደቀበት ከ1987 ዓ.ም ወዲህ ኢትዮጵያ አምስት ተከታታይ አገር አቀፍ እና የክልል ምክር ቤት ምርጫዎችን (በ1987፣ በ1992፣ በ1997፣ በ2002 እና በ2007) አካሂዳለች። ሆኖም ሁሉም ምርጫዎች ማለት በሚያስችል ደረጃ ለአገሪቱ መድብለ ፓርቲ ስርዓት ይህ ነው የሚባል አስተዋፅኦ ያላደረጉ ምርጫዎች የነበሩ ሲሆን "ሁሉም ምርጫዎች በፖለቲካ ፓርቲዎችና አለምአቀፍ ታዛቢዎች እንደነፃና ፍትሀዊ ምርጫ እውቅና ያልተሰጣቸው ነበሩ።"1 ከእነዚህ የምርጫ ዙሮች መካከል በ1997 ዓ.ም የተካሄዳው ሶስተኛው አጠቃላይ ምርጫ የበለጠ ፖለቲካው ፉክክር የታየበት እና ከሌሎች ምርጫዎች ጋር ሲነፃፀር ሲቪል ማህበረሰቡ እና ሚድያው ንቁ ተሳትፎ ያደረጉበት ነበር። ምንም እንኳን ምርጫ 97 በአንፃሩ የተሻለ ምርጫ የነበረ ቢሆንም የተደመደመው በድህረ ምርጫ ግጭቶች እና በሲቪክ ምህዳሩ ላይ በተደረገ ከፍተኛ ጫና ነበር። ከ1997ቱ ምርጫ ቀጥሎ የሲቪክ ምህዳሩን በእጅጉ ያጠበቡ ህጎች ፀድቀው ስራ ላይ ውለዋል። ይህም የሚድያ ባለሙያዎች፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪክ ማህበራትና የመብት ተሟጋች ቡድኖች እንዲዳከሙ አድርጓል። በዚህ የተነሳ ቀጥለው በ2002 እና በ2007 ዓ.ም የተካሄዱት ምርጫዎች ፉክክር

1 Getahun Kassa (2018) Contribution to the 3rd Cycle Universal Periodic Review (UPR)A Joint UPR Submission on The Federal Democratic Republic of Ethiopia's implementation of recommendations from UPR second cycle on Civil and Political Rights pp.15-17

የተሞላባቸውና አሳታፊ ሳይሆኑ አድርጓቸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በወቅቱ አገሪቱን ይመራ የነበረው ኢህአዴግ በ2002 ዓም 99 በመቶ መቀመጫዎችን እንዲሁም በ2007ቱ ምርጫ ሁሉንም መቀመጫዎች (100%) ማሸነፉ እንደማሳያ ሊጠቀስ ይችላል። የ2007 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ በጥቂት ወራት ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ህዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ጀመሩ። እነዚህ ተቃውሞዎች ከመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ሀይልን የተጠቀሙ ምላሾችን ያስከተሉ ሲሆን፤ በአማራ እና ኦሮምያ ክልሎች ጎዳናዎች ላይ የተከሰቱት ህዝባዊ አመፆች ገዢው ፓርቲ የተለያዩ ውስጣዊ ለውጦችን (ሪፎርሞችን) እንዲያደርግ አስገድደውት ነበረ። በመጋቢት 2010 ዓ.ም የኢህአዴግ ጠቅላላ ጉባኤ ፓርቲው ዶ/ር አብይ አህመድን ሊቀመንበር አድርጎ መሾሙን ተከትሎ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ተደርገው ተመርጠዋል። ከስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ሁለት አመት አስቀድሞ የአዲሱ አስተዳደር ስልጣን መያዝ በምርጫው ላይ በተለያዩ አካላት ዘንድ ከፍተኛ ተስፋን ያጫረ የነበረ ሲሆን የለውጥ (ሪፎርም) አጀንዳው የተለያዩ የህግና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን በማድረግ የሲቪክ ምህዳሩ እንዲሰፋ ወሳኝ እርምጃዎችን ወስዷል።

# የግንቦት 2012ቱ አጠቃላይ ምርጫ መተላለፍ

ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ «ለረጅም ጊዜ ከዘለቁት ያለመረጋጋት ወይም ግልጽ ግጭቶች ምንጭ ከሆኑት የዘር ውጥረቶች ጋር የተያያዙ»[2] በርካታ ፖለቲካዊና የደኅንነት ቀውሶችን አስተናግዳለች። የስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ከግንቦት 2012 መተላለፍ ተከትሎ የተከሰቱት ፖለቲካዊ አለመግባባቶች ደግሞ እነዚህ የተስፋፉ ፖለቲካዊና የደህንነት ቀውሶች የበለጠ ስር እንዲሰዱ አድርገዋል። ምርጫው በመጀመርያ በምርጫ ቦርድ የዝግጅት እጥረት ምክንያት ሁለት ጊዜ ተላልፎ በነሐሴ 23 2012 ዓ.ም እንዲደረግ ውሳኔ ተላልፎ የነበረ ሲሆን በመቀጠል የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ በአገሪቱ መከሰቱን ተከትሎ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ምርጫውን በነሐሴ 23 ቀን ማካሄድ እንደማይችል በማሳወቅ ለህዝብ ተከታዮች ም/ቤት ምርጫው እንዲራዘም ምክረ ሀሳቡን ማቅረቡ የሚታወስ ነው። ምክር ቤቱ በበኩሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤትን፣ የፌዴሬሽን ም/ቤትን እና የክልል ም/ቤቶችን እንዲሁም የፌደራልና ክልል አመራሮችን የስልጣን ዘመን ማራዘሙ ህገ መንግስቱን የተከተለ ውሳኔ እንደሆነ በመግለፅ የኮቪድ-19 ወረርሺኝ በማህበረሰቡ ጤና ላይ የሚያሳድረውን የጤና ችግር መቆቆጣጠር እስከሚቻል ድረስ ምርጫውን እንዳራዘመ ይታወቃል።

ይህ ጠቅላላ ምርጫውን ላልተወሰነ ጊዜ ለማራዘም የተወሰነው ውሳኔ በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ ተቃውሞን ያስነሳ ሲሆን በዋነኝነት ***የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)***፣ ***የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ)***፣ ***የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር (ትህነግ/ህወሃት)*** እና ***የኦጋዴን ብሔራዊ የነጻነት ግንባር (ኦብነግ)*** ተጠቃሽ ፓርቲዎች ናቸው። ይህንንም ተከትሎ ምንም እንኳን ቦርዱ የትግራይ ክልላዊ ም/ቤት ክልላዊ የምርጫ አስፈፃሚን በማዋቀር ምርጫውን በትግራይ ክልል ለማድረግ የወሰነውን ውሳኔ በተደጋጋሚ ቢቃወምም በክልሉ በጳጉሜ 4፣ 2012 ዓ.ም ምርጫ ተካሂዷል። ይህ በጳግሜ 2012 በተናጠል የተከናወነው ክልላዊ ምርጫ በብልፅግና ፓርቲና በህወሃት መካከል እንዲሁም በፌደራል መንግስቱና በትግራይ ክልላዊ መንግስት መካከል የነበረውን ሻካራ ግንኙነት እንዲባባስ አድጓል።

# ስድስተኛው ብሐራዊና ክልላዊ ምርጫ እና የደህንነት ችግሮች

ከቀዳሚ ምርጫዎች ጋር ሲነጻጸር የኢትዮጵያ ስድስተኛው ብሔራዊና የክልል ምርጫ የተካሄደው በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች በከፍተኛ ደረጃ የደኅንነት ስጋቶች በተስፋፉበት ሁኔታ ነበር። የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር በኅዳር 24 ቀን 2013 ዓ.ም ባደረጉት ንግግር መሠረት አዲሱ አስተዳደር ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት ቀርበው ንግግሩን እስካደረጉበት ቀን ድረስ 113 የጥቃት/አመፅ ክስተቶች አጋጥመው ነበር።[3] ይህ እየተባባሰ የመጣው የደኅንነት ችግር በ2013ቱ አጠቃላይ ምርጫ አፈፃፀም እና የሁሉንም ዜጋ የመምረጥ መብት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አድርጓል።

የሕወሃት ኃይሎች በኢትዮጵያ የሃገር መከላከያ ሠራዊት የሰሜን ዕዝ ላይ የሰነዘሩትን ጥቃት ተከትሎ በጥቅምት 2013 ዓ.ም በትግራይ ክልላዊ መንግሥት የተቀሰቀሰው ግጭት በክልሉ ውስጥ ምርጫ እንዳይካሄድ አስገድዷል። ግጭቱ ከተቀሰቀሰበት ጊዜ አንስቶ የትግራይ ክልላዊ መንግሥትን ከቀሪው የአገሪቱ ክፍል ጋር እንዲነጠል ማድረጉ የምርጫ ቦርድ ክልሉን በስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ የዝግጅት ሥራዎቹ ውስጥ ላለማካተት ቀደም ብሎ እንዲወስን አድርጎታል። ሆኖም ከዚያ በኋላ ግጭቱ ወደ ሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በተለይም ወደ አማራ እና የአፋር ክልላዊ መንግሥታት ተስፋፍቷል። በተጨማሪም ራሱን ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር በመነጠል በመንግስት ላይ የትጥቅ ትግልን ያወጀው ኦነግ

2 Joint IRI-NDI Virtual Pre-Election Assessment Delegation Report Summary of Findings and Priority Recommendations MAY 13, 2021 p.3)

3 ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያደረጉት ንግግር (bit.ly/3AB6SKZ)

ሸኔ በምዕራብ ኦሮምያ እና ጉጂ አካባቢዎች ከፍተኛ የደህንነት ስጋት ሆኗል።

እነዚህ ግጭቶች የምርጫ ቦርድ በአካባቢዎቹ መራጮችን መመዝገብ እና ምርጫዎቹን በሰኔና መስከረም ወር የምርጫ ቀናት ማካሄድ እንዳይችል ማድረጋቸውን ተከትሎ የአጠቃላይ ምርጫው አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል። ከዚህ በተጨማሪም ቦርዱ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት መተከል እና ካማሺ ዞኖች እንዲሁም በአፋር ክልላዊ መንግሥትና በሶማሌ ክልላዊ መንግስት መካከል ግጭት በተፈጠረባቸው በአፋር ክልላዊ መንግስት አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ ቦታዎች መራጮችን መመዝገብና ሌሎች የምርጫ ዝግጅት ተግባራትን ማከናወን አልቻለም ነበር።

# በኢትዮጵያ ምርጫዎች ላይ የሲቪክ ማኅበረሰብ ተሳትፎ

የዜጎች የምርጫ ታዛቢነት መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች) ወይም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አማካኝነት የሚከናወን ተግባር ነው። የዜጎች የምርጫ ሂደቶችን የመታዘብ መብት ከዜጎች **የፖለቲካ ተሳትፎ የመሳተፍ መብት** ( ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ (UDHR) አንቀጽ 21 እና የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ዓለም አቀፍ የቃል ኪዳን ሰነድ (ICCPR) አንቀጽ 25) የመነጨ ነው።[4] በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በቀዳሚዎቹ ምርጫዎች በምርጫ ታዛቢነት፣ በሲቪክና የመራጭ ትምህርቶችን በመስጠት ሥራዎች ላይ ተሳትፈዋል። በአምስት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህብረት የተመሰረተው Ad-Net/E95 በ1987 ዓ.ም በተካሄደው ጠቅላላ ምርጫ ወቅት የምርጫ ትዝብት እንዲሁም የመራጮች ትምህርት ሥራዎችን አከናውኗል። የህብረቱ አባላት ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ (IAG)፣ አቡጊዳ (ABUGIDA)፣ አክሽን የባለሙያዎች ማኅበር ለሕዝብ (Action Professionals Association for the People /APAP)፣ የሰላምና ልማት ጊዜያዊ ኮሚቴ እና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ነበሩ። ህብረቱ የተቋቋመበት ግብ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾችን ማንቀሳቀስ እና ዜጎችን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ስላሏቸው መብቶችና ኃላፊነቶች በተመለከተ ማስተማር ነው።[5] በተመሳሳይ እንደ የሥነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት ማኅበር (CVEA)፣ የዴሞክራሲ ምክር ቤት እና የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ኅብረት ጉባዔ (CDHRA) የመሳሰሉ ድርጅቶች በቀደምት ምርጫዎች ላይ ከምርጫ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ባለው ሥራዎች ላይ ተሳትፈዋል።[6] ምንም እንኳን ያደረጉት ጥረት እና ዝግጅት በቀድሞው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በተላለፈው ውሳኔ እና በተከተለው የህግ ክርክር ቢስተጓጎልም «ከግንቦት 15 የምርጫ ቀኑ በፊት ከ3,000 በላይ ታዛቢዎችን ለማሠማራት ዕቅደው የነበሩት ወደ 30 በሚጠጉ የአገር ውስጥ ድርጅቶች»[7] ነበሩ።

በስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ በጠቅላላው 36[8] የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በምርጫ ታዛቢነት እንዲሳተፉ በምርጫ ቦርድ ዕውቅና የተሰጣቸው ሲሆን 155[9] የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሲቪክና የመራጭ ትምህርትን ለመስጠት ዕውቅና አግኝተዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ከአቅም ማነስ፣ ከገንዘብ ድጋፍ እጥረትና ሌሎች ምክንያቶች ጋር ተያይዘው ባጋጠሙት የተለያዩ ተግዳሮቶች የተነሳ በምርጫ ታዛቢነቱ ላይ በንቃት የተሳተፉት በቁጥር ውሱን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ነበሩ። በስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ወቅት ከየኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ / CECOE) በተጨማሪ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA)፣ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበራት ፌደሬሽን (FEAPD)፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) እና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) በሰኔ 2013 ዓ.ም በተካሄዱት ጠቅላላ ምርጫዎች ላይ ታዛቢዎችን[10] በማሠማራት በምርጫ መታዘብ ሥራዎች ላይ በንቃት ክተሳተፉ ድርጅቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። ከአገር ውስጥ ታዛቢ ቡድኖች በተጨማሪ የአፍሪካ ኅብረት የዓለም አቀፍ ታዛቢነት ተልዕኮም ምርጫውን ታዝቧል። ከዚህ በተጨማሪም ምርጫውን ከመታዘብ ጋር በተያያዘ እንደ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊክ ኢንስቲትዩት - ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (IRI - NDI) የመሳሰሉ በቁጥር ውሱን የውጭ ታዛቢ ቡድኖች ውስን የትዝብት ስራን አከናውነዋል።[11]

4 የ ACE የምርጫ ትዝብት www.aceproject.org/ace-en/topics/eo/eo1/what-is-citizen-observation/default

5 Jeffrey Clark (2000) Civil Society, NGOs, and Development in Ethiopia A Snapshot View P.10

6 UPDATED MAPPING STUDY OF NON STATE ACTORS IN ETHIOPIA bit.ly/3r2nSXz, P.135

7 OBSERVING THE 2005 ETHIOPIA NATIONAL ELECTIONS CARTER CENTER FINAL REPORT December 2009. bit.ly/3H5ZidR P.19

8 በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ምርጫን ለመታዘብ የተፈቀደላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር bit.ly/348W5Me

9 በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የሲቪክ እና የመራጮች ትምህርት እንዲሰጡ ፈቃድ የተሰጣቸው የሲቭል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር bit.ly/3r2odJP

10 ETHIOPIA JUNE 21, 2021 NATIONAL ELECTIONS REPORT bit.ly/3AB7qAx

11 Joint NDI/IRI Limited Election Observation Mission for Ethiopia Report on the June 21, 2021 National Elections bit.ly/3fVgWFo




“የተከበሩ ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ፣ የአፍሪካ የምርጫ ትዝብት ተልዕኮ ቡድን መሪ፣ የCECOEን የምርጫ ትዝብት ሪፖርት ማስተባበሪያ ማዕካል በምርጫው እለት በመጎብኘት ላይ

# ምዕራፍ ፪፡ ስድስተኛው የኢትዮጵያ አገር አቀፍ ምርጫ፡ የምርጫ ደንቦች ጠቅላላ ምልከታ

የምርጫወችወን ሂደቶች ለማስታዳደር የሚወጡ ህጎች በየትኛውም ሁኔታ የሚካሄዱ ምርጫወችን ጥራት ለመገምገም ወሳኝ መለክያወች ናችው። ይህ የሪፖርቱ ክፍል በኢትዮጵያ የተካሄደውን ስድስተኛውን አገር አቀፍና የክልል ምርጫወችን እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የተካህደውን ሕዝብ ውሳኔ ለማስፈጸም የወጡ ህጎችን ይዳስሳል። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ምዕራፍ በመንግሰት የተወሰዱ እንደ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን መልሶ ለማደራጀት አንዲሁም፤ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የሚተዳሩበት ህግ እና በመሳሰሉ ህጎች ላይ የተደረጉ ዋና ዋና የሕግ ማሻሻያወች በመጠኑ ይዳስሳልሳል።

## የ1987ቱ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት

በአገሪቱ የሕገ መንግሥት ታሪክ አራተኛው ሕገ መንግሥት የሆነው የ1987 ዓ.ም የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ከ15 ነሐሴ 1987 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ውሏል። ሕገ መንግሥቱ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ (የ2013 ዓ.ም ስድስተኛውን ምርጫን ጨምሮ) በኢትዮጵያ ስድስት አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች፣ ሁለት የአካባቢ ምርጫዎች እና ሰባት ሕዝበ ውሳኔዎች ተካሂደዋል። የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 38 «ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት»[12] በማለት የሁሉንም ኢትዮጵያውያን የመምረጥና የመመረጥ መብት ያረጋግጣል። ይሄው ተመሳሳይ ድንጋጌ የሁሉንም ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሠራተኛ ማኅበራት፣ የንግድ ድርጅቶች እና የሌሎች ቡድኖች አባል የመሆን መብትን ያረጋግጣል። ሕገ መንግሥቱ በተጨማሪም ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ[13] የሚቋቋምበትን ሁኔታ ይደነግጋል። በተጨማሪም ሕገ መንግሥቱ ከምርጫ ጋር የተያያዙ እና አግባብነት ያላቸውን ዋና ዋና የፖለቲካ መብቶች ይደነግጋል።[14]

በፅደቀበት ወቅት ዘጠኝ ክልላዊ መንግስታትን ያቋቋመው[15]፣ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በተጠቀሱት ክልላዊ መንግሥታት ውስጥ የሚገኙት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከሕገ መንግሥቱ መፅደቅ በኋላ በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት እንዳላቸው ዕውቅና ይሰጣል።[16] ድንጋጌውም ሆነ አዋጅ ቁጥር 251/1993[17] አንቀጽ 19 ይህ መብት እውን ይሆን ዘንድ የሚመለከተው የክልል ምክር ቤት ሁለት ሦስተኛ አብላጫ ድምፅ መስጠት እንዳለበት ይደነግጋሉ። ይህ መስፈርት በተሟላ ጊዜ ሁሉ ጥያቄው ለፌደሬሽን ምክር ቤት ከቀረበ በኋላ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጥያቄው ላይ ሕዝበ ውሳኔ መሰጠት እንዳለበት ተደንግጓል። ሕዝበ ውሳኔው የአብላጫውን ድጋፍ ካገኘ አዲስ የክልል አስተዳደር ለማቋቋም የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያገኛል። ከ2011 ዓ.ም አንስቶ ይህ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ በተደጋጋሚ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን በ2011 ዓ.ም የተካሄደው የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ አንዲሁም በቅርቡ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም የተካሄደውን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕዝበ ውሳኔ ምርጫዎች ይህ ሕገ መንግሥታዊ ሥነ ሥርዓት በአግባቡ ጥቅም ላይ የዋለባቸው የቅርብ ጊዜ ምሳሌዎች ሲሆኑ ሁለቱም የህዝበ ውሳኔወች አዳዲስ ክልሎች እንዲፈጠሩ አሰችለዋል።

## አዋጅ ቁጥር 1133/2011

ስድስተኛውን የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫ ልዩ ከሚያደርጉት ባሕሪያት መካከል ከምርጫው በፊት የተከናወነው የህግ የማሻሻያ ሂደቶች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የማሻሻያ ሂደቶች እውን የተደረጉት በመጋቢት 2010 ዓ.ም የጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ አስተዳደር ወደ ፖለቲካዊ ሥልጣን ከመጣ ወዲህ ሲሆን ይህን ተከትሎ በነበሩት ግዜያት የተለያዩ የፖለቲካ እስረኞች በስፋት ከእሥር ከመፈታታቸው እና በስደት የሚገኙ በቀዳሚው የአገዛዝ ዘመን ወደ ውጭ አገር ተሰደው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ወደ አገር ከመመለስ

12 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አዋጅ ቁጥር 1 1987፣ ኅዳር 1987 ላይ የወጣ እና ነሐሴ 15 ቀን 1987 በሥራ ላይ የዋለ፣ አንቀጽ 38

13 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 102

14 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 29 (የአመለካከት እና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት)፣ አንቀጽ 30 ( የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ - የማቅረብ መብት) እና አንቀጽ 31 (የመደራጀት መብት)

15 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 47

16 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 47 (2)

17 6 አዋጅ ቁጥር 251/1993 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣ አዋጅ፣ አንቀጽ 19(1)

ጋር ተያይዞ በፖለቲካ ምህዳሩ ላይ እጅግ ወሳኝ የሆኑ ለወጦች ተደርገው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በ2010 ዓ.ም በጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ ሥር የተቋቋመው የኢትዮጵያ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች አማካሪ ምክር ቤት በምርጫ ሕጉና እና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እነ ማህበራት አዋጅ ላይ ዋና ዋና ማሻሻያ ማድረግ ያስቻለ ሲሆን ይህም በስድስተኛው የኢትዮጵያ አጠቃላይ አገር አቀፍና የክልል ምክር ቤት ምርጫ ላይ ከፍተኛ እንድምታን አስከትሏል።

ከስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ በፊት ምምርጫወችን ያካሂድ የነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከተቋማዊ ነጻነት እና ፖለቲካዊ ገለልተኝት አንፃር ጥያቄዎች ይነሱበት ነበር። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው በ1986 ዓ.ም ሲሆን ይህ የማቋቋሚያ አዋጅ በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አስተዳደር ተሻሽሎ በአዋጅ ቁጥር 1133/2019 ጸድቋል። አዋጁ የምርጫ ቦርድ መዋቅርን፣ ኃላፊነትና ስብጥርን በማሻሻል የበለጠ የፋይናንስና ተቋማዊ ነጻነት ያለው ተቋም እንዲሆን አስችሎታል።እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ምርጫ ቦርድን የሚያቋቁሙ ድነጋጌወች የምርጫ አዋጁ አካል የነበሩ ሲሆን በተሻሻለው አዋጅ ግን ቦርዱ ራሱን የቻለ አካል ሆኖ መቋቋሙ በኢትዮጵያ ምርጫን በሚያሰተዳድረው የሕግ ማዕቀፍ አኳያ ትልቅ እድገት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። በአጠቃላይ የተደረገው ማሻሻያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን ተገቢው ሥልጣን ያለው፤ እራሱን የቻለና ጠንካራ ተቋም እንዲሆን አድርጎታል። ከቀድሞው አዋጅ ጋር ሲነጻጸርም የተሻሻለው አዋጅ ቦርዱ በበጀት ላይ ቁጥጥር እንዲኖረው ማሰቻልን፤ በጀት አዘጋጅቶ በቀጥታ ለፓርላማ ማቀረብና ማስጸደቅን በማካተት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንን ገድቧል። በሰው ሃይል ቅጥር ረገድም ቦርዱ አስፈላጊ የሆኑ በቂ ሰራተኞችን ያለመንግስት ጣልቃ ገብነት መልምሎ የመቅጠር የተሻለ ነጣነትን አዋጁ አቀዳጅቶታል።

# አዋጅ ቁጥር 1162/2011

በ2013 ዓም ከተካሄደው ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የሥነ ምግባር ደንብ አዋጅ መውጣት ከተገኙ ጠቃሚ የህግ ማሻሻያ ውጤቶች መካከል አንዱ ነው። አዋጁ በኢትዮጵያ የተለያዩ የምርጫ አይነቶችን፣ የምርጫ ሥርዓቱን፣ የምርጫ አሰተዳደሩ አረከኖችን፣ የምርጫ ሥነ ምግባርን ፣ የመራጮችና የዕጩዎች ምዝገባን፣ የምርጫ ቅስቀሳን፣ የቅሬታ አሰማማም ስርአቱን፣ የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደትን እንዲሁም የውጤት አገላላለፅን የሚመለከቱ በርካታ ጉዳዮችን የያዙ ጠቃሚ ድንጋጌወችን አካትቷል። ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመሠረቱባቸው፣ የሚዋሀዱባቸው፣ የሚተኩባቸው፣ የሚመዘገቡባቸውን እና የሚፈርሱበትን መንገዶች እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችና አባላቶቻቸው ያሏቸውነ መብቶችና ግዴታዎች በዝርዝር ይደነግጋል። ከዚህ በተጨማሪ በአዋጁ ክፍል 5 ሥር ታዛቢ ቡድኖች ጋዜጠኞች እና በምርጫ ሂደቱ ላይ ክተትል ማደረግ የሚፈልጉ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በምርጫው ሂደት ላይ ለመሳተፍ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሕጎችን በግልጽ ይደነግጋል። አዋጁ ስራ ላይ መዋል የጀመረው ከ ጥቅምት 6/ 2013 ዓ.ምጀምሮ ነው።

# ሌሎች የምርጫ ሕጎች

ከምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ እና ከምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የሥነ ምግባር ደንብ አዋጆች በተጨማሪ የምርጫ ቦርድ ስድስተኛውን የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫወች ለማካሄድ የተለያዩ ደንቦችን አውጥቷል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የቦርዱ ክልላዊ ፅህፈት ቤቶች ቢሮዎች አወቃቀር እና ንስብጥርን፣ ለሀገር ውስጥና ለዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ስለሚሰጥ እውቅና፣ ለጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ስለሚሰጥ ዕውቅና አሰጣጥን፣ ስለየቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አወቃቀርና የአሰራር ሥነ ሥርዓት ሕጎችን፣ ስለየልዩ ምዝገባና የድምፅ አሰጣጥሥነ ሥርዓት፣ የምርጫ ቅስቀሳ ለፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ ማካሂጃ የሚፈቀድ የአየር ሰዓት እና የጋዜጣ ዓምዶችድ፣ ስለኮቪድ-19ን እና በምርጫ ሂደቱ የሚያጋጥሙ የደኅንነት ስጋቶችን ምደባን ጨምሮ ከምርጫ ጋር በተገኛኙ ለተያያዙ የተለያዩ ጉዳዮች ዙርያ 22 መመሪያዎችን እንዲሁም ኮቪድ-19ን እና በምርጫ ሂደቱ የሚያጋጥሙ የደኅንነት ስጋቶችን የተመለከቱ መመሪያዎችን ጥቅም ላይ አውሏል።

# የተሻሻለው የሲቪክል ማህበራት ድርጅቶች አዋጅ

ከ1997 ዓ.ም አጠቃላይ ምርጫ ቀጥሎ በስራ ላይ የዋለው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የሲቪል ማህበራትአዋጅ ቁ. 621/2001 የአገር በቀል ሲቪል ማህበራት ከምርጫ ጋር ተያይዞ የሚሰሩትን ስራ ለአስር አመት ለሚጠጋ ጊዜ ገመገደቡ ይታወቃል። የሲቪክ ማህባራት ድርጅቶች በዚህ አዋጅ ስር በተቋቋመው ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ከሚደርስባቸው ከፍተኛ ጫና በተጨማሪ የተለያዩ የፋይናንስና አስተዳደራዊ ተግዳሮቶች ተጭነውባቸው ነበር። በመጋቢት 3 2011 ዓ.ም ተሻሽሎ የጸደቀው የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች አዋጅ ቁ. 1113/2011 ከቀድሞው አዋጅ ጋር ሲነፃፀር የተለያዩ ለውጦችን አደርጓል። አዋጁ ሲቪክ ማህበራት ድርጅቶችን በአገር በቀል እና የውጭ አገር ድርጅቶች በማለት የሚከፍል ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች የተመሰረቱበትን አላማ ለማሳካት የሚረዷቸውን ስራዎች ያለምንም ገደብ መስራት እንደሚችሉ በግልፅ ይደነግጋል። በሌላ አነጋገር ከቀድሞው አዋጅ በተለየ የውጪ አገር ወይም በውጭ አገር ድርጅቶች የገንዘብ

ድጋፍ የሚደረግላቸው አገር በቀል ድርጅቶች በአድቮኬሲ እና ሰብዓዊ መብት ነክ ስራዎች ላይ መስራት የሚችሉበት የህግ ማዕቀፍ በዚህ አዋጅ ተካትቶ ይገኛል። አዲሱ ሕግ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች «ከሚያከናውኗቸው ሥራዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው» ሕጎችና ፖሊሲዎችን በተመለከተ የማግባባትና ተጽእኖ የመፍጠር ሥራዎችን እንዲሰሩ የሚያበረታታ ነው። ህብረቱ በዚህ አዋጅ ስር በተደረጉት ማሻሻያዎች ከተጠቀሙ ድርጅቶች አንዱ ሲሆን በአዋጁ ስር ያሉት የፋይናንስ፣ አስተዳደራዊና የቁጥጥር ማሻሻያዎች ባይኖሩ ህብረቱ በአገሪቱ አዲስ የሚባል የትዝብት ስራን ማከናወን ይቅርና ጨርሶ ላይመሰረት የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ እንደነበር ልብ ሊባል ይገባል።

ከ1997 ዓ.ም ምርጫ የተገኘውን ተሞክሮ ተከትሎ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የሲቪል ማህበራትአዋጅ ቁ. 621/2001 ወደ ዐሥር ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ የሲቪል ማህበራትድርጅቶችን የምርጫ ተሳትፎ ገድቦታል። የሲቪል ማህበራትድርጅቶች በተጠቀሰው አዋጅ የተቋቋመው ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ከፍተኛ ን ተጽእኖ ሥር ከመወደቁ በተጨማሪ የፋይናንስና አስተዳደራዊ ገደቦች ተጥለውባበቸው አነደነበር የሚጣወስ ነው። መጋቢት 3/ 2011 ዓ.ም የጸደቀው የሲቪል ማህበራትድርጅት አዋጅ ቁ. 1113/2011 በቀዳሚው አዋጅ አኳያ ሲታይ መሰረታዊ ለውጦችን አድርጓል። አዋጁ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን በአገር በቀል (የአገር ውስጥ) እና የውጭ አገር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ብቻ ይመድባቸዋል። አዋጁ በተጨማሪም ማናቸውም ድርጅቶች ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት በሚያስችል በየትኛውም ሕጋዊ ተግባር ላይ የመሠማራት መብት እንዳላቸው በግልጽ ይደነግጋል። በሌላ አነጋገር የውጭ አገርና በውጭ አገር የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በአድቮኬሲና የሰብአዊ መብቶች ሥራ ላይ ለመሠማራት አይከለከሉም። በርግጥም አዲሱ ሕግ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን «ከሚያከናውኗቸው ሥራዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው» ሕጎችና ፖሊሲዎችን በተመለከተ በማግባባትና ተጽእኖ መፍጠር ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታቸዋል። ሕብረት ለምርጫ (CECOE) የፋይናንስ፣ የአሠራርና ቁጥጥር ሕጎች ማሻሻያ ባይደረግባቸው ኖሮ መመሥረትም ሆነ ከስድስተኛው አገር አቀፍና የክልል ምርጫ ጎን ለጎን ፈር ቀዳጅ የሆነ የምርጫ ትዝብት ፕሮጀክቱን መተግበር የማይችል የነበረ በመሆኑ ምክንያት ከዚህ አዋጅ ተጠቃሚዎች መካከል አንደኛው ነው ማለት ይቻላል።

## ከስድስተኛው ምርጫ የምርጫ ደንቦች ጋር በተያያዘ የሕብረት ለምርጫ (CECOE) ምልከታዎች

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ ከስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ አስቀድሞ የተደረጉ የህግ ማሻሻያዎች በኢትዮጵያ ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ እንዲካሄድ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በምርጫ ሂደቱ ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ከማሳደግ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው ብሎ ያምናል። ነገር ግን ህብረቱ ከህጎች አተገባበር እና ከአሰራር ጉድለቶች አንፃር የተለያዩ ክፍተቶችን መታዘቡንነ እና እነዚህን ክፍተቶች ለማስተካከል በቀጣይ የምርጫ ሂደቶች ምርጫ ቦርድም ሆነ የሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ሊያስተካከሉ ይገባል ብሎ ያምናል። ከስድስተኛው የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫወች ጋር በተያያዘ ሊተኮርበት የሚገባው አንዱ ትልቅ ክፍተት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተለያዩ የምርጫ ጉዳዮች ላይ ያወጣቸውን መመርያዎች በአብዛኛው ቀደም ብሎ በቂ በሚባል ደረጃ አለማሰራጨቱ ህዘቡንም ሆነ በምርጫ ሂደቱ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላት በመመሪያወቹ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ውሱን እንዲሆን አድርጓል ብሎ ህብረቱ ያምናል።

ከላይ በገለጽናቸው አዋጆችና እና መመሪያዎች ሥር የተካተቱት የተወሰኑ ሕጎች ተግባር ላይ መዋል አለመቻልም ሌላኛው ተግዳሮት ነበር። ምንም እንኳን የተከናወነው የሕግ ማሻሻያ በመራጮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩዎች እና ገለልተኛ ዕጩዎች ምዝገባ ላይ አዳዲስ ድንጋጌዎችን ያወጣ ቢሆንም ቦርዱ በተጨባጭ እነዚህን ሕጎች ለመተግበር ተቸግሮ ነበር። እንደማሳያ መራጮችን ለመመዝገብ ለማስመዝገብ እማኞችን ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ግልጽ አሰራር አለመኖሩ፤ የመንግሥት ሠራተኞች በዕጩነት የሚቀርቡ ከሆነ ከኃላፊነታቸው መልቀቅ እንዳለባቸው በሚጠይቀው መስፈርት ዙሪያ፣ እንዲሁምና የእንደ ፓርቲና እና የግል ዕጩዎችን ለመመዝገብ ፊርማ ከመሰብሰብ ጋር በተያያዘ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሲተገበሩ በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ አሳሳቢ ችግሮች ነበሩ። ለምሳሌ፣ ምንም እንኳን ለአገር አቀፍ ፓርቲዎች 10,000 ፊርማዎች እና ለክልል ፓርቲዎች 4,000 ፊርማዎች ማሰባሰብ የምርጫ አዋጁ አንድ ድንጋጌ ክፍል ቢሆንም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኮቪድ-19 እና በተለያዩ ምክንያቶች ተጥለው ከነብሩ በየእንቅስቃሴ ገደቦች አማካኝነት ይህን ማሳካት እንደማይችሉ ማስታወቃቸውን ተከትሎ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፊርማ መስፈርቱን በማውረድ የመስፈርቱን 35 በመቶ ያሟሉ ፖለቲካ ፓርቲዎች መመዝገቡ እንደማሳያ ሊጠቀስ ይችላል። ላየመንግሥት ሠራተኞች ዕጩ ሆነው ለመመዝገብ ከሥራቸው ጊዜያዊ የማይከፈልበት ዕረፍት መውሰድ አለባቸው የሚለው ሕግ የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት ግልጽነት ማጣትም ለሌላኛው ልብ ሊባል የሚገባው ክፍተት ነው።



“ሕብረት ለምርጫ ያሰማራቸው ታዛቢዎች፣ በቆሎጂ
የስደተኞች ምርጫ ጣቢያ በትዝብት ላይ ሆነው”

# ምዕራፍ ፫፡ የምርጫ ቅሬታዎች አሰማም እና የአለመግባባት አፈታት ሥርዓት

## የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቅሬታ አሰማም ሥነ ሥርዓቶች

በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና ምርጫዎች የሥነ ምግባር ደንብ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 7 (11) ሥር በምርጫ ሂደቱ የተለያዩ ደረጃዎች ሊከሰቱ የሚችሉ ቅሬታዎችን ለማስተናገድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ  በምርጫ ሂደት ወቅት በተለያዩ ደረጃዎች የሚነሡ የምርጫ ቅሬታዎችን ለመፍታት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን (GHCs) በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች፣ የምርጫ ክልሎች፣ ክልልና አገር አቀፍ ደረጃዎች የማቋቋም ሥልጣን እንዳለው በግልጽ ተደንግጓል። በተጨማሪም በድምፅ መስጫ ጣቢያ፣ በየምርጫ ክልል እና በክልል ደረጃዎች የሚቋቋሙት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አባላት አመራረጥ ስርዓት ስብጥር በተጨማሪም በበምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ማቋቋሚያና የሥነ ሥርዓት መመሪያ ከአንቀጽ 7 እስከ 11 ተደንግጓል።

ከላይ የተጠቀሰው መመርያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ከማዋቀር በተጨማሪ እንደቅሬታው ይዘት በየትኛው የቅሬታ አሰማም እርከን ቅሬታዎች መቅረብ እንዳለባቸው የሚደነግጉ የስነ ስርዓት እና የዳኝነት ስልጣን አንቀፆችን ያካተተ ነው። እንደምሳሌ ለማንሳት መመርያው ከመራጮች ምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች በምዝገባ ጣቢያ በሚዋቀሩ ኮሚቴዎች እንዲስተናገዱ የሚደነግግ ሲሆን በውሳኔው ቅሬታ ያለው አካል የይግባኝ ጥያቄውን በምርጫ ክልልና በክልል ፅ/ቤት ደረጃ ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል። በአንፃሩ የቅሬታው ይዘት ከእጩዎች ምዝገባ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ ቅሬታ አቅራቢዎች አቤቱታቸውን በምርጫ ክልል ደረጃ ማቅረብ እንደሚገባቸው የሚደነግግ ሲሆን በምርጫ ክልሉ ውሳኔ ቅሬታ ያለበት አካል በክልልና በብሔራዊ ደረጃዎች በሚገኙ ኮሚቴዎች ይግባኝ መጠየቅ እንደሚችል መመርያው አስቀምጧል። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በድምፅ መስጫ ቀን  በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ እንደሚመሰረቱ የምርጫ ህጉ የሚደነግግ ሲሆን እነዚህ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች መራጮች እና እጩ ተወዳዳሪዎች በድምፅ አሰጣጥ ወይም አቆጣጠር ወቅት ያሏቸውን ቅሬታዎችን በወቅቱ እንዲያቀርቡ ያስችላሉ።

## በመራጮች ምዝገባ ወቅት የቀረቡ ቅሬታዎች

በ6ኛው አጠቃላይ ጠቅላላ ምርጫ ወቅት ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ  በሱማሌ ክልል የነበረው የምርጫ ምዝገባ ሂደት ከፍተኛው የቅሬታዎች ብዛት የተመዘገበበት ክልል ነበር። በክልሉ የተወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች (ኦብነግ፣ ነጻነትና እኩልነት፣ ኢዜማ፣ እና ሌሎች የግል ተወዳዳሪዎች) የምዝገባ ሂደቱ ወጥነት የጎደለው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በድምፅ-ምስል ቅጂዎች አስደግፊው ቅሬታዎችን ለቦርዱ ያስመዘገቡ ሲሆን እነዚህም ማስረጃዎች በማኅበራዊ ትስስር ገጾች ላይ ተሠራጭተው እንደነበር የሚታወስ ነው። ብሔራዊ የምርጫ ቦርዱ ከላይ ይተጠቀሱትን በማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ የተዘዋወሩ ምስሎች በሚድያ ዳሰሳ ቡድኑ (Media Monitoring Unit) አማካኝነት ማግኘቱን ተከትሎ በክልሉ በሚገኙ አብዛኛዎቹ የምርጫ ክልሎች ውስጥ የተከናወኑ የመራጮች ምዝገባ ሂደቶችን የሚያጣራ ቡድን ወደክልሉ አሰማርቶ ነበር።  ቦርዱ በተጨማሪም ይህን በማኅበራዊ ትስስር ገጽ ላይ የተሠራጨውን መረጃ በክልሉ ውስጥ በተካሄዱት በአብዛኞቹ ምዝገባዎች ላይ ምርመራ ለማካሄድ በሚዲያ ተቆጣጣሪ ክፍሉ በኩል ተቀባይነት አግኝቷል።

በክልሉ የተነሱት አብዛኞቹ ቅሬታዎች የገዥው ፓርቲ ባለሥልጣናት የመራጮችን ምዝገባ ለማሳሳት ጣልቃ ከመግባታቸው፣ ያልተሞሉ የምዝገባ ካርዶችን በቀበሌ ደረጃ ላሉ ኃላፊዎች ከመሠራጨታቸው፣ የተፎካካሪ ፓርቲ ደጋፊ እንደሆኑ የታመነባቸውን መራጮች እንዳይመዘገቡ በመከልከል የመምረጥ መብታቸውን ከመገደቡ እና የምርጫ  አስፈፃሚዎች በክልሉ የመንግስት መዋቅር ውስጥ የሚሰሩ ግለሰቦች ከመሆናቸው ጋር የተያያዙ ነ ናቸው። ቦርዱ ምርመራ ካካሄደ በኋላ በምዝገባ ወቅት ያጋጠሙ ህጸጾች ለውሳኔው ዋነኛ ምክንያት መሆናቸውን በመጥቀስ የሱማሌ ክልላዊ መንግሥት የሰኔው ምርጫ እንዳይከናወን በማገድ ውሳኔ አሳልፏል።

# በምርጫ ቀን የቀረቡ ቅሬታዎች

ከድምፅ አሰጣጥ እነ ቆጠራ ሂደቶች ወሳኝነት እና አከራካሪነት አንፃር በአብዛኞቹ በአለም ላይ በሚከናወኑ ምርጫዎች ላይ የምርጫ ቀን ቅሬታዎች  በከፍተኛ ቁጥር የሚቀርቡበት ወቅት ነው። ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ የተከናወነባቸውን የሰኔና የመስከረም የምርጫ ቀናት ተከትሎም የተለያዩ ቅሬታዎች ቀርበው ነበር። ህብረቱ ከምርጫ ቦርድ የህግ ክፍል ያገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የሰኔውን ምርጫ ተከትሎ 31 የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ስድስት የግል ዕጩዎች በ ስድሰት የምርጫ ክልሎች ላይ በጋራ ቅሬታዎችን ያቀረቡ ሲሆን በመስከረም ወር ደግሞ ስድስት ፓርቲዎች እና 24 የግል ተወዳዳሪዎች በ25 የምርጫ ክልሎች ላይ ቅሬታ አቅርበዋል።  ነገር ግን ብሀሔራዎ የምርጫ ቦርድ ከላይ የተቀመጠውን የቅሬታ አሰማም እርከን ወደጎን በመተው በተለይም በሰኔ ወር የቀረቡ ቅሬታዎችን በአንድ ላይ በብሔራዊ ደረጃ እንዳየ የሚታወስ ሲሆን ስለውሳኔውና ስላስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ በዚህ ሪፖርት የድህረ ምርጫ ግኝቶች ክፍል ህብረቱ ማብራሪያ አስቀምጧል። ከላይ ከተጠቀሱት ቅሬታዎች መካከል በወላይታ ዞን በሰኔ ወር የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ በዞኑ በተወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የቀረበውን ጥምር ቅሬታ ከታች በአጭሩ ተብራርቷል።

በሰኔ 14 ቀን 2013 በወላይታ ዞን  በስድስት የምርጫ ክልሎች እና በ 467 የምርጫ ጣቢያዎች ምርጫ ተካሂዷል። በእነዚህ የምርጫ ክልሎች እና የምርጫ ጣቢያዎች የተወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በድምፅ መሰጫ  ቀን በድምፅ አሰጣጥና በምርጫ ሂደቱ ላይ ስለተፈፀሙ ከባድ ጥሰቶች በጋራ ባቀረቡት ቅሬታ ቦርዱ የምረጫው ውጤት እንዲታገድ ወስኗል። በመሆኑም በወላይታ ዞን ውስጥ 467 የምርጫ ጣቢያዎችን ያካተቱ እነዚህ ስድስት የምርጫ ክልሎች በመስከረም 2021 ምርጫ ሊካሄድባቸው አቅድ ተይዞላቸው  ከነበሩ  የምርጫ ክልሎች ዝርዝር ውስጥ ተካተው ከሶማሊ እና ሀረሪ እንዲሁም በደቡብ ክልል ከተደረጉ የማሚያ፣ የድጋሙ እንዲሁም የህዝበ ውሳኔ ምርጫዎች ጋር በመስከረም 20፣ 2013 ዓ.ም ምርጫው በእነዚህ ምርጫ ክልሎች ተከናውኗል።

# ለፌዴራልና ለክልል ፍርድ ቤቶች የቀረቡ የምርጫ ቅሬታዎች

የምርጫ ቦርድ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ከምርጫ ሂደቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት የመጨረሻ  አካለት አይደሉም። የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች በምርጫ ቦርድ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ አቤቱታ ያላቸውን አካላት ይግባኝ የመስማት ስልጣን አላቸው። ይግባኝ እንደሚጠየቅበት ቅሬታ ይዘት በፌደራል እና ክልል ፍርድ ቤቶች ለምርጫ ጉዳዮች የተቋቋሙ ችሎቶች በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተሰጡ ውሳኔዎችን የመመልከት ስልጣን አላቸው። ለምሳሌ ከመራጮች ምዝገባ ጋር በቀረቡ ቅሬታዎች ዙሪያ የክልልና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የይግባኝ ጥያቄዎችን የሚያስተናግዱ ሲሆን ከእጩዎች ምዝገባ ጋር በበተያያዙ ቅሬታዎች ዙሪያ በክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በቀረበበት ጉዳይ ላይ አቤቱታ ያለው አካል በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ይግባኝ መጠየቅ እንደሚችል ተደንግጓል። በተጨማሪም በቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ ዙሪያ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ደረጃ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደረጃ አቤቱታ ማሰማት እንደሚችል ማስታወስ ያስፈልጋል።

በስድስተኛው የኢትዮጵያ ምርጫ አውድ የክልል መንግስታት እና ፓርቲዎች በቅድመ ምርጫ እና በድህረ ምርጫ ወቅት ከላይ የተጠቀሱትን ስርዓቶች በመጠቀም የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ክሶችንክሶችን ያቀረቡ ሲሆን የተለያዩ ፍ/ቤቶች አዳዲስ የህግ ጉዳዮች ላይ ወሳኔዎችን ሲሰጡ ታይተዋል። ይህ አበረታች የምርጫው ገፅታ ሆኖ ሊወሰድ ቢችልም በተለይም በድህረ ምርጫ ወቅት ከይግባኝ መጠየቅያ ጊዜ ገደብ አለማክበር ጋር በተያያዘ ብዙ አቤቱታዎች ይዘታቸው በፍርድ ቤት ሳይታይ ውድቅ መደረጉ እንደተግዳሮት መጠቀስ ይችላል። ይህን የፍርድ ቤቶች የተሻለ ተሳትፎ ለማሳየት ሲባል በቀጣዩ የሪፖርቱ ክፍል በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ እና በባልደራስ የታሰሩ አባላት እንደእጩ መቅረብ ዙሪያ በቀረቡ ክሶች ላይ የተሰጡ ውሳኔዎች ላይ አጭር ማብራሪያ ተቀምጧል።

## ሀ) የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ

ከስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ አስቀድሞ ከሌሎች ክልሎች በተለየ መልኩ የሐረሪ ክልላዊ መንግስት ሁለት ክልላዊ ም/ቤቶች ነበሩት። እነዚህ ሁለት ም/ቤቶች 22 መቀመጫዎች ያሉት የሐረሪ ክልል ህዝቦች ም/ቤት እና 14 መቀመጫዎችን የያዘው እና ለሐረር ብሔር ተወላጆች ብቻ ክፍት የሆነው የሐረሪ ብሔራዊ ም/ቤት ናቸው። ከዚህ ቀደም በተከናወኑ ምርጫዎች በክልሉ የተደረጉ ምርጫዎች በዚህ መልኩ የተከናወኝ ሲሆኑ ምንም እንኳን በምርጫ ህጉ አንድ መራጭ ድምፅ

ለመስጠት በአንድ አካባቢ ቢያንስ ለስድስት ወራት መኖር እንደሚጠበቅበት ቢደነግግም በ1987 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የወሰነውን ውሳኔ ተከትሎ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚኖሩ የሐረር ብሔር ተወላጆች ከዚህ ቀደም በተከናወኑ ምርጫዎች ለብሔራዊ ጉባኤው በያሉበት ቦታ ድምፃቸውን ሲሰጡ ቆይተዋል። ከላይ የተጠቀሰው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ውሳኔ በሐረሪ ክልል ህገ መንግስት አንቀፅ 50 ስር የተደነገገ ሲሆን ህገ መንግስቱ ጉባኤው የሐረር ብሔር ተወላጆችን ባህል እና ማንነት የማስጠበቅ ሀላፊነት እንዳለው ያስረዳል።
ከዚህ አሰራር ጋር በተያያዘ በሚያዚያ 08፣ 2013 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይህን አሰራር እንደማቀበል ያስታወቀ ሲሆን ከክልሉ ውጪ የሚኖሩ የሐረር ብሔር ተወላጆች በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ወቅት ድምፃቸውን ለጉባኤው ተመራጮች መስጠት እንደማይችሉ ገልፆ ነበር። ይህንንም ተከትሎ በምርጫ ዙርያ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች የመጨረሻው እርከን ለሆነው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የክልሉ ም/ቤት ክሱን አቅርቦ የምርጫ ቦርድን ውሳኔ መከራከሩ የሚታወቅ ነው። ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የቀረበውን ክስ በመመልከት በሚያዝያ 27፣ 2013 ዓ.ም የምርጫ ቦርድን ውሳኔ በመቀልበስ ከክልሉ ውጪ የሚኖሩ የሐረሪ ብሔር ተወላጆች የብሔራዊ ጉባኤውን አባላት እንዲመርጡ በህዝበ ተወካዮች ም/ቤት የተሰጣቸውን መብት የሚያስቀጥል ውሳኔ አሳልፏል። ይህንን ውሳኔ ተከትሎም ብሔራዊ የምርጫ ቦርዱ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት አለ በማለት ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኝ የጠየቀ ሲሆን በግንቦት 26፣ 2013 ዓ.ም ሰበር ሰሚ ችሎቱ ባስተላለፈው ውሳኔ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ያሳለፈውን ውሳኔ በማፅናት በክልሉ የማይኖሩ የሐረሪ ብሔር ተወላጆች 14 መቀመጫ ላለው ብሔራዊ ጉባኤ ድምፃቸውን መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ችግር የለበትም ሲል የቦርዱን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል። ይህን ውሳኔ ተከትሎ የክልሉ መስተዳደር የፍርድ አፈፃፀም ክስ የከፈተ ሲሆን ፍ/ቤቱ ውሳኔው መፈፀም አለመፈፀሙን ለማረጋገጥ ለሰኔ 7፣ 2013 ዓ.ም ቀጠሮ ይዞ ጉዳዩን መደምደሙ ይታወሳል። ብሔራዊ የምርጫ ቦርዱ የፍ/ቤቱን ውሳኔ የተቀበለ ሲሆን በመስከረም 20 ዓ.ም በተከናወነው ምርጫ ወቅት በሐረር፣ ድሬ ዳዋ፣ አዳማ እና አዲስ አበባ በመሰረታቸው የምርጫ ጣቢያዎች አሰራሩን ተፈፃሚ አድርጓል።

እንደዚህ ያሉ የፍርድ ቤት ጉዳዮች ካላቸው ጉልህ ጥቅም ጋር በተያያዘ ህብረቱ ክልሎች በዚህ መልኩ የፍትህ ስርዓቱን መጠቀማቸው ፍ/ቤቶች በሌሎች የመንግስት አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ከህግ አንፃር የማየት (check and balance) አቅማቸውን ያሳየ ጉዳይ እንደሆነ ያምናል። ይህ እንዳለ ሆኖ በአንፃሩ በምርጫ ቦርዱና በክልላዊ መንግስቱ መካከል የተደረገው ክርክር በሐረሪ ክልል ምርጫው በሰኔ ወር እንዳይከናወን የራሱን አስተዋፅኦ ያደረገ ሲሆን ይህም ምናልባት ቦርዱ ይህን አሰራር ቀደም ብሎ ለማስተካከል ጥረት ቢያደርግ ይህ ላይፈጠር እንደሚችል ህብረቱ ያምናል። ነገር ግን ምንም እንኳን ከክልሉ ጋር በነበረው ክስ ምክንያት ምርጫው በሰኔ ወር ባይከናወንም ከውሳኔው አስቀድሞ የምርጫ ቦርድ መራጮችን በክልሉ መዝግቦ እንደነበር የሚታወስ ነው። በተመሳሳይ የአፋርንና ሶማሊ ክልሎችን አዋሳኝ አካባቢዎች ከሚገኙ 8 ወረዳዎች ጋር በተያያዘ ወረዳዎቹ በሶማሊ ክልል ስር መካተታቸው ልክ አይደለም በማለት የአፋር ክልል መስተዳድር በሚድያ ያቀረበውን ቅሬታ ተከትሎ ምርጫ ቦርድ ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ በወረዳዎቹ ምርጫ እንደማይከናወን ማሳወቁ ይታወሳል።

## ለ) ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ እና እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ[18]

በምርጫው ሂደት የዳኝነት ሰርአቱን ጥቅም ላይ በማዋል ጉዳያቸውን በፍርድ ቤት የተከራከሩት ክልላዊ መንግስታት ብቻ አልነበሩም። ቦርዱ ተገቢውን እርምጃ በመውሰዱ ወይም ባለመውሰዱ ምክንያት የሥነ ሥርዓት ጉድለቶች ተፈጽመዋል ብለው ያመኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ላይ አቤቱታቸውን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ቦርዱን መርታት የቻሉባቸው አጋጣሚዎችም ተጠቃሽ ናቸው። ምንም እንኳ የተለያዩ እና ብዛት ያላቸው ቅሬታዎች ለቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲዎች አማካኝነት ቀርበው የነበር ቢሆንም ህብረቱ የባልድራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በፍርደ ቤት ባደረገው ክርክር ዙሪያ የተስተዋሉ አንዳንድ ጉዳዮችን ከዚህ ቀጥሎ ያብራራል።

በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ወቅት ከተስተዋሉ ወሳኝ የሕግ ጉዳዮች መካከል አንዱ አንዱ የሆነው በባልድራስ ፓርቲ እና በብሔራዊ ምርጫ መካከል የተደረገው ክርክር ሲሆን፣ ፓርቲው የምርጫ ቦርዱን በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ የምርጫ ጉዳዮች ሰሚ ችሎት ቢረታም በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመከራከር ማሸነፍ ችሏል። ይህ ጉዳይ የፓርቲው ሊቀ መንበር እስክንድር ነጋን ጨምሮ አራት በእስር ላይ የነበሩ የፓርቲው ከፍተኛ አባላት (በሽብርተኝነት እና ሌሎች ክሶች ምክንያት በእስር ላይ የነበሩት የፓርቲው አባላት ስንታየሁ ቸኮል፣ አስቴር ስዩም እና አስካለ ደምሌ ናቸው[19]) በምርጫው ላይ በእጩነት መሳተፍ አለመሳተፋቸውን የተመለከተ ነበር። ብሔራዊ ምርጫ

18 የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር ሰሚ ችሎት፣ የመዝገብ ቁጥር 207000

19 በታህሳስኅሣሥ 29 ቀን 2014 ዓ.ም የፍትሕ ሚኒስቴር በባልደራስ ፓርቲ መሥራቶችና መሪዎች እንዲሁም በሌሎች የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) አንጋፋ ተቃዋሚ መሪዎች ላይ የመሠረተውን ክስ ለውጤታማ አገር አቀፍ የምክክር መድረክ ሲባል ክሱን ማቋረጡን አሳውቋል።

ቦርድ እነዚህን በእስር ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በዕጩነት ላለመመዝገብ መወሰኑን ተከትሎ በመጋቢት 12 2013 ዓ.ም ፓርቲው ጉዳዩን ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የወሰደው ሲሆን በሚያዚያ 6 ቀን፣ 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦርዱን ውሳኔ አፀንቶ የፓርቲውን አቤቱታ ውድቅ አድርጎት ነበር። ይህን ውሳኔ ተከትሎ ፓርቲው ጉዳዩን ወደ ፌደራልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመውሰድ ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱ በግንቦት 24፣ 2013 ዓ.ም የምርጫ ቦርዱንና የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር የተጠቀሱት የፓርቲው ተወካዮች በሰኔ ወር 2013 ለሚካሄደው ምርጫ በእጩነት እንዲመዘገቡ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ትዕዛዝ ሰጥቷል። የምርጫ ቦርዱ የተለያዩ ምክንያቶችን በማስቀመጥ ውሳኔውን መተግበር ከፍተኛ ወጪ እንደሚያስወጣው (በየድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይን የ4ቱን የአዲሶቹን ዕጩዎች ስም ዝርዝር በማካተት መልሶ ማሳተም እስከ 3.5 ሚሊዮን ብር እንደሚያስወጣው በመጥቀስ) እና ከሥነ ሥርዓት አንጻርም አስቸጋሪ እንደሆነ ለማስረዳት ሞክሯል። ሆኖም በቦርዱ ላይ ፓርቲው የአፈፃጸም ማመልከቻ ማቅረቡን ተከትሎ ሰኔ 04፣ 2013 ዓ.ም 4ቱንአራቱን የፓርቲውን ተወካዮች በዕጩነት መዝግቧቸዋል።

ይህ በፍርድ ቤቱ የተላለፈው ውሳኔ እና በከባድ ወንጀል የተከሰሱ በእስር ላይ የሚገኙ የፓርቲ አባላት በዕጩነት መካተት አንዱ በምርጫ ዑደቱ ከተስተዋሉት ልዩ ክስተቶች ውስጥ ሲሆን ሁኔታው በምርጫው ቀን እነዚህ ዕጩዎች በየተወዳደሩባቸው የምርጫ ክልሎች ቢያሸንፉ በቀጣይ በክሳቸው ዙሪያ ምን ሊከሰት ይችላል የሚል ትልቅ ጥያቄ ጉዳዩን በሚከታተሉ ወገኖች ዘንደ የፈጠረጥሮ ነበር። ከዚህ ጉዳይ በተጨማሪ እንደ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ ፓርቲ (ኢዜማ)፣ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ፓርቲ (አብን)፣ እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) አንደኛው ክንፍ በቅድመ ምርጫ እና የድኅረ- ምርጫ ወቅቶች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ችሎት ተእዛዝ እንዲሰጥላቸው በመጠየቅ ጉዳዮቹን ወደ ፍርድ ቤት ሥርዓት መውሰዳቸው ሳይጠቀስ አይታለፍም።

## የቅሬታ አይነቶች እና የት እንደሚቀርቡ (የምርጫ ህግ፣ አንቀፅ 152-155)



# ምዕራፍ ፬፡ የምርጫ ትዝብት ዘዴ እና ውሱንነት

## የድምጽ መስጫ ምርጫ ቀን ትዝብት ዘዴ (Methodology)

በኢትዮጵያ ስድስተኛው አጠቃላይ አገር አቀፍ ምርጫ ላይ ሕብረቱ ከትግራይ ክልል በስተቀር በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ከ3000 በላይ ታዛቢዎችን አሠማርቷል። ሕብረቱ የምርጫ ሂደቱን ከምርጫ ቦርድ ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ ያስችላሉ ተብለው ከወጡ መመዘኛዎች እና አሠራሮች አንጻር ለመገምገም የቅድመ- ምርጫ ትዝብት፣ የአጭር-ጊዜ (የድምፅ መስጫ ዕለት) ትዝብት እና የረጅም ጊዜ ትዝብት የአሠራር ዘዴዎችን በጥቅም ላይ አውሏል። የዚህ እሳቤ መነሻ ምርጫዎች በድምጽ መስጫ ቀን ከሚያጋጥሙ የአንድ ቀን ክስተቶች ይልቅ ሶስቱንም ወቅቶች ያካተተ ሂደት ነው ከሚለው የህብረቱ ጠንካራ እምነት ነው።

የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ምርጫን ለመታዘብ የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርገዋል። ሕብረቱ በበኩሉ ሶስት ተመጋጋቢ የምርጫ ትዝብት ዘዴዎችን ማለትም፤ ቋሚ ታዛቢዎችን በተመጣጣኝ ስምሪት (Proportional Stationary Observation)፣ አመቺነትን መሰረት ባደረገ የቋሚ ታዛቢዎች ስምሪት (Convenient observation) እና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች (Mobile observation) ተጠቅሟል። እያንዳንዱ የትዝብት አሠራር ዘዴ የራሱ ጠንካራ ጎኖች ያሉት ከመሆኑም በተጨማሪ ሌሎቹን ለመደገፍ ያገለግላል።

## ቋሚ ታዛቢዎችን ተመጣጣኝ በሆነ ስምሪት በማሰማራት የሚካሄድ ትዝብት (Proportional Stationary Observation)

በተለያዩ ክልሎች እና የከተማ መስተዳደሮች ከሚገኙ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ሥርጭት ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ታዛቢዎችን በማሰሠማራት ላይ ያተኩራል። በዚህ ዓይነቱ የናሙና አወሳሰድ መሠረት ታዛቢ ቡድኑ (ህብረቱ) በቁጥር የበለጡ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሚገኙበት ክልል በቁጥር የበለጡ ታዛቢዎችን ያሰሠማራል። (በዚህ ሁኔታ በኢትዮጵያ የተመጣጣኝ ሥምሪት ዘዴ ሆኖ የኦሮሚያ ክልልን እንደ ማመሳከሪያ ሊያገለግል ይችላል) ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የምርጫ ጣቢያዎችን በሚይዘው ክልል የሚሰሠማሩት ታዛቢዎች ብዛት ላይ ተመሥርቶ የተመጣጣኝ ዘዴ በሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች የሚሠማሩትን ታዛቢዎች ብዛት ይወስናል። ይህ የመታዘቢያ ዘዴ የታዛቢ ቡድኖችን በመላው አገሪቱ ያለውን የድምፅ አሰጣጥ እና የድምፅ ቆጠራ ሂደት በተመለከተ ጠንካራ ድምዳሜዎች ላይ እንዲደርሱ በማስቻል የአገር አቀፍ የምርጫ ሂደቱን በተመለከተ በከፍተኛ ደረጃ አስተማማኝ መረጃ (ዳታ) ለማግኘት ያስችላል።

## አመቺነትን መሰረት ባደረገ የቋሚ ታዛቢዎች ስምሪት የሚደረግ ትዝብት (Convenient observation)

ከተመጣጣኝ የታዛቢዎች ስምሪት ዘዴ በተለየ ይህ ዘዴ በድምጽ መስጫ ዕለት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ታዛቢዎችን በማሠማራት ላይ ያተኩራል። በዚህ የስምሪት ዘዴ የሚሰማሩ ታዛቢዎች ከመኖሪያቸው አቅራቢያ በሚገኝ አንድ የምርጫ ጣቢያ በመገኘት ቀኑን በሙሉ በአንድ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ በመሆን የድምፅ አሰጣጥና የድምፅ ቆጠራ ሂደቱን ታዝበው ሪፖርት ያደርጋሉ። ለእነዚህ ታዛቢዎች የተሰጣቸው መጠሪያ እንደሚያመለክተው ታዛቢዎች የሚሠማሩት በዋናነት መራጮች በድምፅ አሰጣጡ እና በአጠቃላይ የምርጫ ሂደቱ ሕጋዊነት ላይ የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸው ለማገዝ ነው። ይህ የትዝብት ዘዴ ስለ ምርጫው አካሄድ መረጃ የሚሰጥ ቢሆንም ስለ አጠቃላይ የምርጫ ሁኔታው ሙሉ እና ተመጣጣኝ ምስል ላይሰጥ ይችላል።

# ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት የሚደረግ ትዝብት (Mobile observation)

በሌላ በኩል ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ልዩ ባሕሪያቸው ቀኑን በሙሉ በአንድ የምርጫ ጣቢያ ከመቀመጥ ይልቅ በመንቀሳቀስ መታዘብ ሆኖ እንደ ተመጣጣኝ ወይም አመቺ ታዛቢዎች ሊመደቡ ይችላሉ። የእንቅስቃሴያቸው ዝርዝር በምርጫ ታዛቢ ቡድኑ የሚወሰን ቢሆንም የህብረቱ ታዛቢዎች በድምፅ መስጫው ዕለት ከአምስት (5) እስከ ስምንት (8) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በመንቀሳቀስ የምርጫ ጣቢያዎችን አከፋፈት እና የድምፅ ቆጠራ ሂደት ይታዘባሉ። ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች የምርጫውን አካሄድ በተመለከተ የሚሰጡት መረጃ የተቆራረጠ ቢሆንም ከቋሚ ታዛቢዎች በተለየ ከድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ውጪ የነበረውን የምርጫ ቀን ሁኔታ የተመለከተ መረጃ ይሰጣሉ። ህብረቱ በሰኔ 14 ቀን ፣2013 ዓ.ም እና በመስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተካሄዱት ምርጫዎች ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን አሠማርቷል።

ከዚህ በታች የቀረበው ሠንጠረዥ በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች በሰኔ እና መስከረም ወር የምርጫ ዙሮች ህብረቱ ያሰሠማራቸውን ታዛቢዎች ብዛት እና ዓይነት አጠቃሎ ይዟል። ተከታዩ ሠንጠረዥ ህብረቱ በሰኔው እና በመስከረሙ ምርጫዎች ያሰማራቸውን የታዛቢዎችን ብዛት እና ዓይነት በክልል እና በከተማ መስተዳደር ምደባ ከፋፍሎ ያቀርባል።

የ ሕብረቱ ታዛቢዎች በ አይነት፣ ስምሪት ጊዜ እና የሪፖርት ብዛት




ሕብረቱ የምርጫ ትዝብት ሥራውን ንድፍ ባዘጋጀበት ወቅት ለቅድመ ምርጫ፣ የምርጫ ቀን እና የድኅረ- ምርጫ ትዝብት የምርጫውን የተለያዩ ጉዳዮች በተመለከተ አስተማማኝ እና ሁሉን አቀፍ ድምዳሜዎች ላይ ለመድረስ እንዲያስችለው የመረጠው የተመጣጣኝ የታዛቢዎች ስምሪት ዘዴን ነበር። ህብረቱ ለቅድመ- ምርጫ ትዝብት ስድስተኛው አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች ይደረጉባቸዋል ተብለው በሚታሰቡት በ72[20] ዞኖች ውስጥ በዞን ሁለት ታዛቢዎችን በማሠማራት 144 የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችን ለማሰሠማራት ዕቅዶ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ህብረቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የምርጫ ጣቢያዎች የሚገኙበትን የኦሮሚያ ክልል የስምሪት ቁጥሩ የማመሳከሪያ ነጥቡ አድርጎ በመውሰድ ከ1,500 እስከ 2,500 የድምጽ መስጫ ቀን ታዛቢዎችን ለማሠማራት ወስኖ ነበር። በመጨረሻም ህብረቱ ለድኅረ- ምርጫ ትዝብት ሥራው ተጨማሪ 106 የረዥም ግዜ ታዛቢዎችን በመጨመር ቁጥራቸውን ከ144 ወደ 250 ለማሳደግ ዕቅዶ ነበር። ሆኖም ህብረቱ በእያንዳንዱ ከታች በተመለከቱት የምርጫ ዙሮች ወቅት ካጋጠሙት በተለያዩ የውስጥና የውጭ ተግዳሮቶች ምክንያት ይህን የናሙና አወሳሰድ ዘዴ መተግበር ሳይችል ቀርቷል።

20 የህብረቱ የቅድመ- ምርጫ የአሠራር ዘዴ የትግራይ ክልል ውስጥ በተከፈተው ጦርነት ምክንያት ክልሉ ከምርጫ ውጭ እንዲሆን በመወሰኑ ምክንያት የትግራይ ብሔራዊ ክልል በዚህ ዘዴ ውስጥ እንዲካተት አልተደረገም።

# የሕብረቱ የምርጫ ትዝብት ዘዴዎች ውሱንነት

## የቅድመ- ምርጫ ትዝብት

ሕብረቱ በሰኔ እና በመስከረም ወራት ከሚካሄዱትን የድምፅ አሰጣጥ ሂደቶች አስቀድሞ የነበረውን ሁኔታ እንዲታዘቡ የቅድመ ምርጫ ታዛቢዎችን አሠማርቷል። በሰኔ ወር ምርጫ ወቅት ህብረቱ በጠቅላላው 117 የመራጮች ምዝገባ ታዛቢዎች የተሠማሩ ሲሆን በመስከረሙ ምርጫ በስድስት ክልሎች የተሠማሩ 51 ታዛቢዎች የቅድመ-ምርጫ ሁኔታውን ታዝበዋል። ህብረቱ በየቅድመ-ምርጫ ሂደቱን በታዘበበት ወቅት የታቀዱትን የአሠራር ዘዴዎች እንዳይተገብር የተለያዩ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል።

ውስጣዊ ተግዳሮቶች ሲታዩ፣ ሕብረቱ እንደ ኦሮሚያ እና የሱማሌ በመሳሰሉ ዋና ዋና ክልሎች በሚፈለገው መጠን ታዛቢዎችን ለመመልመል ያልቻለ ሲሆን እነዚህ ክልሎች ከአስተዳደራዊ መዋቅር አንፃር በኦሮሚያ 22 እንዲሁም በሶማሊ ክልል ደግሞ 11 ዞኖችን ይይዛሉ። ህብረቱ በአንፃራዊነት አዲስ የተቋቋመ ድርጅት እንደመሆኑ ታዛቢዎችን በመመልመል ረገድ በአባል ድርጅቶች ላይ የተመረኮዘ ቢሆንም ይህ በሁለቱ ክልልሎች ውስጥ ይበልጡኑ አስቸጋሪ ሆኖበታል።

በሰኔ ወሩ ምርጫ የምርጫ ቦርድ ለታዛቢዎች የታዛቢነት ዕውቅና ባጅ የሰጠው የመራጮች ምዝገባው ከተጀመረ በኋላ በመሆኑ ምክንያት ህብረቱ የመራጮች ምዝገባ ትዝብቱ ላይ ያጋጠመው ሌላኛው ተግዳሮት ነው። በአንዳንድ ቦታዎች የህብረቱ ታዛቢዎች አድራሻ ከሥልጠና ቦታዎች በርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ምክንያት ቀደም ሲል ላሰለጠናቸው ታዛቢዎች ባጆቻቸውን ለማድረስ ከፍተኛ ተግዳሮት አጋጥሞታል።

በመጨረሻም ወጥነት የጎደለው የመራጮች ምዝገባ ሂደት በህብረቱ የትዝብት ዘዴ ላይ ተጽዕኖ የፈጠረ ሌላኛው ተግዳሮት ነበር። እንደ አብነት ለመጥቀስ፤ በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግሥት የተካሄደው የመራጮች ምዝገባ በከፊል አለመካሄዱ በክልሉ ከተሠማሩት ስምንት የመራጮች ምዝገባ ታዛቢዎች መካከል አራቱን እንዳይታዘቡ አድርጓቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የቅድመ ምርጫው ወቅት በምርጫ ቦርድ በኩል የግንኙነት/መረጃ ክፍተቶች የነበሩ መሆናቸው እንዲሁም ቦርዱ ከተለመደው አሠራር በተለየ ከመራጮች ምዝገባ ቀድሞ በማካሄዱ የተነሣ ህብረቱ የእጩዎች ምዝገባ ሂደቱን ለመታዘብ አልቻለም።

ከዚህ በተጨማሪም በቅድመ ምርጫ ትዝብት ሂደት ውስጥ በነበሩ የመረጃ ልውውጥ ክፍተቶች አማካኝነት ሕብረቱ ታዛቢዎችን ለማሰማራት ያቀደው የድምፅ መስጫው ቀን በጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ይሆናል በሚል እሳቤ ላይ ተመስርቶ የነበረ በመሆኑ የቅድመ-ምርጫ ታዝቢዎችን ሥልጠና የሰጠው በነሐሴ ወር 2013 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ነበር። ከዚህም በመቀጠል ስልጠና የወሰዱትን የቅድመ-ምርጫ ታዛቢዎች ከነሐሴ ወር 2013 ዓ.ም መጀመርያ አንስቶ በማሰማራቱ ህብረቱ በሰበሰበው መረጃ (ዳታ) ጥራት ላይ ጉልህ ተጽእኖ አሳድሯል። በተጨማሪም በሰኔ ወር በተካሄደው ምርጫ ባልተሳተፉ ቦታዎች ላይ ምርጫ ይካሄዳል በሚል እምነት ሕብረቱ በ6 ክልሎች የቅድመ-ምርጫ ታዛቢዎችን አሠማርቶ ነበር። ሆኖም ግን ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በነሐሴ ወር አጋማሽ ላይ የድምፅ መስጫው ቀን በመስከረም 20 ቀን ፣ 2014 ዓ.ም. እንደሆነ አሳወቀ። በተጨማሪም ምርጫ የሚካሄድባቸውን አካባቢዎች በተመለከተ ደግሞ ምርጫ በሰኔ ወር ፣2013 ዓ.ም በተለያዩ ምክንያቶች ባልተካሄደባቸው በሐረሪ እና ሱማሌ ክልሎች እንዲሁም በከፊል በምርጫው በተሳተፉት የደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ድጋሚ ድምፅ በሚሰጥባቸው አካባቢዎች እንደሆነ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕዝበ ውሳኔ ድምጽ አሰጣጥ በሚካሄድባቸው ዞኖች እና ልዩ ወረዳዎች የድምጽ መስጠት እንደሚከናወን አስታወቀ። ይህ ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) የቅድመ ምርጫ ታዛቢዎችን ቀደም ብሎ ምርጫ በማይካሄድባቸው ቦታዎች በማሰማራቱ ቀድመው ለታዛቢዎች በተሰጡት የትዝብት ቅጾች ሥር የተካተቱት ጥያቄዎች ጥራት እንዲጓደል ብሎም የሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) የቅድመ-ምርጫ ትዝብትሥራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

## የድምጽ መስጫ ቀን ምልከታ (ትዝብት)

ሕብረት ለምርጫ ተግባራዊ ለማድረግ ያቀደውን የምርጫ ትዝብት የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በተፈለገው መንገድ እንዲሰሠራ በአገሪቱ ከሚገኙት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ቁጥር ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው የኦሮሚያ ክልል በመሆኑ ምክንያት በኦሮሚያ ክልል የሚሰማሩት ታዛቢዎች ብዛት ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃጸር በእጅጉ አስፈላጊ ነበር። በዚሁም መሰረት በኢትዮጵያ ባሉት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ሥርጭት ላይ ተመሥርቶ 37% ያክሉ የድምጽ መስጫ ቀን ታዛቢዎች በኦሮሚያ ክልል የሚሠማሩ መሆን ነበረባቸው። ሆኖም በተለያዩ ውስጣዊ እና ውጫዊ ምክንያቶች የተነሳ ሕብረት ለምርጫ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ ተመጣጣኝ የናሙና አወሳሰዱን ለማሳካት ያሰበውን ያክል የሚያስፈልጉትን ታዛቢዎች መመልመል፣መቅጠርና ማሰሠማራት አልቻለም። ከኦሮሚያ ክልል በተጨማሪ

ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) በመስከረም ወር በተካሄደው ምርጫ የትዝብት ሥራ በሱማሌ ክልላዊ መንግሥት ታዛቢዎችን በመመልመል እና በማሰማራት ረገድ ጠንካራ ተግዳሮት አጋጥሞት ነበር።

ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) በተለይም በሰኔ ወር ካጋጠሙት የውስጥ ችግሮች ለመጀመር በኦሮሚያ ክልል ውስጥ መሠረቱን የጣለው በጣም በቅርቡ የነበረ በመሆኑ በክልሉ ውስጥ አስፈላጊውን የታዛቢዎች ብዛት ለማግኘት የሚያስችል ጥንካሬ አልነበረውም። ከዚህ በተጨማሪም ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) ምንም እንኳን በተወሰኑ የኢትዮጵያ ክፍሎች ታዛቢዎችን መቅጠር ቢችልም አባል ድርጅቶች የታዛቢዎችን ስሞች በሰጡበት ወቅት ስልክ ቁጥሮችን ባለመስጠታቸው ምክንያት ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) በተለያዩ አጋጣሚዎች ከታዛቢዎች ጋር ለመገናኘት፣ መረጃ ለመለዋወጥ፣ ለማሰሠልጠን እና ለማሰሠማራት አልቻለም።

ሆኖም ተከስተው የነበሩ የውስጥ ችግሮች እንዳሉ ሆነውም የሕብረቱን የምርጫ ትዝብት ፕሮጀክት ያጋጠመው ዋነኛው ችግር አስተማማኝ ተመጣጣኝ ናሙና እንዲኖረው ያስችለው ዘንድ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያቀደውን ያክል የታዛቢዎች ብዛት ማሠማራት አለመቻሉ እና በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጠው ትክክል ያልሆነ የታዛቢነት ዕውቅና ፈቃድ ዘግይቶ ለሕብረቱ መድረሱ ናቸው። በተጨማሪም የተለያዩ ድክመቶች የተስተዋሉበት የነበረ ሲሆን ይህም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እና በአገራችን ሌሎች ክልሎች ያሠማራቸው ታዛቢዎች ብዛት በከፍተኛ ደረጃ እንዲመነምን አድርጓል። ምንም እንኳን በመስከረም ወር በተካሄደው ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ የተሻለ ቢሆንም በሰኔ ወር ምርጫ ወቅት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) የሰጣቸው የዕውቅና ባጆች የተሳሳቱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ እነዚህም የተሰጡት እስከ ምርጫው ቀን ድረስ ዘግይተው ለሕብረቱ የደረሱ ነበር። ምንም እንኳን ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) ከሰኔ የድምፅ መስጫ ቀን በፊት እስካለው ቀን ምሽት ድረስ ለታዛቢዎቹ ባጆችን ለማድረስ የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ያደረገ ቢሆንም ከአገልግሎትና ዘግይቶ የዕውቅና ባጆች ዘግይተው ከመሰጠታቸው ጋር በተያያዘ ብዙዎቹ ታዛቢዎች ዕውቅና ያላገኙ ሲሆን ባለማግኘታቸውም ምክንያት ሕብረት ለምርጫ ከቀጠራቸው እና ካሠለጠናቸው ከ3,000 በላይ ታዛቢዎች ውስጥ ማሠማራት የቻለው 2,050 ብቻ ነው።

## ድኅረ- ምርጫ ምልከታ

በድኅረ ምርጫ የታዛቢነት ተግባር ረገድ ሕብረቱ ቀደም ሲል ተግባራዊ ባደረጋቸው የቅድመ ምርጫ እና የድምጽ መስጫ ቀን የትዝብት ተግባሮች ላይ ያጋጠሙት ዓይነት ከፍተኛ ተግዳሮቶች አላጋጠሙትም። ይህ ሊሆን የቻለው ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) ቀደም ሲል በቅድመ ምርጫ እና ድኅረ ምርጫ የትዝብት ተግባሮች ዕውቅና ያገኙ ታዛቢዎችን በማሠማራቱ ምክንያት ነው። ሆኖም ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) በከፊል የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ መራጮች በድምጽ መስጫው ቀን ድምጽ ያልሰጡ በመሆኑ የተነሣ ምርጫው በመደበኛው የምርጫ አካሄድ ያልተከናወነ በመሆኑ ሕብረቱ ለማሰማራት አቅዶ የነበረውን የታዛቢዎች ብዛት (250) ሊያሰማራ አልቻለም። ሙሉ የአገሪቱ ክፍሎች በምርጫው ላይ ባልተሳተፉበት ሁኔታ ታዛቢዎችን በተመጣጣኝ ሁኔታ ማሠማራት የሚቻል ያልነበረ ሲሆን ሕብረት ለምርጫ በሰኔ ወር የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ ለድኅረ ምርጫ ትዝብት ተግባር 97 ታዛቢዎችን ብቻ በማሰማራት በመስከረም ወር በተካሄደው ምርጫ ደግሞ በሐረሪ፣ ሱማሌ እና ደብብ ክልሎች 50 የድህረ-ምርጫ ታዛቢዎችን አሠማርቷል።

ሆኖም ይህን ክፍል ከማጠናቀቃችን በፊት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ቅሬታዎች የሚሰሙት በማዕከል ደረጃ እንደሆነ በማሳወቁ ምክንያት ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) የድኅረ ምርጫው ወሳኝ ክፍል የሆኑት ምርጫውን ተከትለው የሚመጡትን የቅሬታ ሥነ- ሥርዓቶችን በተመለከተ በቂ መረጃ መሰብሰብ አልቻለም። ይህን ክፍተት ለመሸፈን በመዲናዋ አዲስ አበባ የሚገኙትን ታዛቢዎች በመጠቀም የቅሬታ አሰማም ሂደቱን ከመገምገም በተጨማሪ ሕብረቱ (ሕብረት ለምርጫ) ለቦርዱ የቀረቡትን ቅሬታዎችን ይዘት እና ከቅሬታ መስማት ሥነ ሥርዓቶቹ በኋላ የተላለፈውን ውሳኔ ለመረዳት ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር ሠርቷል።



**80 የመረጃ ተቀባዮች**

በሰኔ ምርጫ በጊዚያዊ የመረጃ ማእከል ውስጥ ይሰሩ ነበር።

**40 የመረጃ ተቀባዮች**

በመስከረም ምርጫ በጊዚያዊ የመረጃ ማእከል ውስጥ ይሰሩ ነበር።




“የሕብረት ለምርጫ መረጃ ተቀባዮች በጊዜያዊ የመረጃ ማዕከል ውስጥ፣ በሥራ ላይ ሆነው

# ምዕራፍ ፫፡ የሕብረቱ የምርጫ ትዝብት ግኝቶች

## የቅድመ ምርጫ ትዝብት

### መግቢያ

ለማንኛውም የምርጫ ሂደት በቅድመ ምርጫ ወቅት የሚከናወኑ ሁኔታዎች ወሳኝ ሚና አላቸው። ከድምፅ መስጫ ዕለት አስቀድሞ ባሉት ወራት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ህጋዊነት እና ጥራት (የቅድመ ምርጫ ግዜ)፤ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን ህጋዊነት እና ፍትሃዊነት ይወስናሉ። በቅድመ ምርጫ ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል የምርጫ አስተዳደሪው አካል ለሕዝብ ይፋ የሚያደርገው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ፣ የዕጩ ተፎካካሪዎች እና የመራጮች ምዝገባ፣ የምረጡኝ ዘመቻ እና የተፎካካሪ ፓርቲዎች ክርክር መድረክ፣ የመራጮች ሥልጠና እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ የሲቪል ማህበራት በምርጫው ሂደት ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ምቹ ማድረግን ይጨምራል። ይሁን እንጂ በቅድመ ምርጫ ወቅት የሚከናወኑት ተግባራት በእነዚህ ጉዳዮች ብቻ የተወሰኑ አይደሉም። በአገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ታዛቢ ቡድኖች ከወጡ የቅድመ ምርጫ ግኝቶች ጋር በተስማማ መልኩ ሕብረቱ የቅድመ-ምርጫ ትዝብት ሥራውን ያከናወነ ሲሆን በትዝብቱም የተፎካካሪ ፓርቲዎችን እና ዕጩዎች ምዝገባ፣ የመራጮች ምዝገባ፣ የሚዲያ ክትትል (ሞኒተሪንግ) እና ሌሎች በቅድመ ምርጫ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የደኅንነት ስጋቶችን ለመታዘብ የሚያስችል ቅጾችን በማዘጋጀት ታዝቧል።

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ

የምርጫ ቦርድ በሰኔ እና በመስከረም በ2 ዙር ለሚከናወኑት ምርጫዎች ያስቀመጠውን የጊዜ ሰሌዳ ለሰኔ ምርጫ እስከ በታህሳስ 16 ቀን፣ 2013 ዓ.ም እንዲሁም ለመስከረም ምርጫ ደግሞ በነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ለሕዝብ ይፋ አድርጓል ። በዚሁም መሠረት ቦርዱ ለዕጩዎች እና ለመራጮች ምዝገባ፣ የመራጮች ትምህርት እና የምረጡኝ ቅስቀሳ፣ የዕጣ አወጣጥ፣ የምርጫ ወረቀቶች ኅትመት እንዲሁም ሌሎች ከድምጽ መስጫ ቀን በፊት የሚከናወኑ ተግባራትን አስመልክቶ ዝርዝር የጊዜ ሰሌዳ አስቀምጧል።

ቦርዱ በሰኔ እና በመስከረም ወራት ለተካሄዱት በ2 የተለያዩ ዙሮች ለሚያከናውናቸው ምርጫዎች ይፋ ያደረጋቸው የጊዜ ሰሌዳዎች ላይ ግልጽ ያልሆኑ አንዳንድ ሁኔታዎች የነበሩ ሲሆን ይህም ህብረቱ እና ሌሎች የታዛቢ ቡድኖች ከመራጮች ምዝገባ አስቀድሞ ተጠብቆ የነበረውን የዕጩዎች ምዝገባ መታዘብ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። በተጨማሪም ቦርዱ የምርጫውን ሂደት በተመለከተ ለታዛቢዎች አሰቀድሞ በቂ መረጃ አልሰጠም። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ ምክንያቶች የመራጮች ምዝገባ በየጊዜው ከመራዘሙ-ጋር ተያይዞ በአጠቃላይ በመራጩ ሕብረተሰብ ዘንድ ግራ የመጋባት ስሜት ፈጥሮ ነበር። ቦርዱ አስቀድሞ ለሕዝብ ይፋ ያደረገው የድምጽ መስጫ ቀን ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም የነበረ ቢሆንም የድምጽ መስጫውን ቀን ወደ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም አራዝሟል። በተመሳሳይ በጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ለማካሄድ ዐቅዶ የነበረውን የ2ኛ ዙር ምርጫ ደግሞ ወደ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም አራዝሟል። ይህም ቦርዱ ለ6ኛው አጠቃላይ አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫዎች ከሥራው ከፍተኛ ጫና የማሳደር ባህሪ አኳይ በቂ እና የተሟላ ዝግጅት አለማድረጉን የሚያሳይ ነው። ይሁን እንጂ ህብረቱ ቦርዱ 6ኛውን አጠቃላይ አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫዎች በተቻለ መጠን ሰላማዊ እና ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ እንዲከናወኑ ያለውን ጽኑ ፍላጎት ይገነዘባል።

ቦርዱ ምርጫው በተረጋጋ ሁኔታ እንዲያልፍ ያከናወናቸውን ሥራዎች መጠነ ሰፊነት ህብረቱ የሚረዳ ቢሆንም በምርጫ ወቅት ከምርጫ የጊዜ ሰሌዳ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማለትም በመራጮች፣ ዕጩ ተፎካካሪዎች፣ የምርጫ ታዛቢ የሲቪል ማህበራት እና ሌሎች አጋሮች መካከል የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦች በአጠቃላይ የምርጫ ዝግጅት ጥራት ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖራቸው ሊሰመርበት ይገባል።

## የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የዕጩ ተፎካካሪዎች ምዝገባ

ለ6ኛ አጠቃላይ ምርጫ በተመለከተ የዕጩዎች (ፓርቲዎች እና የግል ተፎካካሪዎች) ምዝገባ የተከናወነው ከየካቲት 8 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ የካቲት 21 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ነበር። ይሁን እንጂ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ጥያቄ መሠረት የዕጩዎች ምዝገባ እስከ የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ.ም ሊራዘም ችሏል። ምንም እንኳን ምርጫው የተካሄደው በመላው ኢትዮጵያ ባይሆንም በሰኔ እና በመስከረም ወራት በ2 ዙር ለተከናወኑት ምርጫዎች የዕጩዎች ምዝገባ የተከናወነው በየካቲት ወር ውስጥ ነበር። ይህ ምዝገባ ቦርዱ የሰኔውን ምርጫ ለማከናወን አስቀድሞ ዕቅድ ባልያዘበት የትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን እንዲሁም በሶማሌ እና በኦሮሚያ ክልሎች ከምርጫው ራሳቸውን ያገለሉ ፓርቲዎችን ያካተተ አይደለም።

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የዕጩ ተፎካካሪዎች ምዝገባ የተከናወነው ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ለግል ተፎካካሪዎች ወይንም በፓርቲዎች አማካኝነት በዕጩነት ለሚቀርቡ ዕጩዎች ያወጣውን አዲስ መስፈርት እና መመሪያ መሠረት በማድረግ ነው። በዚህ መሠረት የምርጫ ቦርዱ አገራዊ ፓርቲዎች ማሰባሰብ ያለባቸው የአባላት ፊርማ ቀድሞ ከነበረው ከ1,500 ወደ 10,000 ከፍ ያደረገ ሲሆን ፊርማቸው የሚሰበሰቡት ፓርቲዎች አባላቱ ቢያንስ በ4 የኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ መሆን ይኖርባቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ ለየክልል ፓርቲዎች ማሰባሰብ ያለባቸውን የአባላት ፊርማ ከ750 ወደ 4000 ከፍ ያደረገ ሲሆን አባላቱ በአንድ ክልል ወይንም የከተማ አስተዳደር የሚገኙ ሊሆኑ እንደሚገባ ደንግጓል። ቦርዱ በሰኔ እና በመስከረም በ2 ዙሮች ለተከናወኑት ምርጫዎች 53 የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመዘገበ ሲሆን ከዚሀም ውስጥ 20ዎቹ ለብሔራዊ እና 26ቱ ደግሞ በክልል ደረጃ በምርጫው ተሳትፈዋል። በሌላም በኩል ቦርዱ የግል ተፎካካሪዎች ማሰባሰብ ያለባቸው የድጋፍ ፊርማ 5,000 መሆን እንዳለበት የወሰነ ሲሆን በፓርቲያቸው አማካኝነት በዕጩነት ለሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች ደግሞ 3000 የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ እንዳለባቸው ወስኗል። በተመሳሳይ ሁኔታ ይህም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ የሚፎካከሩ ዕጩዎች ማሰባሰብ ያለባቸው ፊርማ ከአሁን ቀደም ከተከናወኑት ምርጫዎች የፊርማ ማሰባሰብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ብልጫ አሳይቷል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ቦርዱ የዕጩዎች ምዝገባ የሚካሄድበትን የጊዜ ሰሌዳ አስቀድሞ ባለማሳወቁ ምክንያት ህብረቱ የቅድመ ምርጫ ሂደቶችን በበቂ ሁኔታ መታዘብ አልቻለም። ቦርዱ የጊዜ ሰሌዳውን አስቀድሞ አለማሳወቁ ህብረቱ የምርጫ ቅድመ ሁኔታዎችን ለመታዘብ በቂ ዝግጅት እንዳያደርግ ምክንያት ሆኗል። ይሁን እንጂ ከቦርዱ እና ከሌሎች ታዛቢ ቡድኖች ሪፖርት በመነሣት ለ6ኛ ዙር አጠቃላይ ምርጫ የተመዘገቡት አጠቃላይ ተፎካካሪ ዕጩዎች ብዛት 9,505 ሲሆን ከዚህም ውስጥ 98 በመቶ (9,357) ዕጩዎች በፖለቲካ ፓርቲዎች የቀረቡ ዕጩዎች ሲሆኑ የተቀሩት 2 በመቶ (148) ዕጩዎች በግል ተፎካካሪነት የተመዘገቡ ናቸው። የኤን ዲ አይ/አይ አር አይ (NDI/IRI) ውስን ምልከታ ሪፖርት እንደሚያመለክተው 60 በመቶ (86 ዕጩዎች) በግል ተፎካካሪነት የተመዘገቡት ዕጩዎች በሶማሌ ክልል ሲሆን በክልሉ መስከረም 20 ቀን በተካሄደው 2ኛ ዙር ምርጫ ላይ በብቸኛ ተፎካካሪነት የቀረበው የብልጽግና ፓርቲ ነው። ከታች የተመለከተው ምስል ቦርዱ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ለተካሄደው ምርጫ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጠቅላላ መረጃ የሚያሳይ ነው። [21]

21 National Electoral Board of Ethiopia, List of Registered Candidates for Sixth National and Regional Elections of Ethiopia (Published on 16 June 2021) nebe.org.et/en/candidate-list [Last Accessed 24 August 2021]




በተጨማሪም 12 ፓርቲዎች ከ100-250 ዕጩ ተፎካካሪዎችን ያቀረቡ ባልደራስ ለእውነተኛ ፓርቲ፣ የወላይታ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ግንባር፣ የጋምቤላ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የሲዳማ ሕዝቦች አንድነት ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፣ የአፋር ሕዝቦች ፓርቲ እና የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲን ይገኙበታል። ከዚህም ሌላ 28 ፓርቲዎች ለ6 ኛው አጠቃላይ አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ከ100 ያነሱ ዕጩ ተፎካካሪዎችን አስመዝግበዋል።

ምንም እንኳን ምርጫው ክፍተኛ ውድድር እንደሚታይበት እና የተለያዩ ኅብረ ብሔራዊ ፓርቲዎች እንደሚሳተፉ የተጠበቀ ቢሆንም በኦሮሚያ ክልል ይንቀሳቀሱ የነበሩ ትላልቅ ፓርቲዎች ማለትም የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረንስ (ኦፌኮ) እንደዚሁም በሶማሌ ክልል በመስከረም ከተከናወነው ምርጫ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ) ራሳቸውን ማግለላቸው የምርጫው ጥራት እና ተፎካካሪነት ላይ ተጽዕኖ ፈጥሯል። ለአብነት ያህል የብልጽግና ፓርቲ በኦሮሚያ ክልል በፌደራል ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካለው አጠቃላይ 170 መቀመጫዎች ውስጥ ብልጽግና ፓርቲ 104 ዕጩዎችን አቅርቦ የተፎካከረ ሲሆን፤ በተመሳሳይ በሶማሌ ክልልም ምርጫው ያለ ትልልቅ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ተካሂዷል። ከዚህም ባሻገር ግልፅነት ከጐደላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በተያያዘ ቦርዱ በሰኔ ወር 2012 ዓ.ም ከታዋቂው የኦሮምኛ ሙዚቃ ድምፃዊ ሀጫሉ ሁንዴሳ መገደልን ተከትሎ በተነሣው ረብሻ ጋር በተያያዘ በህግ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ 4 የባልደራስ ፓርቲ አባላትን በዕጩነት ላለመመዝገብ የወሰደውን ውሳኔ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በመሻሩ እና በእጩነት መመዝገብ እንደሚችሉ በመወሰኑ ምክንያት ቦርዱ ለከፍተኛ የሀብት እና የግዜ ብክነት ተዳርጓል።

ምንም እንኳን ከላይ የተመለከቱት ውስብስብ የፖለቲካ ችግሮች የዕጩዎች ምዝገባ ላይ ተጽእኖ ቢፈጥሩም ቦርዱ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል ተፎካካሪዎች የተሻለ እና ምቹ ሁኔታዎችን ሊፈጥሩ የሚያስችሉ ሥራዎች ሊሰሩ እንደሚገባቸው ህብረቱ ያምናል። ይህን ማድረግም ቀጣይ የሚደረጉ ምርጫዎችን ተፎካካሪነት ከማሳደጉም ባሻገር ምርጫዎች ያለፉክክር በአንድ ፓርቲ ብቸኛ ተወዳዳሪነት እንዳይደረጉ ያስችላል።

## የመራጮች ምዝገባ

የኢትዮጵያ  ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሰኔ ወር በተከናወነው ምርጫ የመራጮች ምዝገባን ለማከናወን ያቀደው ከመጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ.ም. እስከ ሚያዚያ 15 ቀን 2013 ዓ.ም. ነበር። ይሁን እንጂ ከፀጥታ እና ከሎጅስቲክስ አቅርቦት ችግሮች ጋር በተያያዘ ምክንያት ቦርዱ አስቀድሞ ይዞ የነበረውን የመራጮች ምዝገባ ጊዜ እስከ ሚያዚያ 29 ቀን 2013 ዓ.ም በ2 ሳምንት ጊዜ አራዝሟል። በተመሳሳይ መልኩ በሶማሌ እና አፋር ክልሎች የመራጮች

ምዝገባ ግዜን እስከ ግንቦት 6 ቀን 2013 ዓ.ም ለ3 ሳምንታት አራዝሟል። በመስከረም ወር ለተደረገው 2ኛ ዙር ምርጫ የአዲስ መራጮች ምዝገባ የተከናወነው በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ ከነሐሴ 26 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2013 ዓ.ም ባሉት ቀናት ሲሆን፤ አስቀድሞ የመራጮች ምዝገባ በመጋቢት ወር ምዝገባ ተጀምሮ በተቋረጠባቸው አንዳንድ አካባቢዎች ከጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 5 ቀን 2013 ዓ.ም ተከናውኗል።

በ2ኛ ዙር ምርጫ ወቅት ቦርዱ ለመራጮች ምዝገባ ያስቀመጠውን የጊዜ ሰሌዳ አላራዘመም። ይህም በአፋር ክልላዊ መንግሥት፣ በሶማሌ ክልል፤ እና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በሚገኙት የመተከል እና ካማሺ ዞኖች ውስጥ የመራጮች ምዝገባ ሂደት በተስተጓጎለበት ሁኔታ መሆኑ የ6ኛ አጠቃላይ ብሔራዊ እና ክልላዊ ምርጫ በመላው የኢትዮጵያ ክፍሎች የመራጮች ምዝገባ በወጥነት ላለመከናወኑ አስረጂ ነው። በሌላ በኩል ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት አንጻር ግማሽ ያህል ቦታዎች ላይ እስከ ሚያዚያ ወር ድረስ የምርጫ ጣቢያዎች ያልተቋቋሙ መሆናቸውን ቦርዱ ካቀረበው ሪፖርት እና ሌሎች የታዛቢ ቡድኖች ካቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህም ሌላ የመራጮች ምዝገባን አስመልክቶ በርካታ ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በከሶማሌ ክልላዊ መንግሥት የቀረበውን ቅሬታ ለመመርመር ልዩ ቡድን ተዋቅሮ ምርመራ እንዲያደርግ ቦታው ድረስ የተላከ ሲሆን የተቋቋመው ልዩ ቡድን የምርመራ ሥራውን እስኪያጠናቅቅ ድረስ ምርጫው ለመስከረም እንዲዘዋወር ተደርጓል።

ከቦርዱ ከተገኘው መረጃ በመነሣት ከሰኔው ምርጫ አስቀድሞ ወደ 31 ሚሊየን የሚገመቱ መራጮች ተመዝግበዋል። ከዚህም ሌላ 7.8 ሚሊየን መራጮች በመስከረም ወር ለተደረገው ምርጫ የተመዘገቡ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1.3 ሚሊየን መራጮች በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ውሳኔ /ሪፈረንደም/ ላይ ብቻ የተሳተፉ ናቸው።

ህብረቱም 117 ታዛቢዎችን ከመጋቢት ወር 2013 ዓ.ም እስከ ግንቦት ወር 2013 ዓ.ም ድረስ የመራጮች ምዝገባ በተከናወነባቸው 1,209 የምርጫ ጣቢያዎች ላይ በማሰማራት አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ምርጫ መረጃዎችን አሰባስቧል። ይሁን እንጂ ቦርዱ በየጊዜው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ በመለዋወጡ ምክንያት ሕብረቱ ለመስከረሙ ምርጫ የተደረገውን የመራጮች ምዝገባ ሂደት በአግባቡ መታዘብ አልቻለም። ከዚህም በመነሳሣት ህብረቱ ያቀረባቸው ግኝቶች፣ ህብረቱ ለሰኔው ምርጫ በተካሄደው የመራጮች ምዝገባ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል። ቦርዱ በመራጮች ምዝገባ ወቅት ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች እንዲሁም ህብረቱ የመራጮች ምዝገባን ለመታዘብ የነበረውን ዝግጁነት ታሳቢ በማድረግ ከመጋቢት ወር እስከ ግንቦት 2013 ዓ.ም ድረስ ሕብረቱ ባደረገው ትዝብት እና በሰበሰባቸው ሪፖርቶች ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው። የህብረቱ ትዝብት የድምፅ መስጫ ግዜው ወደ መስከረም የተራዘመባቸውን የምርጫ ጣቢያዎችንም ይጨምራል።

ህብረቱ ምርጫ ከታዘበባቸው 1,209 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ውስጥ 860 (71.2 በመቶ) የሚሆኑት በከተማ አካባቢ የሚገኙ የምዝገባ የምርጫ ጣቢያዎች ሲሆኑ የተቀሩት 348 (28.8 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ በገጠር አካባቢ የሚገኙ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል። የሕብረቱ ታዛቢዎች መረጃዎቹን ያሰባሰቡት ከ1,196 መደበኛ የምዝገባ ጣቢያዎች ነው። ኅብረቱ የተሰማሩ ታዛቢዎቹን ሥራ ለማቀላጠፍ ሲባል የመራጮች ምዝገባ መታዘቢያ ልዩ ቅጽ እንዲሁም በምዝገባ ሂደት የሚያጋጥሙ አሳሳቢ ሁነቶችን መመዝገቢያ ቅጽ ያዘጋጀ ሲሆን እነዚህን ቅጾች በርካታ ጥያቄዎችን ያካተቱ ናቸው። ጥያቄዎቹም የተዘጋጁት የምርጫ ጣቢያዎችን አደረጃጀት ማለትም የምርጫ አስፈጻሚዎች እና የምርጫ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን ለመመዘን፤ እንዲሁም የመራጮች ምዝገባ ሕጋዊ መስፈርቶችን አሟልቶ የተከናወነ መሆኑን ለመገምገም በሚያስችል መንገድ ነው። ከዚህም ሌላ ቅጹ የተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው እና እንደ ልብ መንቀሳቀስ የማይችሉ ግለሰቦች ወዘተ) እና የኮቪድ-19 የመከላከያ መንገዶች በመራጮች ምዝገባ ሂደት በአግባቡ የተተገበሩ መሆኑን ለመከታተል የሚያስችል ነው።

## ፩/ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች አደረጃጀት

የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች አደረጃጀት እና ተደራሽነት በመራጮች ምዝገባ ሂደት ላይ ቁልፍ አንድምታ አለው። ህብረቱ ያሰማራቸው የመራጮች ምዝገባ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት በመነሣት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ውስጥ የነበረው የምዝገባ ጣቢያዎች አደረጃጀት እና ተደራሽነት የተለያየ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። መረጃ ከተሰበሰበባቸው 1,209 የምርጫ ጣቢዎች መካከል 22.7 በመቶ የሚሆኑት በጣም ቅርብ እና በቀላሉ ተደራሽነት ያላቸው ሲሆኑ 72.6 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ መራጮች በአንፃራዊነት በቀላሉ ተጉዘው ሊደርሱባቸው በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ የተቋቋሙ ናቸው። በህብረቱ ታዛቢዎች ከቀረበው ሪፖርት በመነሣት 75.2 በመቶ የመራጮችምርጫ ምዝገባ የተከናወነው በሕንጻዎች ወይንም በየተደራጁ ቢሮዎች፣ ሲሆን 99.2 በመቶ በድንኳን ውስጥ፣ 12.7 በመቶ

ውጪ ሜዳ ላይ እና 3 በመቶ ደግሞ በሌሎች ቦታዎች ላይ በተቋቋሙ የምዝገባርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ነው። ሌላው ጠቃሚ ግኝት ደግሞ አብዛኛዎቹ የምዝገባ ጣቢያዎች የተቋቋሙት በምርጫ ሕግ በተፈቀዱ ቦታዎች ላይ ቢሆንም 21 የምዝገባ ጣቢያዎች በግለሰብ ቤቶች ውስጥ፣ 10 በፖለቲካ ፓርቲ ቢሮዎች ውስጥ፣ 3 በፖሊስ ጽሕፈት ቤት ውስጥ እንደዚሁም ሌሎች 3 የምዝገባ ጣቢያዎች ደግሞ በወታደራዊ ካምፕ ውስጥ የተቋቋሙ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

ሌሎች የሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ምርጫ የመራጮች ምዝገባን የተመለከቱ ግኝቶች ደግሞ ከታች የተዘረዘሩት ናቸው፦

- በ12 በመቶ የምዝገባ ጣቢያዎች ውስጥ የአካል ጉዳት ያለባቸው ወይንም የመንቀሳቀስ ውስንነት ያለባቸው (አዛውንቶች፣ ሕፃናት ያዘሉ እናቶች ወዘተ) ያለ ድጋፍ ወደ ጣቢያዎችው መግባት አልቻሉም ነበር፤

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ባስቀመጠው መመሪያ መሠረት ሁሉም የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ከፀሐይ እና ከዝናብ የሚከላከል መጠለያ ሊኖራቸው ይገባል። ይሁን እንጂ 57 በመቶ የምዝገባ ጣቢያዎች ተመዝጋቢዎችን ከፀሐይ ወይንም ከዝናብ መከለያ አልነበራቸውም። በዚህም መሠረት በገጠራማ አካባቢዎች ከነበሩት የምዝገባ ጣቢያዎች ውስጥ 63 በመቶ መጠለያ ያልነበራቸው ሲሆን በተነጻጻሪነት 54 በመቶ የከተማ የምዝገባ ጣቢያዎች መጠለያ አልነበራቸውም።

- ቦርዱ ካስቀመጠው መመሪያ ጋር በሚስማማ መሠረት 71 በመቶ በሚሆኑ የምዝገባ ጣቢያዎች ውስጥ ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈጻሚዎች የነበሩ ሲሆን የህብረቱ ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ በ930 የምዝገባ ጣቢያዎች (77 በመቶ) ውስጥ በአማካኝ ቢያንስ አንድ ሴት የምርጫ አስፈጻሚ ተካታለች።

- የአካል ጉዳት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ የህብረቱ ታዛቢዎች በታዘቧቸው ጣቢያዎች ውስጥ በ95.4 በመቶ የምዝገባ ጣቢያዎች የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች በምርጫ አስፈጻሚነት አልተካትተቱም።

- የሕብረቱ ታዛቢዎች ጉብኝት ባደረጉባቸው አብዛኛዎቹ ቦታዎች የምዝገባ ቁሳቁሶች ተሟልተዋል። ይሁን እንጂ የህብረቱ ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ በ40 የተለያዩ ጊዜያቶች የመራጮች የጣት አሻራ ቀለም (ፓድ) አልነበረም። ከዚህም ሌላ የህብረቱ ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ በ16 የምዝገባ ጣቢያዎቹ ውስጥ ጆርናል እንደዚሁም በ12 በተለያዩ ጊዜያት የምስክርነት ቅጾች ያልተሟሉ መሆናቸውን አረጋግጧል።

በመራጮች ምዝገባ ወቅት በተጎበኙ ቦታዎች ላይ ያልነበሩ ቁሳቁሶች



## ፪/ የመራጮች ምዝገባ ሂደት እና አሳታፊነት

የማንኛውንም የመራጮች ምዝገባ ጥራት እና ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ ሂደቱ በምርጫ ሕግ ውስጥ የተካተቱ ድንጋጌዎችን ያከበረ መሆኑን መገምገም እጅግ አስፈላጊ ነው። እነዚህን ቁልፍ መስፈርቶች የመራጩን ማንነት / መታወቂያ/ መርምሮ ማረጋገጥ፣ የመራጭነት ምዝገባ ሂደቱን የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች አለመኖር፣ በቂ እና የተሟላ የምርጫ ቁሳቁሶች አቅርቦት እና የመራጮች ምዝገባ ምርጫ አስፈጻሚዎች ምደባ እንዲደዚሁም ከመራጮች የተሟላ ግላዊ መረጃዎችን ጠይቆ በመመዝገብ የምርጫ ካርድ መስጠትን፣ የቅሬታ አቀራረብ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ሌሎች ሕብረቱ ያዘጋጃቸው መከታተያ ቅጽ ውስጥ የተመለከቱ መረጃዎችን ይጨምራል። በአጠቃላይ የህብረቱ ታዛቢዎች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለምሳሌ እንደ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በመተከል ዞን የመራጮች ምዝገባ የቦርዱን መመሪያዎች ያልተከተለ መሆኑን እንደዚሁም በሶማሌ ክልላዊ መንግሥት የመራጮች ምዝገባ ተቋርጦ የነበረ መሆኑን እና በመላው አገሪቱ ይደረግ የነበረው የመራጮች ምዝገባ የመረጃ እጥረት እንደነበረበት ለመገንዘብ ችሏል። ከታች የተመለከቱት መረጃዎች ከ1,209 የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባን አስመልክቶ የህብረቱ ታዛቢዎች ያሰባሰቧቸው መረጃዎች ናቸው።

## ፫/ የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት

የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ተደራሽነት ለምርጫ ሂደት ግልፀኝነት መሠረታዊ ነው። በዚህም መሠረት ሕብረቱ ያሰማራቸው የመራጮች ምዝገባ ታዛቢዎች ከታዘቡባቸው ጣቢያዎች ውስጥ 96 በመቶ የሚሆኑት የታዛቢዎች፣ ጋዜጠኞች ወይንም የፓርቲ ወኪሎች ብዛት ላይ ገደብ አልተደረገም። ይሁን እንጂ በ44 አጋጣሚዎች - ሕብረቱ ከወሰደው ናሙና 3.6 በመቶ ውስጥ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎቹ ለታዛቢዎች፣ ለጋዜጠኞች ወይንም ለፓርቲ ወኪሎች ውስን ተደራሽነት ነበራቸው። የሕብረቱ ታዛቢዎች ከጎበኟቸው 1,209 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች መካከል በ1,163 (96 በመቶ) በሚሆኑት ውስጥ ገብተው መታዘብ የቻሉ ሲሆን በ42 ሁኔታዎች ሂደቱን በከፊል እንዲታዘቡ እንደዚሁም በ3 ሁኔታዎች ደግሞ ታዛቢዎች ወደ መራጮች ምዝገባ ክፍል ውስጥ እንዳይገቡ ተከልክለዋል። በሌላም በኩል 498 የምዝገባ ጣቢያዎች ወይንም በ41 በመቶ በሚሆኑት ሌሎች ታዛቢ ቡድኖች የተገኙ ሲሆን በ710 ወይንም በ59 በመቶ የምዝገባ ጣቢያዎች የሕብረቱ ታዛቢዎች ብቻ ተገኝተዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ እጅግ ጠቃሚው ግኝት ከ1,209 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች መካከል በ967 (80 በመቶ) የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ላይ የፓርቲ ወኪሎች አልተገኙም። በ94 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ደግሞ የፓርቲ ወኪሎች የተገኙ ሲሆን በሌሎች 147 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች 2 ወይንም ከዛ በላይ የፓርቲ ወኪሎች ተገኝተዋል።

## ፬/ የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ

በአብዛኞዎቹ የመራጮች የምዝገባ ጣቢያዎች የምዝገባ ሂደት የተጀመረው በሰዓቱ ሲሆን የህብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው 1,209 ጣቢያዎች መካከል በ1,160 የምዝገባ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ የተጀመረው ከረፋዱ 3፡30 ደቂቃ በፊት ነው። ከዚህም ውስጥ 582 ጣቢያዎች ከጠዋቱ 2፡30 በፊት የተከፈቱ ሲሆን ይህም ቦርዱ ያስቀመጣቸውን መመሪያዎች የተከተለ ነው። በ578 ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገበ የጀመሩት ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡30 ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን በ5 የተለያዩ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ እስከ ቀኑ 6፡00ሰዓት ድረስ አልተጀመረም። በሌላም በኩል የህብረቱ ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ በ 928 (75.1 በመቶ) የምዝገባ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ ሂደት ከ30 ደቂቃ ላልበለጠ ጊዜ ሳይቋረጥ የተከናወነ ሲሆን በ36 ጣቢያዎች በአየር ሁኔታ (በአብዛኛው ዝናብ)፣ በ6 ጣቢያዎች በምዝገባ ቁሳቁሶች እጥረት፣ በ5 ጣቢያዎች በመራጮች ላይ በደረሰ ዛቻ እና ማስፈራሪያ፣ እንዲሁም በ16 ጣቢያዎች ምንነታቸው ባልተረጋገጠ ምክንያቶች የመራጮች የምዝገባ ሂደት ተቋርጧል። ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት በመነሣት ከምዝገባ ጣቢያዎቹ መካከል በ96 በመቶ ከረፋድ ከሰዓት 11 ሰዓት ተኩል 30 ወይንም ከምሽቱ 12 ሰዓት በፊት ተዘግቷል። ይሁን እንጂ በ54 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ ከምሽቱ 12 ሰዓት በኋላ ቀጥሎ ሲከናወን እንደነበረ እና ይህም ከመዝጊያ ሰዓቱ በፊት ረዣዥም ሰልፎች ስለነበሩ እንደሆነ የመራጮች ምዝገባ ታዛቢዎች ገልፀዋልገልፀዋል።

፭/ ሂደቱን የተከተለ የመራጮች ምዝገባ

የሕብረቱ ታዛቢዎች በታዘቡባቸው1,209 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች መካከል በ1,190 (በ98 በመቶ) የመራጮች ግላዊ መረጃዎች በአግባቡ ተመዝግበዋል። እንዲሁም ከ1,209 የምዝገባ ጣቢያዎች ውስጥ በ1,200 (99 በመቶ) የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ለተመዝጋቢዎች የመራጭነት ካርድ የተሰጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ይሁን እንጂ የመራጮች ምዝገባ ብሎ በዘፈቀደ ሁሉንም መመዝገብ ሳይሆን በሕግ የተቀመጡ የመራጭነት መስፈርቶችን

የሚያሟሉ መራጮችን መለየት እና መመዝገብን የሚያካትት ሂደት ነው። ሊመዘገቡ የተሰለፉ ግለሰቦችም መመዝገብ ሳይሆን ለምርጫ ብቁ የሆኑ እና አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን ያሟሉ መራጮችን ለይቶ መመዝገብ ነው። የህብረቱ ታዛቢዎች ምልከታ ባደረጉበት ወቅት ከ123 ጣቢያዎች ቢያንስ አንዲት ሴት ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ መግለጽ ባለመቻሏ ወይንም የምርጫ መስፈርቶችን ባለማሟላቷ እንዳትመዘገብ መከልከሏን፤ እና ከ143 የምርጫ ጣቢያዎች መካከል ቢያንስ አንድ ወንድ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን ባለማሟላቱ ሳይመዘገብ እንደቀረ ለማወቅ ተችሏል። ይህ በመራጮች ምዝገባ ሂደት ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ያወጣቸው መመሪያዎች ተፈጻሚ አለመሆናቸውን ያመላክታል። ይሁን እንጂ በ47 ጣቢያዎች መታወቂያ የያዙ እና የመኖሪያ መስፈርቶችን ያሟሉ ብቁ መራጮች ሳይመዘገቡ ወደ ቤታቸው እንደተመለሱ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በ35 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች መራጮች ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ሳያሳዩ ለመራጭነት ለምርጫ ተመዝግበዋል።

## ፮/ በመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች የተመደቡ የፀጥታ አካላት

ሕብረቱ ከታዘባቸው ሁኔታዎች መካከል በመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ተገኝተው የነበሩ የፀጥታ አካላት እና እነዚህ የጸጥታ አካላት የነበራቸው ሚና አንዱ ነው። ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት በእያንዳንዱ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያ ቢያንስ 2 የፀጥታ አካላት መመደብ እና ከጣቢያ ውጪ ሆነው ፀጥታ ማስከበር ያለባቸው ሲሆን ይህም የመራጮችን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ደኅንነት ለመጠበቅ እና የምዝገባ ቁሳቁሶችን ለመጠበቅ ነው። ይሁን እንጂ የህብረቱ ታዛቢዎች ትዝብት ካደረጉባቸው 1209 የምዝገባ ጣቢያዎች ውስጥ በ733 (61 በመቶ) የፀጥታ አካላት አልተመደቡም። በተጨማሪም ከታዛቢዎች ሪፖርት ላይ ለመረዳት እንደተቻለው በ93 በመቶ የፀጥታ አካላት ወደ መራጮች ምዝገባ ጣቢያ ያልገቡ መሆናቸውን ወይም ወደ ምዝገባ ጣቢያው የሚገቡት የምዝገባ ጣቢያው ሊቀመንበር ወደ ውስጥ እንዲገቡ ሲጠይቃቸው ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። ሆኖም ግን፣ ከምርጫ ሕጉ በተጻራሪ በ31 አጋጣሚዎች የፀጥታ ኃይሎች እንዲገቡ ሳይጠየቁ በራሳቸው ፍቃድ ወደ ምዝገባ ጣቢያዎች ገብተዋል።

## ፯/ የኮቪድ-19 ስርጭት መከላከያ አከባበር ተገዢነት

6ኛው አጠቃላይ አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ የተደረገው የኮሮና ወረርሽኝ በተከሰተበት ወቅት ነበር። በዚህ ምክንያት ቦርዱ በሁሉም የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ተፈጻሚ መሆን ያለባቸውን መመሪያዎች አስቀምጧል። እነዚህንም መመሪያዎች ታሳቢ በማድረግ ሕብረቱ በምዝገባ ወቅት የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች ተግባራዊ የሆኑባቸው ደረጃዎችን ገምግሟል። ቦርዱ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በምዝገባ ጣቢያዎች ሁሉም የኮቪድ-19 መከላከያዎች መሟላት አለባቸው። ምንም እንኳን በአብዛኞዎቹ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች እንደ የፊት እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል እና ሳኒታይዘር ያሉ የኮቪድ-19 መከላከያ ግብአቶች ቢሆንም በ52 በመቶ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች የእጅ መታጠቢያ አልነበረም። በ60 በመቶ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ደግሞ የምርጫ አስፈጻሚዎች የእጅ ጓንት አልነበራቸውም። የምርጫ አስፈጻሚዎች የፊት ጭንብልን በተመለከተ በ13 በመቶ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች የፊት እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል አላደረጉም ነበር። በተጨማሪም 23 በመቶ የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች ሊመዘገቡ ከመጡ ግለሰቦች መካከል 48 በመቶ የፊት እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል አላደረጉም ነበር።

# የቅድመ ምርጫ ድባብ

በሰኔ እና መስከረም ለተደረገው 6ኛው አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ መዳረሻ ወራቶች (ቅድመ ምርጫ ሂደቶችን በ4 ንዑስ ክፍሎች ከፋፍለን ለማየት ተሞክሯል። ይሁን እንጂ ሕብረቱ ባቀረበው ሪፖርት ውስጥ ታዛቢዎቹ ከመስከረም ወር ምርጫ በፊት የነበሩ የቅድመ ምርጫ ከባቢያዊ ሁኔታ መረጃዎችን ያካተተ ቢሆንም የቅድመ ምርጫ ታዛቢዎችን የመደበው በሰኔ የተደረገው ምርጫ የመጀመሪያ ዙር ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ሕብረቱ የሚዲያ ክትትል ቡድኑን የጥናት ውጤት እንዲሁም የተለያዩ የዴስክ ጥናቶችን በዚህ የቅድመ ምርጫ ግኝቶቹ ላይ አካቷል።

## የምረጡኝ የምርጫ ዘመቻ እና የሚዲያ ሽፋን

ሕብረቱ አሰልጥኖ ካሰማራቸው የምርጫ ታዛቢዎች ባሻገር የራሱ የሆነ የሚዲያ ክትትል ቡድን በማቋቋም በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም እና በመስከረም 2014 ዓ.ም ምርጫዎች ወቅት የምርጫ ሂደቱን አስመልክቶ የተሰጡ የሚዲያ

ሽፋኖችን ተከታትሏል። ይህ ሪፖርት የሚዲያ ክትትል ቡድኑ ያሰባሰባቸው መረጃዎች ማጠቃለያ ነው። ሕብረቱ የመራጮች መረጃ የማግኘት መብትን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የዕጩዎች መረጃ የማሠራጨት መብት፣ ሐሳብን የመግለጽ መብት እና ሚዲያዎች ያላቸውን የተለያዩ ሐሳቦችን የማንሸራሸር ነፃነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚዲያ ክትትል ቡድኑ የአገሪቱ ሚዲያዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለመራጮች ቅስቀሳ፣ የዕጩ ተፎካካሪዎች የምረጡኝ ዘመቻ እና ክርክርን አስመልክቶ የሰጡትን ሽፋን ለመገምገም ሞክሯል።

የሚዲያ ክትትል ቡድኑ ከተለያዩ የመንግሥት እና የግል ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ተመልካቾች /አድማጮች/ አይነት እና ብዛት፣ የሕጋዊነት ደረጃ እና የሥርጭት ቋንቋዎቻቸውን መሠረት በማድረግ ናሙና ወስዷል። በዚህም መሠረት 7 የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን የምርጫ ዘመቻውን ሲያሳዩ ከነበሩት ጣቢያዎች መካከል የኦሮሞ ብሮድካስት ኔትዎርክ (ኦቢኤን) ቴሌቪዥን ለምርጫ ዘመቻ ሰፊ ጊዜ የሰጠ ሲሆን ፋና ቴሌቪዥን በ2ኛ ደረጃ ለምርጫ ዘመቻ ሽፋን የሰጠ ጣቢያ ነው።




የሚዲያ ክትትል ቡድኑ የሚዲያ ሽፋን ግምገማ ለማድረግ አኃዛዊ እና አኃዛዊ ያልሆኑ (Qualitative and Quantitative methods) ዘዴዎችን በመጠቀም የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የተሰጠውን የአየር ሰዓት መጠን ለመገምገም ሞክሯል። ይህ በሚዲያ ክትትል ቡድኑ የተዘጋጀው ሪፖርት ነው፦ Final CECOE Media Monitoring Unit Report[22]

የህብረቱ የሚዲያ ክትትል ቡድን ክትትል ባደረገባቸው የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በተለያዩ ፕሮግራሞቻቸው የሰጡትን የአየር ሰዓት ሽፋን ለመገምገም ሞክሯል። ይህም ግምገማ የተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ለምርጫው የሰጡትን ትኩረት እና በተለያዩ ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ምን ያህል ስለ ምርጫው እንደዘገቡ የተደረገ ዳሰሳዊ ጥናት ነው። በዚህም መሠረት የቴሌቪዝን ጣቢያዎቹ በዜና ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ለምርጫው ሰፊ ሽፋን የሰጡ ሲሆን በቀጣይነት ደግሞ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የተደረጉ ክርክሮች በ2ኛነት የአየር ሰዓት ወይንም የሚዲያ ሽፋን የሰጡ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል።

22 የህብረቱን የሚዲያ ክትትል ሪፖርት ለማግኘት በሚከተለው የድር አድራሻ ላይ እንዲያገኙ ይመከራሉ፦ bit.ly/3KL75jx




በግምገማው ወቅት የሕብረቱ የሚዲያ ክትትል ቡድን እነዚህ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የኢኮኖሚ ጉዳዮች፣ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ የፖለቲካ፣ የዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ወዘተን አስመልክቶ ምን ያህል የአየር ሰዓት እንደሰጡ ለመገምገም ሞክሯል። የቡድኑ የግምገማ ውጤት እንደሚያሳየው የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻው ከሁሉም ጉዳዮች የበለጠ ከፍተኛ የአየር ሰዓት ወይንም የሚዲያ ሽፋን ያገኘ ሲሆን የምርጫ ቅድመ ዝግጅቶች ደግሞ በ2ኛ ደረጃ ሽፋን አግኝተዋል።




በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የተደረገውን ክርክር አስመልክቶ 11 የተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች 27 በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ለተደረጉ ክርክሮች የአየር ሰዓት በመስጠት የሸፈኑት ሲሆን እነዚህ ክርክሮች ቢያንስ በተለያዩ 12 የፖለቲካ ፓርቲ የተወከሉ ዕጩዎች መካከል የተደረገ ነው። በክርክሮቹ ላይ የተሳተፉት ፓርቲዎች የተመረጡት ፓርቲው ለምርጫ ባቀረባቸው ዕጩዎች ብዛት ላይ በመመርኮዝ ነው። በምርጫ ዘመቻ ወቅት የቴሌቪዥን ጣቢዎቹ እንደ ሪፖርቶች፣ ቃለ መጠይቆች እና ቶክ ሾዎች የሰጡት የአየር ሰዓት ዝቅተኛ ነበር ነው።

የተለያዩ ተቋማት ማለትም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የክልል መንግስታት እና ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት በተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያ መርሃ ግብሮች ላይ ያገኙትን የአየር ሰዓት ሽፋን ስንመለከት ብልጽግና ፓርቲ በአብዛኛው የቴሌቪዥን ጣቢዎች ሰፊ የአየር ሰዓት እና የሚዲያ ሽፋን አግኝቷል። ይህ የሚዲያ ክትትል በሰኔ እና በመስከረም በ2 የተለያዩ ዙሮች የተደረጉ ምርጫዎችን ይሸፍናል።



ከዚህም ሌላ የህብረቱ የሚዲያ ክትትል ቡድን 9 የተለያዩ በሕዝብ ዘንድ የጎላ ታዋቂነት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ከየካቲት 8 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ከመስረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ በፌስቡክ ገጾቻቸው ላይ ያሰራጪቸውን የምረጡኝ ቅስቀሳ ይዘቶች ገምግሟል። ይህም ፌስቡክ በምርጫ ቅስቀሳ ላይ ያለውን የጎላ ተጽዕኖ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተደረገ ሲሆን 9ኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአጠቃላይ 1,222 የተለያዩ ይዘት ያላቸው ጽሑፎችን /ምስሎችን/ በፌስቡክ ገፆቻቸው ላይ የለጠፉ ሲሆን ይህም በአማካይ በቀን 16 የፌስ ቡክ መልዕክቶች (ልጥፎች) ማለት ነው።




## የመራጮች፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ነጻነት ወይንም የደረሰባቸው ማስፈራሪያዎች እና ዛቻዎች

በቅድመ ምርጫ ወቅት መራጮች፣ ዕጩ ተፎካካሪዎች፣ ሚዲያ፣ የሲቪል ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸው ነጻነት፣ የምርጫው የግልጽነት፣ አካታችነት እና ተጠያቂነት ለመመዘን ጠቋሚ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በመራጮች፣ በምርጫ አስፈጻሚዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ላይ የሚደርሱ ዛቻዎች እና ማስፈራሪያዎች የምርጫውን ሕጋዊነት እና ፍትሃዊነት ለመመዘን ጉልህ ማሳያዎች ናቸው። እነዚህን ሁኔታዎች ከግንዛቤ በማስገባት ህብረቱ ታዛቢዎቹን ከማሰማራት ባሻገር የሚዲያ ክትትል ቡድን በሐረሪ፣ ሶማሌ እና በደቡብ ሕዝቦች ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥት ሰኔ ላይ የተደረገውን ምርጫ አስመልክቶ የቅድመ ምርጫ ትዝብት አድርገዋል።

የህብረቱ ታዛቢዎች ከመስከረም ምርጫ በፊት ከተሰማሩባቸው አካባቢዎች ያሰባሰቧቸው መረጃዎች እንደሚያሳዩት ምርጫውን ለመታዘብ በክልሎቹ ውስጥ የተመደቡ ጋዜጠኞች ወይንም የሚዲያ ተቋማት እንደዚሁም በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ የደረሰ ዛቻ ወይንም ማስፈራሪያ አልነበረም። በተጨማሪም በታዛቢዎቹ ምልከታ መሠረት በመራጮችም ሆነ በምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ የደረሰ ዛቻ ወይንም ማስፈራራት አልነበረም።

ይሁን እንጂ የህብረቱ የሚዲያ ክትትል ቡድን ካደረገው ጥናታዊ ዳሰሳ በመነሣት በኢትዮጵያ 6ኛ አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ወቅት በአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ላይ እንግልት የደረሰባቸው መሆኑን ያረጋግጣል። ይህም ለሰኔ ምርጫ መዳረሻ ወቅት በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ላይ የተለያዩ እንግልቶች የደረሱ መሆናቸውን እና እነዚህም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ ሁኔታዎችን ለመዘገብ በተሠማሩ ጋዜጠኞች ላይ መጉላላት የደረሰ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከዚህ ውስጥ የካቲት 6 ቀን 2013 ዓ.ም እና ሚያዚያ 13 ቀን 2013 ዓ.ም በተከታታይ የተገደሉት የኢዜማ ፓርቲ የቢሾፍቱ ቅርንጫፍ ሊቀመንበር እንዲሁም የኤፍራታ እና ግድም ወረዳ ሊቀመንበር ከ6ኛው አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫዎች ጋር በተያያዘ ጥቃት ከደረሰባቸው የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩዎች ውስጥ ይገኛሉ። ከዚህ ባሻገር የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ፓርቲ አንድ አባል ሚያዚያ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በጎንደር ከተማ የተገደለ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ ሚያዚያ 1 ቀን 2013 ዓ.ም የአብን ፓርቲ አባል በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን ውስጥ መገደሉ የሚታወስ ነው። በተጨማሪም ሐምሌ 2013 ዓ.ም በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መተከል ዞን ውስጥ በቦሮ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ዕጩ ላይ የተፈጸመው ግድያ በክልሉ የነበረውን የፀጥታ እና ደኅንነት ችግር ማሳያ ነው።

የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች መታሰር በዕጩዎች ላይ የደረሰው እስራት እንደዚሁም በሚዲያ ባለሙያዎች ላይ የደረሱት እንግልቶች እና እስራት በቅድመ ምርጫ ወቅት የታዩ ችግሮች መሆናቸውን የህብረቱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት ላይ ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ ያህል የአሜሪካ ድምፅ ባቀረበው ዘገባ የኦሮሞ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ መሪ የጦር መሣሪያ ይዘው ተገኝተዋል በሚል ክስ የ3 ወር እስራት ተወስኖባቸው በእስር ላይ በመቆየታቸው ቦርዱ ለዕጩ ተፎካካሪዎች ምዝገባ ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ አልፏቸዋል። ይህ እስራት ፓርቲው ግለሰቦቹ በምርጫው ተመዝግበው ለፓርላማ እንዳይወዳደሩ ሆን ተብሎ የተፈጸመ ድርጊት መሆኑን እንደሚያምን ገልጿል። ከዚህም ባሻገር ሁለት በመስቃን እና ማረቆ ለፉክክር የቀረቡ የግል ተወዳዳሪዎች በደቡብ ክልል መንግሥት ምክንያቱ ባልተረጋገጠ ሁኔታ ታስረው ቆይተው የዕጩዎች ምዝገባ ጊዜ ከመጠናቀቁ አስቀድሞ መለቀቃቸውን ለመረዳት ተችሏል። በአጠቃላይ የኦፌኮ ከፍተኛ አመራሮች ከሰኔ ምርጫ አስቀድሞ መታሰራቸው ተከትሎ ፓርቲው ራሱን ከምርጫ በማግለሉ የብልጽግና ፓርቲ በኦሮሚያ ክልል በአብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ለብቻው እንዲወዳደር መንገድ ከፍቶለታል። ከዚህም በመነሳት ሕብረቱ ለወደፊት የሚደረጉ ምርጫዎች ላይ አስፈላጊ የሆኑ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ እና የነጻነት ምህዳሩ ሰፍቶ በአገራችን የተሻለ ጥራት ያለው ምርጫ መደረግ እንዳለበት መለዕክቱን ያስተላልፋል።

# የድምፅ መስጫ ቀን ትዝብት

## መግቢያ

ይህ ክፍል ሕብረቱ በሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም እና መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም በሁለት ዙሮች በተደረጉት ምርጫዎች ያደረጋቸው የትዝብት ምልከታ ግኝቶች ይቃኙበታል። ህብረቱ በድምፅ መስጫው ዕለት የምርጫው ሂደት አግባብ ባለው ስነ ስርዓት መከናወኑን ለማረጋገጥ ቀን በድምፅ መስጫ ቀን ሂደት መከታተያ ልዩ ቅጻ ቅጾችን እና የአሳሳቢ ሁነቶችን መመዝገቢያ ቅጽ በማዘጋጀት ምርጫውን ታዝቧል። እነዚህ ቅጻ ቅጾች የተለያዩ መጠይቆችን ያካተቱ ነበሩ። በድምፅ መስጫው ቀን የምርጫ አስፈጻሚዎች ወደ ምርጫው ጣቢያ የደረሱበት ሰዓት፣ የምርጫ ጣቢያዎች የተከፈቱባቸውን ሰዓቶች፣ የድምጽ መስጠት ሂደትን ምርጫ ሂደት እንደዚሁም የድምፅ ቆጠራ ሂደቶችን ለመታዘብ ሞክረዋል። በድምፅ መስጫ ቀናት ያጋጠሙ ጉልህ የሕግ ጥሰቶችን እና የምርጫውን ውጤት ሊቀይሩ የሚችሉ ተግባራት/ሂደቶች ላይ በማተኮር ምርጫውን ታዝበዋል። በዚህም መሠረት በሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም እና መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም የተደረጉት የምርጫ ቀኖች ታዛቢዎች ጉልህ የሆኑና በርካታ የአሳሳቢ ሁነት ክስተቶችንና ችግሮችን የታዘቡ ሲሆን ቦርዱ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቀጣይ ምርጫ ላይ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የእርምት እና ማሻሻያ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል።

## ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች የደረሱበት ሰዓት

### የምርጫ አስፈጻሚዎች በምርጫ ጣቢያ የደረሱበት ሰዓት

በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ መሠረት ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ከንጋቱ 12 ሰዓት ተከፍተው ለድምፅ መስጠት ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል። ለዚህም ሲባል የምርጫ አስፈፃሚዎች ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት በፊት በየምርጫ ጣቢያዎቹ መገኘት ይኖርባቸዋል።[23] ሕብረቱ ታዛቢዎቹ ወደ ምርጫ ጣቢያው ከንጋቱ 11፡30 በምርጫ ጣቢያዎቹ በመገኘት አስፈፃሚዎች ቀድመው ተገኝተው የድምፅ መስጠት ሂደቱ በሰዓቱ መጀመሩን ወይም አለመጀመሩን እንዲታዘቡ አድርጓል። በዚህም መሰረት ታዛቢዎች ከንጋቱ 11፡30 በየተመደቡባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በመገኘት የትዝብት ስራቸውን ማከናወን እንደጀመሩ ሪፖርት አድርገዋል፡፡

በሁለቱም (በሰኔ እና በመስከረም) ምርጫዎች ወቅት የህብረቱ ታዛቢዎች በጎበኟቸው የምርጫ ጣቢያዎች አብዛኞዎቹ የምርጫ አስፈጻሚዎች በሰአቱ መገኘታቸውን እና የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መከፈታቸውን ታዝበዋል። በሰኔው ምርጫ ወቅት 93 በመቶ የሚሆኑት  ታዛቢዎች ወደ የምርጫ ጣቢያዎች ሲደርሱ አስፈጻሚዎች በምርጫ ጣቢያ በመገኘት ቅድመ ዝግጅት ሲያደርጉ እንደነበረ ሪፖርት አድርገዋል። በተመሳሳይ፣ በመስከረም በተደረገው ምርጫ ወቅት 98 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች አስፈጻሚዎች አስቀድመው ተሟልተው መገኘታቸውን ለመረዳት ተችሏል።

23 *የኢትዮጵያ የምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/ 2011፣ አንቀጽ 49*

## የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት

ከዚህ ረገድ ታዛቢዎች የቀረበላቸው ጥያቄ ተገቢውን የታዛቢነት ፈቃድ (ባጅ) ካሳዩ በኋላ ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ለመግባት የመቻላቸውን ሁኔታ ወይም የምርጫ ጣቢያውን ተደራሽነት የተመለከተ ነው። በሰኔው ምርጫ 97 በመቶ፤ እንዲሁም በመስከረሙ ምርጫ በ98 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ታዛቢዎች የትዝብት ስራቸውን እንዲያከናውኑ ተፈቅዶላቸዋል። በሁለቱም የምርጫ ቀናቶች ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ አልፎ አልፎ ታዛቢዎች ለጥንቃቄ ሲባል ከምርጫ ጣቢያ እንዲወጡ ከመደረጉ በስተቀር የህብረቱ ታዛቢዎች አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱን (የምርጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ ሰዓት ጀምሮ እስኪዘጉ ድረስ) ያለውን ሁኔታ ታዝበዋል። ከዚህ በታች ያለው ምስል ከህብረቱ ታዛቢዎች የተሰበሰበን መረጃ መሠረት በማድረግ በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በእለቱ የነበረውን የተደራሽነት ሁኔታ ያሳያል።






በአጠቃላይ ቦርዱ የሕብረቱ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ በመስጠት በምርጫ ጣቢያዎቹ ተገኝተው እንዲታዘቡ በመፍቀዱ እንዲሁም የምርጫ አስፈጻሚዎች ለኅብረቱ ታዛቢዎች ላሳዩት አክብሮት እና የሥራ ትብብር ከወዲሁ ያመሰግናል። ይሁን እንጂ የታዛቢነት ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓቱ የጐላ ክፍተት እንደነበረበት ታይቷል። በዚህ ሪፖርት ውስንነቶች በሚለው ክፍል የተብራራው የዘገየ ፈቃድ አሰጣጥ መዘግየት ችግር ኅብረቱ ያሰማራቸውን የታዛቢዎች ቁጥር ብዛት በጉልህ እንዲቀንስ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ በሰኔ እና በመስከረም ምርጫዎች ባጅ የያዙ ታዛቢዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች እንዳይገቡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች የተከለከሉ ሲሆን፣ በመስከረም ምርጫ ወቅት ደግሞ በ3 ክልሎች ከቦርዱ የተሰጠውን ኦፊሴላዊ ባጅ የያዙ ታዛቢዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች እንዳይገቡ የተከለከሉባቸው ሁኔታዎች ነበሩ።

## የምርጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መከፈት

በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ቀን ከንጋቱ 12 ሰዓት[24] ተከፍተው ለመራጮች ዝግጁ መሆን ያለባቸው ሲሆን ይህም የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ ከመጠናቀቁ በፊት ሁሉም የተመዘገቡ መራጮች ድምፃቸውን መስጠት እንዲችሉ ለማስቻል ነው። ይህ ወሳኝ የምርጫ ቀን ህግ ወይም ስርዓት ሲሆን ምርጫ ጣቢያዎች በተቀመጠው ሰዓት 1500 መራጮችን ማስተናገድ መቻላቸው ጋር በቀጥታ የሚገኛኝ ነው። በተጨማሪም የምርጫ ጣቢያዎች የመክፈቻ እና የመዝጊያ ሰዓት መከበር ለመራጭነት ብቁ ሆነው ካርድ የወሰዱ ዜጐች ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ውስጥ ባለው በየትኛውም ሰዓት ድምፃቸውን የመስጠት መብታቸው እንዳይጣስ ያግዛል።

ህብረቱ በሰኔው ምርጫ ካሰማራቸው 2,116 (ሁለት ሺህ አንድ መቶ አስራ ስድስት) ታዛቢዎች የሰበሰባቸው ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት (98 በመቶ) የሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ አንድ ሰዓት (1፡00) በፉት ተከፍተው መራጮችን ማስተናገድ ጀምረዋል። በተመሳሳይ ህብረቱ ለመስከረሙ ምርጫ ካሰማራቸው 927 ታዛቢዎች ውስጥ 98 በመቶ የሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት[25] ተከፍተው እንደነበር ሪፖርት አድርገዋል። ምንም እንኳን ኅብረት ለምርጫ በሁለቱም ዙር ምርጫዎች ከጣቢያዎች አከፋፈት ጋር ያገኘው ግኝት አበረታች የነበረ ቢሆንም በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፋፋን የምርጫ ክልል ውስጥ በሚገኘው የቆሎጂ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዬች ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ የተቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች እስከ ጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ድረስ ያልተከፈቱ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደማስተካከያ የሚነሳ ነው። በአጠቃላይ በመጠለያ ካሙፑ የኅብረት ለምርጫ ልዩ የታዛቢዎች ቡድን ያደረገው ክትትል እና ሪፖርት እንደሚያሳየው በመጠለያ ካምፑ በሚገኙት 41 የሚደርሱ የምርጫ ጣቢያዎች የተስተዋለው መዘግየት ከአስፈፃሚዎች ብቃት ማነስ እና የስልጠና እጥረት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏልተችሏል።

የምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙባቸውን ቦታዎች በተመለከተ በሰኔ ወር በተካሄደው ምርጫ ወቅት 92 የምርጫ ጣቢያዎች (4 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች እንደፖሊስ ጣቢያ፣ ወታደራዊ ካምፕ እና ፖለቲካ ፓርቲ ፅ/ቤት በመሳሰሉ በምርጫ ህጉ ለምርጫ ጣቢያነት በተከለከሉ ስፍራዎች መመስረቱን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን በአንፃሩ በመስከረም ወር በተደረገው ምርጫ ይህ ሪፖርት የተደረገው በአንድ ከደቡብ ክልል በተሰማራ ታዛቢ ብቻ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። በተጨማሪም ምንም እንኳን በምርጫ ህጉ መሰረት ፓርቲዎች ከድምፅ መስጫ አራት ቀን በፊት የምርጫ ቅስቀሳ እንዳያከናውኑ[26] እንዲሁም በምርጫ ጣቢያ 200 መቶ ሜትር ርቀት ማናቸውም የቅስቀሳ ቁሳቁሶች እንዳይለጠፉ/እንዳይሰራጩ[27] የሚደነግግ ቢሆንም በሰኔና በመስከረም ወር የተሰማሩ አንዳንድ ታዛቢዎች ከዚህ በተጓዳኝ ቅስቀሳ ወይም የቅስቀሳ ቁሳቁሶች እንደነበሩ ሪፖርት አድርገዋል። የሰኔውን ምርጫ ብንመለከት 12 በመቶ የሚሆኑት ታዛቢዎች (256) በምርጫ ጣቢያ ውስጥ ወይም አካባቢ ቅስቀሳ ወይም የቅስቀሳ ቁሳቁስ እንደነበር ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን በመስከረም ወር በአንፃሩ የፅሞና ጊዜውን ባከበረ መልኩ 98 በመቶ በሚሆኑ የህብረቱ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች ቅስቀሳም ሆነ የቅስቀሳ ቁሳዉሶች እንዳልነበሩ ሪፖርት አድርገዋል።

24 ዝኒ ከማሁ

25 እዚህ ላይ ለምርጫ ትዝብት ሥራ በተዘጋጀው የታዛቢዎች ቼክ ሊስት የአፈጻጸም ክትትል ማድረጊያ ዝርዝር ላይ በተፈጠረ ነበረ የአፋን ኦሮሞ ቅጂ የኦሮሚኛ ትርጉም ችግር ምክንያት፣ ሕብረት ለምርጫ በአንድነት ሦስት የመረጃ መስጫ ምላሾችን ትንታኔ እንደሰጠባቸው (ማለትም ከጠዋቱ 12 ሰዓት በፊት፣ ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ 1 ሰዓት እና ከጠዋቱ 1 ሰዓት በፊት) ልብ ሊባል ይገባል። በመሆኑም፣ ኅብረቱ እዚህ ላይ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 1 ሰዓት በፊት አልተከፈቱም ነበር እያለ እንዳልሆነ ሊሠመርበት ይገባል።

*26 የኢትዮጵያ የምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/ 2011፣ አንቀጽ 43(1)*

*27 ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 46 (1፣ ሠ)*

# የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት

በምርጫ ሂደት ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ ተግባራት መካከል አንዱ የቦርዱ መመሪያና ደንብን ባከበረ ሁኔታ የሚቋቋሙ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አንዱ ነው። ስለዚህም የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ላይ ትዝብት አድርገዋል። በዚህም መሰረት ታዛቢዎች የነበሩትን ሁኔታዎች መታዘባቸው የምርጫ ሂደቱን ቁቡልነት ለመገምገም እንዲያስችለው ሲሆን፤ የምርጫ ጣቢያዎቹን ተደራሽነት፤ የምርጫ ቁሳቁሶች መሟላት (መገኘት) እንዲሁም ሌሎች  የምርጫ ታዛቢዎች እና የፓርቲ ወኪሎችን ተሳትፎን ለመታዘብ መገምገም ሞክረዋል። ከዚህም ባሻገር ታዛቢዎቹ በምርጫው ወቅት የኮቪድ-19 ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል የተወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች ዝግጅት ታዝበዋል። ከታዛቢዎች በተሰበሰቡት ሪፖርቶች ላይ በመመርኮዝ፣ የምርጫ ጣቢያዎችን አደረጃጀት በተመለከተ የኅብረቱ የትዝብት ግኝቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። በተጨማሪም፣ ከኮሮና ቫይረስ ጋር በተገናኘ ያሉት ግኝቶችን የሚያትተው ክፍል ቫይረሱ ያሳደረውን ተጽእኖ በሚያብራራው ክፍል ሥር ራሱን ችሎ ለብቻው ቀርቧል።

## የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት

መራጮች በቀላሉ ድምፃቸውን ለመስጠት እንዲችሉ ቦርዱ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ አካባቢዎች ሊያቋቁም ይገባዋል። በሌላ አነጋገር፣ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የተደራጁበት መንገድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች፣ ነፍሰ ጡሮች እና ሌሎች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆን አለበት። በአጠቃላይ በሰኔ (95%) እና በመስከረም (97%) የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የሁለቱም ጾታዎች እንደዚሁም የአካል ጉዳት ላለባቸው በቀላሉ ተደራሽ እንደነበሩ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን፤ የምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ከነበራቸው ተደራሽነት አኳያ ሲታዩ በሰኔና በመስከረሙ ምርጫዎች ላይ በጉልህ የሚታይ መሻሻል እንደነበራቸው ከታዛቢዎች ከተሰበሰቡት ሪፖርቶች መረዳት ተችሏል።  እዚህ ላይ፣ በሁለቱም ዙር ምርጫዎች ለሴቶችና ለወንዶች የነበረው ተደራሽነት እኩል እንደነበረ የሚያሳዩት ግኝቶች እንደተጠበቁ ሆነው በመስከረሙ ምርጫ ላይ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ከመሆናቸው አንጻር ሲታዩ የመስከረሙ ምርጫ (96%) ከሰኔው (87%) አንፃር ከፍተኛ መሻሻል አሳይተዋል።

## የምርጫ አስፈጻሚዎች ተሟልቶ መገኘት

በምርጫ ቦርድ መመሪያ መሠረት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን ለማስጀመር ቢያንስ 3 (ሶስት) የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘት ይኖርባቸዋል። ኅብረት ለምርጫ በታዘበባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሁለቱም ዙር ምርጫዎች በአማካይ 4 የምርጫ አስፈጻሚዎች ተገኝተዋል፤ በመስከረም ምርጫ ከምርጫ አስፈጻሚዎች መካከል 37 በመቶዎቹ ሴቶች ነበሩ።

## የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች አቅርቦቶች መሟላት

የድምፅ መስጫ ጣቢያ ቁሳቁሶች አቅርቦት መሟላት ለድምፅ አሰጣጡ ሂደት እጅግ ወሳኝ ነው። ከድምፅ መስጫ ዕለት አስቀድሞ ሁሉም መራጮች በአግባቡ ድምፅ መስጠት እንዲችሉ የምርጫ ቁሳቁሶች በእያንዳንዱ የድምፅ መስጫ ጣቢያ ተሟልቶ መቅረቡን እና ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ የቦርዱ ኃላፊነት ነው። በተጨማሪም በየምርጫ ጣቢያው የሚወዳደሩት ዕጩዎች ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚለያዩ በመሆኑ ቦርዱ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች መድረስ ያለባቸው  የምርጫ ቁሳቁሶች በአግባቡ መሠራጨታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

ሰኔ 14 በተደረገው ምርጫ የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው አለመቅረብ በበርካታ የምርጫ ጣቢያዎች ተስተውሏል። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተጨባጭ መታዘብ የቻሉት በሰኔው ምርጫ የምርጫ ቁሳቁሶች ሥርጭት በቂ እና አጥጋቢ እንዳልነበረ ከዚህም የተነሣ የምርጫ ጣቢያዎች በመላው አገሪቱ ከምሽቱ በ12 ሰዓት መዘጋት ሲገባቸው እስከ ምሽቱ 3፡00 ሰዓት የተራዘመባቸው ሁኔታዎች የነበሩ ሲሆን በተለይም በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግሥት፣ በጋምቤላ ክልላዊ መንግሥት እንደዚሁም በሲዳማ ክልላዊ መንግሥት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ እስከ ቀጣይ ቀን ተራዝሞ ነበር። ለአብነት ያህል 14 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች በቂ የምርጫ ወረቀት ያልነበራቸው ሲሆን ለ10 በመቶ የድምፅ መስጫ ሳጥን ጉድለት እንዲሁም በ12 በመቶ የቦርዱ ማኅተም ያልተደረገባቸው የምርጫ ወረቀቶች ነበሩ።

ይሁን እንጂ በመስከረም ምርጫ ወቅት ቦርዱ የምርጫ ቁሳቁሶችን አቅርቦት በተመለከተ ትልቅ የማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በቂ የምርጫ ቁሳቁሶች የተሠራጩ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። መስከረም 20 በተደረገው ምርጫ ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹ በተሠማሩባቸው ቦታዎች 99 በመቶ የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶች፤ ማለትም የድምፅ መስጫ ወረቀት፣ የድምፅ መስጫ ሣጥን፣ የድምፅ መስጫ ሣጥን ማሸጊያ፣ የቦርዱ ሕጋዊ ማኅተም፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የውጤትና የእርቅ ማመሳከሪያ ቅጽ እንደነበር ገልጸዋል። ይሁን እንጂ በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን በአንድ ጣቢያ ውስጥ የመራጮች መመዝገቢያ መዝገብ የጠፋ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ይህም የምርጫ አስፈፃሚዎች የተመዘገቡ መራጮችን ህጋዊነት ለመለየት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። ከታች የተመለከተው ሥዕላዊ መግለጫ በምርጫ ጣቢያዎች የነበረውን የምርጫ ቁሳቁሶች አቅርቦት የሚያሳይ ነው።




ኅብረቱ ለምርጫ ቦርዱ በሰኔ ወር ካደረገው ምርጫ ትምህርት በመውሰድ በመስከረም ላይ ላደረገው ቀጣይ ዙር ምርጫ የምርጫ ቁሳቁስ አቅርቦትን አሟልቶ በማሠራጨቱ ምስጋና እያቀረበ፤ ህብረቱ ከተለያዩ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ሲደርሱት የነበሩት የትዝብት ግኝቶች እንደሚያመለክቱት የምርጫ ቁሳቁሶች አለመሟላት እና ትክክለኛ ያለመሆን በምርጫው ሀቀኝነት ላይ ተጽኖ አሳድሯል።

ይሁን እንጂ በሰኔ እና በመስከረም በተደረገው አገር አቀፍ ምርጫ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች መባል በሚቻልበት ሁኔታ የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የምርጫ ኮሮጆዎች ባዶ መሆናቸውን ታዛቢዎች እንዲመለከቱ ተደርጓል። ይህም የምርጫውን ፍትሐዊነት እና ትክክለኛነት ከሚያመላክቱ የስነ ስርዓት ሂደት ሁኔታዎች መካከል አንዱ እንደመሆኑ የሚበረታታ ነው። በተጨማሪም ታዛቢዎች የምርጫ ቁሳቁሶች በየክልሉ እና አካባቢው ቋንቋዎች የተዘጋጁ መሆናቸውን የታዘቡ ሲሆን ይህንኑ ሁኔታ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ከዚህ በታች ተያይዟል።



### የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩ ወኪሎቸ በምርጫ ጣቢያዎች ስለመገኘት የፓርቲ ወኪሎች ምርጫ ጣቢያዎች ስለመገኘት

የፖለቲካ ፓርቲ/ዕጩዎች ወኪሎች እና ታዛቢዎች በምርጫ ቀን መገኘት ስለ ምርጫ ግልፅኝነት እና ፍትሐዊነት አንዱ ማረጋገጫ ሲሆን ይህም በድምፅ አሰጣጥ ሂደት እና በድምፅ ቆጠራ ወቅት ማጭበርበር እንዳይኖር ዋስትና የሚሰጥ ነው። በኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በሰኔ ምርጫ በ1,937 (91 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች እና ታዛቢዎች የተገኙ ሲሆን በመስከረም ምርጫ ወቅት 231 (25 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች እና ታዛቢዎች ተገኝተዋል። በአንፃሩ በመስከረም የምርጫ የነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች/ዕጩዎች ወኪሎች ተሳትፎ ከሰኔው ምርጫ ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ቁጥር መቀነሱ እጅግ አሳሳቢ ነው።

በሰኔ ምርጫ ወቅት የህብረቱ 1,910 (89 በመቶ) ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያዎች ሲከፈቱና የድምጽ መስጠት ሲጀመር የፖለቲካ ፓርቲ/ ዕጩዎች ወኪሎች መገኘታቸውን ገልፀዋል። በመስከረም በተደረገው ምርጫ ይህ ቁጥር ወደ 77 በመቶ (በ724 የምርጫ ጣቢያዎች) ቀንሷል። ሌላው ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ የህዝበ ወሳኔ ድምጽ ብቻ በተሰጠባቸው ቦታዎች የፓርቲ ወኪሎች ቁጥር በ40 በመቶ ብቻ ነበር።

# የድምፅ አሰጣጥ ሂደት

የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ እና ከተደራጁ በኋላ ቀጣዩና ዋናው የምርጫ ትዝብት ትኩረት በየምርጫ ጣቢያዎች የሚደረግ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ትዝብት ነው። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሠማሩባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን፣ ሂደቱ መመሪያውን የተከተለ መሆኑን፣ እንዲሁም በድምፅ አሰጣጥ ወቅት የኮቪድ-19 መከላከያ መንገዶች ተግባራዊ መሆናቸውን እንዲሁም በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እና አካባቢ ስለነበረው የፀጥታ እና ደህንነት ሁኔታዎችን በመታዘብ መረጃ አሰባስቧል።

## የታዛቢዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን የመታዘብ መብት

ቦርዱ በኮቪድ-19 ምክንያት ከተጣሉ ገደቦች በስተቀር በሁሉም የምርጫው ሂደቶች ላይ ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እና በመዘዋወር መታዘብ ይችላሉ። በዚሁ መሠረት በሰኔው ምርጫ በ1,975 (94 በመቶ የሚሆኑ) የምርጫ ጣቢያዎች የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች አጠቃላይ ሂደቱን ያለምንም ገደብ ለመታዘብ ችለዋል። ይሁን እንጂ በ12 (1 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች ታዛቢዎች ከኮቪድ-19 ጋር ተያያዥነት በሌለው ምክንያት አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱን እንዳይታዘቡ ክልከላ ተደርጎባቸዋል። በተጨማሪም በ119 (6 በመቶ) አጋጣሚዎች የህብረቱ ታዛቢዎች ከኮቪድ-19 የመከላከል እርምጃ ጋር በተያያዘ ምክንያት የምርጫ ጣቢያውን በጊዜያዊነት ለቀው እንዲወጡ መደረጋቸውን ሪፖርት አድርገዋል። ኅብረቱ ሁሉም በቦርዱ ፈቃድ አግኝተው የተሰማሩ ታዛቢዎች በምርጫው ሂደት ላይ መሳተፍ አለባቸው ብሎ ቢያምንም በነበሩት ሁኔታዎችና በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ምክንያት ከኮቪድ-19 ጋር በተገናኙ ምክንያቶች ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያዎችን ለቀው እንዲሄዱ ሊደረጉ እንደሚችሉ አስቀድሞ ከግምት ማስገባቱ እዚህ ላይ ልብ ሊባል ይገባዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በመስከረም ወር በምርጫ ቦርድ ከታዛቢዎች መብት ጋር የወጡ ድንጋጌዎችን ባከበረ መልኩ ከኮቪድ-19 ምክንያቶች በስተቀር በየትኛውም ምክንያት ታዛቢዎች ምርጫ ጣቢያዎችን እንዲለቁ ያልተጠየቁ ሲሆን በ23 አጋጣሚዎች ግን ህብረቱ ለመስከረሙ ምርጫ ያሰማራቸው ታዛቢዎች ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የተነሳ ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ ተጠይቀው እንደነበር ሪፖርት አድርገዋል። ነገር ግን በሰኔ ወር በ12 ታዛቢዎች ሪፖርት ከተደረገው በተቃራኒ ከኮቪድ ጋር ባልተገናኙ ምክንያቶች የትኛውም ታዛቢ ከምርጫ ጣቢያ ለቆ እንዲወጣ እንዳልተጠየቀ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።

በምርጫ ቦርድ ሆነ በምርጫ ህጉ እውቅና ካልተሰጣቸው ህገወጥ ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያ መገኘት ጋር በተያያዘ ምንም እንኳን በሰኔ እንዲሁም በመስከረም ወር የተሰማሩ አብዛኞቹ ታዛቢዎች (96 በመቶ ለሰኔ፣ ከ99 በመቶ በላይ ለመስከረም) ህገወጥ ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያው እንዳልነበሩ ሪፖርት ቢያደርጉም የተወሰኑ ታዛቢዎች (81 ታዛቢዎች በሰኔው ምርጫ፣ 4 ታዛቢዎች በመስከረሙ ምርጫ) በአንፃሩ ህገወጥ ግለሰቦችን በጣቢያዎች ውስጥ እንደተመለከቱ ሪፖርት አድርገዋል።

## ድጋፍ ለሚሹ መራጮች ቅድሚያ እና ተገቢውንተገቢውን ድጋፍ ስለመስጠት

ሁሉም ዜጎች እና የማህበረሰብ ክፍሎች በምርጫ ሂደቱ ላይ እንዲሳተፉ ለማስቻል ድምፅ ለመስጠት የሌሎችን ድጋፍ ለሚሹ መራጮች ቅድሚያ በመስጠት እና ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በፈለጉት ሰው ድጋፍ እንዲያገኙ ተፈቅዷል።[28] አብዛኞቹ (98%) የሚሆኑት ታዛቢዎች የአካል ጉዳተኞች ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው ዜጎች ቅድሚያ በመስጠት ድምጽ እንዲሰጡ እንደተደረገ እና በአብዛኞቹ ሁኔታዎች እነዚህ መራጮች (96 በመቶ%) እገዛ በሚያስፈልጋቸው ወቅት ራሳቸው በመረጡት ሰው እገዛ ያገኙ የነበረ መሆኑን ሪፖርት አድርገዋል። በሌላ በኩል ኅብረቱ ከታዘባቸው 9 በመቶ የሚሆኑ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ነፍሰ ጡር መራጮች እንዲሁም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ መራጮች ድጋፍ አግኝተዋል። በተጨማሪም፣ በሶማሌ ክልል በፋፋን የምርጫ ክልል በቆለጂ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች የመጠለያ ውስጥ በተደረገው የድምጽ መስጠት ሂደት የምርጫ ሥነ ሥርዓት ላይ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ እና ተበታትነው የሰፈሩትን መራጮች ተፈናቃዮች በምርጫው ሂደት በርካታ ድጋፍ የሚሹ መራጮች እንደነበሩ በስፍራው ተሰማርቶ ከነበረው የታዛቢዎች ቡድን ለመገንዘብ ተችሏል።

## የምርጫ ቦርድ ማኅተም ያረፈባቸው የምርጫ ወረቀቶች

ኅብረት ለምርጫ በሰኔ ወር በተደረገው ምርጫ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርት ካደረጉባቸው ከምርጫ ጣቢያዎች በ89 በመቶ (1,879) ያክሉ ለመራጮች የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ከመስጠታቸው በፊት የምርጫ አስፈጻሚዎች የቦርዱን ማኅተም አሳርፈዋል። በመስከረሙ ምርጫ አብዛኛዎቹ (95%) የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለመራጮች ከመታደላቸው በፊት በምርጫ አስፈጻሚዎች የቦርዱ ማኅተም እንዲያርፍባቸው ተደርገዋል። ነገር ግን ከዚህም በመነሣት በሰኔው ምርጫ የህብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው በ226 (11 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ለመራጮች የቦርዱ ማህትም ያረፈባቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶች መሰጠት በአግባቡ እንዳልተተገበረ ተመልክቷል፡፡ ይህ ቁጥር በመስከረም ምርጫ ወደ 5 በመቶ ቀንሷል።

## የመራጮች የጣት ላይ የማይለቅ ቀለም

ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ጉልህ ግኝት በሰኔ ምርጫ ወቅት በ366 (17 የምርጫ ጣቢያዎች) ላይ የማይለቅ የመራጭነት ቀለም በመራጮች ጣት ላይ ያልተደረገ መሆኑን ታዛቢዎች ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን፤ በመስከረም የድምጽ መስጫ እለትም 20 በመቶ ለሚሆኑ መራጮች የማይለቅ የጣት ቀለም ያልተደረገ መሆኑን የህብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሚስጥራዊነት

በሰኔው ምርጫ በ198 (10%) በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ምስጢራዊነት ሙሉ በሙሉ እንዳልተከበረ ለመረዳት ተችሏል። ይህ ተመሳሳይ ሁኔታ መስከረም 20 በተደረገው ምርጫ ወቅት ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች መካከል በ90 በመቶ በሚሆኑት የድምጽ አሰጣጥ የምርጫ ሂደት ምስጢራዊነትን ያከበረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ኅብረቱ ታዛቢዎችን ካሠማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በሰኔ 14 ምርጫ ወቅት በ2,073 (98%) እንዲሁም በመስከረም በ99 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ሣጥኖች (ኮሮጆዎች) በግልጽ የሚታይ ቦታ የተቀመጡ እንደነበረ ለመታዘብ ተችሏል፡፡

## የመራጮች መዝገብ

ቦርዱ ባስቀመጠው መመሪያ መሠረት በድምፅ መስጫ ቀን ድምፅ መስጠት የሚችሉት ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ የተገኘ መራጮች ብቻ ናቸው። ይሁን እንጂ ኅብረቱ ታዛቢዎችን ካሠማራባቸው ጣቢያዎች መካከል በሰኔ ምርጫ በ829 (39 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ስላልተገኘ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ የተደረጉ መራጮች ነበሩ። እንዲሁም በመስከረም ምርጫ በ114 (6%) የምርጫ ጣቢያዎች ስማቸው የመራጮች መዝገብ ላይ እያለ እንዳይመርጡ ተከልክለው ወደ ቤታቸው የተመለሱ ዜጎች እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል። መስከረም 20 በተደረገው ምርጫ በ9 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ቢያንስ አንድ መራጭ ስሙ የመራጮች መዝገብ ላይ ሳይኖር እንዲመርጥ የተፈቀደለት መሆኑን እና በ34 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ቢያንስ አንድ መራጭ የመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ እያለ እንዳይመርጥ የተከለከለ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ይህ

28 በኢትዮጵያ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 14/ 2013፤ አንቀጽ 26

ሁኔታ የአንድን ዜጋ ፖለቲካዊ መብቶች ከመንፈግ ጋር የሚገናኝ በመሆኑ አሳሳቢ ነው። እንፃራዊ በሆነ መልኩ የሕዝበ-ውሳኔ በተደረገባቸው ቦታዎች መሰል ችግር በ19 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች መከሰቱን የህብረቱ ታዛቢዎች ገልፀዋል።

## የምርጫ ጣቢያዎች መዝጊያ ሰዓት

በምርጫ ሕጉ መሰረት ቦርዱ የተለየ መመሪያ ካልተሰጠ በቀር የድምፅ መስጫ ጊዜ ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ ይጠናቀቃል። የህብረቱ ታዛቢዎች በሰኔ 14 ምርጫ ወቅት ባደረጉት ትዝብት ቦርዱ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ያራዘመ ሲሆን፤ ይህም ሁሉም መራጮች ድምፃቸውን እንዲሰጡ በማገዙ ኅብረት ለምርጫ በአዎንታዊ መልኩ ይመለከተዋል። በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ከምርጫ ቁሳቁሶች አቅርቦት ችግር ጋር በተያያዘ እስከሚቀጥለው ቀን ተራዝሟል። በመስከረሙ ምርጫ ሰልፍ ይዘው ሲጠባበቁ የነበሩትን መራጮች ድምፅ መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ ሲባል ቦርዱ በሐሐረሪ ክልላዊ መንግሥትና የሕዝበ-ውሳኔ በተሰጠባቸው አካባቢዎች የድምፅ መስጫ ሰዓቱን (ከምሽቱ 12 ሰዓት ወደ ምሽቱ 2 ሰዓት) በሁለት ሰዓታት አራዝሟል። ይህ በቦርዱ የተወሰደው ውሳኔ አበረታች እና ዜጎች ድምፅ የመስጠት መብታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም በበርካታ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ይህ ሁኔታ በድምፅ አሰጣጡና ቆጠራው ሂደት ላይ መስተጓጎልን ከመፍጠሩ ባሻገር በሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ዘንድ የቆጠራውን ሂደት በተመለከተ የሚያስፈልገውን መረጃ በማግኘት ላይ ተግዳሮት ሆኖባቸዋል።

# የድምፅ ቆጠራው ሂደት

የድምፅ ቆጠራ እጅግ ወሳኝ እና ጥንቃቄ ከሚሹ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። የምርጫ ሕጉ የድምፅ ቆጠራ ስለሚከናወንበት ሂደት ዝርዝር ድንጋጌዎች ያሉት ሲሆን የድምፅ ቆጠራው የሚከናወነው በግልጽ እና ሁሉም ታዛቢዎች በተገኙበት መሆን እንዳለበት በግልጽ ይደነግጋል።[29] በተጨማሪም የድምፅ ቆጠራ የሚደረገው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ምርጫው በተከናወነበት ጣቢያ ውስጥ መሆን አለበት።[30] የድምጽ ቆጠራን በምርጫ ክልል ለማከናወን የመወሰን ስልጣን ለምርጫ ክልሉ ወይም በምርጫ ክልሉ ለተመረጠ የምርጫ አስፈጻሚ ተሰጥቷል።[31] የድምፅ ቆጠራው በማንኛውም ቦታ በሚደረግበት ወቅት የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ ዕጩ ወኪሎች፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እንዲገኙ ይጠበቃል።

## የድምፅ ቆጠራውን ሂደትን መታዘብ

ቦርዱ ባስቀመጠው መመሪያ መሠረት በሰኔ 14ቱ ምርጫ በ1,983 (95%) የምርጫ ጣቢያዎች በድምፅ ቆጠራ ሂደት ወቅት የህብረቱ ታዛቢዎች በጊዜያዊነት ለቀው እንዲወጡ በምርጫ አስፈጻሚዎች አልተጠየቁም። በመስከረም 20 ምርጫ ታዛቢዎች ከተሰማሩባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በ85 በመቶ የሚሆኑት የተዘጉት ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ 1 ሰዓት ባለው መካከል መሆኑን እና 15 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ከምሽቱ 1 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው መካከል የተዘጉ መሆናቸውን ከትዝብት ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል። በመስረከም 20 ምርጫ 19 (2%) ታዛቢዎች ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ ምክንያት ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ የተጠየቁ ሲሆን 98 በመቶ የሚሆኑት የቆጠራ ሂደቱን መታዘብ ችለዋል።

## በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የተደረጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቶች

ከህብረቱ ታዛቢዎች በተገኘ የትዝብት ሪፖርት መሰረት በሰኔ ምርጫ ወቅት በ2043 (99%) የምርጫ ጣቢያዎች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ የተሰጡ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ወዲያው የምርጫ ሁደቱ እንዳለቀ የተቆጠሩ ሲሆን፤ እንዲሁን መሆኑን እና በ1,927 (93 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ለየክልል ወይንም ለከተማ ምክር ቤት የተሰጡ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቆጠራ ወዲያውኑ ተከናውኗል። በሌላ በኩል በመስከረም 20 ምርጫ ወቅት በ95 መቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ የተከሄደው ወዲያው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት እንደተጠናቀቀ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

29 የኢትዮጵያ የምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/ 2011፣ አንቀጽ 57

30 ዝኒ ከማሁ

31 ዝኒ ከማሁ

## የድምፅ አሰጣጥ ሂደት መቋረጥ

በሰኔው ምርጫ የድምጽ መስጫ እለት በ20 (1%) በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የድምፅ ቆጠራ ተቋርጧል። በተመሳሳይ መልኩ በመስከረም 20 ምርጫ ወቅት 99 በመቶ የሚሆኑት የህብረቱ ታዛቢዎች የድምፅ ቆጠራ ከተጀመረ በኋላ ሂደቱ እንዳልተቋረጠ፣ ጣልቃ ገብነት፣ ማስፈራራት ወይንም ትንኮሳ በዚህ ወቅት አለመኖሩን ሪፖርት አድርገዋል። በአንድ አጋጣሚ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ የድምፅ መስጫ ጣቢያ ኃላፊዋ በድምፅ ቆጠራ ሂደት ወቅት ባጋጠማት ከፍተኛ የጤና እክል ቆጠራው ለአንድ ሰዓት ያህል የተቋረጠ ሲሆን በሌላ አጋጣሚ ደግሞ በከባድ ዝናብ አማካኝነት የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ተቋርጦ ነበር። በቆጠራ ወቅት ያጋጠመ ጣልቃ ገብነት፣ ሁከት፣ ወይም ማስፈራራት ችግር በተመለከተ በሁለት የህብረቱ ታዛቢዎች ብቻ ሪፖርት የቀረበ ሲሆን ከታዛቢዎች መካከል አብዛኛዎቹ (99 በመቶ) ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት፣ ሁከት ወይም ማስፈራራት እንዳላጋጠማቸው ሪፖርት አድርገዋል።

## የውጤት እና የማመሳከሪያ ቅጽ

የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያሳየው በአማካይ አራት የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች በድምጽ ቆጠራ ሂደት የተገኙ ሲሆን፣ በ297 (14 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በድምፅ ቆጠራ ማመሳከሪያ ቅጽ ላይ ለመፈረም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በቦርዱ መመሪያ መሠረት፣ የድምፅ ቆጠራ ውጤት መግለጫ እና ማመሳከሪያ ቅጽ የድምጽ ቆጠራ በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ ለህዝብ ግልጽ በሆነ ቦታ መለጠፍ እንዳለበት ይደነግጋል። በዚህም መሠረት የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ከተገኙባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ568 (27 በመቶ) በሚሆኑ ምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ ከተጠናቀቀ ቡኃላ የውጤት እና የማመሳከሪያ ቅጽ ወዲያውኑ ከምርጫ ጣቢያዎች ውጪ አልተለጠፈም ነበር፡፡ ሆኖም ግን የህብረቱ አንዳንድ ታዛቢዎች ሪፖርት እንዳደረጉት በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ ውጤት በቀጣዩ ቀን ተለጥፎ ለሕዝብ ይፋ መሆናቸውን ተመልክተዋል።

# ሌሎች የትዝብት ግኝቶች

## በምርጫ ጣቢያዎች የሴት ምርጫ አስፈጻሚዎች ተሳትፎ

ሰኔ 14 በተደረገው ምርጫ በአማካይ 2 ሴት የምርጫ አስፈጻሚዎች በየምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እንደተገኙ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። በሌላ በኩል በ420 (20%) በሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ኃላፊዎች/ ሊቀመንበሮች/ ሴቶች እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ በመስከረም ምርጫ ከምርጫ አስፈጻሚዎች መካከል 37 በመቶዎቹ ሴቶች ነበሩ።

ከዚህም በተጨማሪ ቦርዱ በየምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ ሴት የምርጫ አስፈጻሚ እንዲኖር ቢደነግግም፣ 11 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ሴት የምርጫ አስፈጻሚዎች እንዳልነበሩ የህብረቱ የትዝብት መረጃ ያመለክታል። በአጠቃላይ 23 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ሴት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች እንደነበሩ ለመገንዘብ ተችሏል።

## በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት ስለተከናወነ የምርጫ ሂደት

በምርጫው ሂደት ወቅት የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል የተደረጉ ጥንቃቄዎችን መገምገም ኅብረቱ ትኩረት ከሰጠባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነበር። በመሆኑም በድምፅ ሰጪዎችና በምርጫ አስፈጻሚዎች ዘንድ የኮቪድ-19 የጥንቃቄ ርምጃዎችን በማክበር ረገድ ያለውን ሁኔታ ለመለካት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ታዝቧል።

የኅብረቱ ታዛቢዎች ካሰባሰቡት መረጃ በመነሣት በ601 (28 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛዎችን በምርጫው ዕለት ሙሉ በሙሉ አልተጠቀሙም። ይህ ቁጥር በመራጮች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ አሻቅቧል። እንደዚሁም የመራጮችን ስንመለከት፣ በ1,312 (62 በመቶ) የምርጫ ጣቢያዎች መራጮች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ሙሉ በሙሉ እንዳላደረጉ ከትዝብት ሪፖርቱ ለመረዳት ተችሏል። ቦርዱ አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ ያደረጉ ዜጎች መምረጥ እንደሚችሉ ቢያሳውቅም፣ 84

(4 በመቶ) በሚሆኑ  የምርጫ ጣቢያዎች መራጮች መደበኛውን የፊትና የአፍንጫ መሸፈኛ (ጭምብል) ጭንብል ባለማድረጋቸው ምክንያት ድምጽ እንደይሰጡ (እንዳይመርጡ) ተደርገዋል፡፡
ከታዛቢዎች  ሪፖርት ላይ ለመረዳት እንደተቻለው የምርጫ ጣቢያዎች በውጪም ሆነ በውስጥ የኮቪድ ፕሮቶኮልን ማለትም አማካይ አካላዊ ርቀትን በጠበቀ መልኩ የተደራጀ መሆኑን ያሳያል። ከዚህም ውስጥ 89 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች መራጮች በሚሰለፉበት ወቅት ተገቢውን ርቀት እንዲጠብቁ ሁኔታዎች የተመቻቹ ሲሆን 96 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ መራጮች ወደ የምርጫ ጣቢያው ከገቡ በኋላ ተገቢውን አካላዊ ርቀት እንዲጠብቁ ቁጥጥር ይደረግ እንደነበረ ለመረዳት ተችሏል።

በመስከረም 20 ምርጫን ወቅቱ በተመለከተ 72 በመቶ በሚሆኑት ኅብረቱ በታዘባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛዎችን በድምፅ አሰጣጡ ሂደት ወቅት ሙሉ በሙሉ ያደረጉ ሲሆን 27 በመቶ የሚሆኑት መራጮች ደግሞ በከፊል ማድረጋቸው ሪፖርት ተደርጓል። በተመሳሳይ ኅብረቱ መራጮች የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ወይንም አለማድረጋቸውን የታዘበ ሲሆን፤ ትዝብት ከተደረገባቸው 34 በመቶ በሚሆኑት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ድምፃቸውን ከሰጡ መራጮች መካከል በሁሉም ሰዓት የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ እንዳደረጉና 55 በመቶ የሚሆኑት መራጮች በምርጫው ሂደት የተወሰኑ ጊዜያት እንዳላደረጉ ኅብረቱ ተገንዝቧል። በሌላ መልኩ ከሪፖርቱ 12 በመቶ የሚሆነው የሚያሳየው በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ መራጮች የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብሎችን አላደረጉም። በመጨረሻም የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛን በተመለከተ ቦርዱ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ አለማድረግ መራጮችን ድምፅ እንዳይሰጡ መከልከያ ምክንያት አለመሆኑን መግለጹ ይታወቃል። በእነዚህ ሁኔታዎች መራጮች አፍ እና አፍንጫቸውን በማንኛውም ዓይነት ጨርቅ (አፍንጫን በአግባቡ የሚሸፍን ሌላ የፊት መሸፈኛ) ማድረግ ከቻሉ ድምፃቸውን መስጠት ይችላሉ። ሆኖም ኅብረቱ የሰበሰባቸው ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት 7 በመቶ በሚሆኑት ምርጫ ጣቢያዎች ለመምረጥ የሄዱ መራጮች ምንም እንኳን መደበኛ ከሆነው የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ውጭ ያሉ የጨርቅ መሸፈኛዎችን ቢያደርጉም፤ መደበኛውን የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ (የሰርጂካል ማስክ) ባለማድረጋቸው ድምፃቸውን እንዳይሰጡ መከልከላቸውን ታዝቧል፡ ፡ ህብረቱ ይህ ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ያምናል።

## የፓርቲ ወኪሎች እና በምርጫ ጣቢያ የቀረቡ ቅሬታዎች

የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በምርጫ ዕለት በተሠማሩባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ 3 የፓርቲ ወኪሎች የተገኙ ሲሆን፤  የህብረቱ ትዝብት ሪፖርት እንደሚያሳየው በመስከም 20 የምርጫ ቀን በየምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ አንድ ቅሬታ እንደቀረበ ያሳያል። በሰኔ 14ቱ የድምጽ መስጫ ቀን በአማካይ በየምርጫ ጣቢያዎች ስድስት ቅሬታዎች የነበሩ ሲሆን፣ ከዚህ አንፃር በመስከረሙ ምርጫ የቀረቡት ቅሬታዎች ቁጥር አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ኅብረቱ አሰማርቷቸው ከነበሩ አንዳንድ ታዛቢዎች ጋር ባደረገው የስልክ ውይይቶች እንደተረዳው ብዛት ባላቸው የድምፅ ምርጫ ጣቢያዎች ሲቀርቡ የነበሩ ቅሬታዎችን እዚያው በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ተቋቁመው በነበሩ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች እልባት እንደተሰጣቸው ተገንዝቧል።

# የድኅረ - ምርጫ ትዝብት

## መግቢያ

የድኅረ ምርጫ ከባቢ ሁኔታ በአንድ ምርጫ ሂደት ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ድምጽ መስጠትን ተከትሎ የሚኖሩ የምርጫ ውጤት አገላለጽ እና የመራጭች ግብረ መልስ (አስተያየት)፤ የቅሬታ ስነ ስርዓት ውጤታማነት፤የቅሬታ አቀራረብ እና እነዚህን ቅሬታዎች ተቀብለው የሚያዩት የምርጫ አለመግባባቶችን የሚዳኙ የፍርድ ቤቶች አወቃቀር፣ የፀጥታ እና ደህንንነት ሁኔታ እንደዚሁም የሲቪክ ምህዳር ሁኔታዎች ወዘተ ከድህረ ምርጫ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጠቃሚ ጉዳዮቸ ናቸው። ኅብረቱ የሰኔውን እና የመስከረሙን ምርጫ ተከትሎ ምርጫ በተከናወነባቸው ስምንት ክልሎች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች በድምሩ 147 ታዛቢዎች ( 97 በሰኔ ምርጫ እና 50 የመስከረም ምርጫ) ማግስት የድህረ ምርጫ ታዛቢዎችን አሰማርቷል፡፡ እነዚህ ታዛቢዎች ከሰኔ 15 2013 እና ከመስከረም 20 2014 ጀምሮ የድኅረ ምርጫ መረጃዎችን ያሰባሰቡ ሲሆን  ህብረቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የድህረ ምርጫ አጠቃላይ ሁኔታዎች እና ያሳሳቢ ሁነት መከታተያ ቅጾችን በማዘጋጀት ታዛቢዎችን አሰማርቷል። ታዛቢዎች የድምጽ መስጫ ዕለትን ተከትለው የነበረውን የጸጥታና የደህንነት ሁኔታ፣ በምርጫው ውጤት ላይ የማህበረሰቡ ምላሽ እና በሲቪክ ምህዳር ላይ የተደረጉ ገደቦች እና መሰል ሁኔታዎችን ተከታትለዋል።

ኅብረቱ ከምርጫው ማግስት አንስቶ ለሶስት ተከታታይ ሳምንታት በሁለቱም የምርጫ ወቅቶች በድምሩ 855 የድህረ ምርጫ ሪፖርቶች (568ቱ ከሰኔ ምርጫ በኋላ የተቀሩት 287 ሪፖርቶች ደግሞ ከመስከረሙ ምርጫ) አሰባስቧል። ይህም መንግሥት በድኅረ ምርጫ ወቅት የሲቪክ ማኅበረሰብ ከዜጎች ጋር በመገናኘት ስለ ምርጫው አንዳንድ ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ እና ግብረ መልሶችን እንዳያቀርቡ የሚደረግባቸውን ገደብ ለመገምገም ነው። የሚከተሉት የድህረ ምርጫ ግኝቶች ከታዛቢዎች በተገኙ መረጃዎች፣ እና የመገናኛ ብዙኃንና የሚዲያ ክትትል ቡድን፣ ከሌሎች ታዛቢ ቡድኖችና በጥናት በተሰባሰቡ የምርምር ሪፖርቶች የተደገፉ ናቸው።

## የምርጫ ውጤት አገላለጽ እና የኅብረተሰቡ ምላሽ

ቦርዱ የምርጫውን ውጤት በ20 ቀናት ውስጥ የመግለጽ ግዴታ ያለበት ሲሆን፤ የሰኔው 14ቱን የምርጫ ውጤት ሐምሌ 3 ቀን 2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ በተገኙበት ይፋ አድርጓል። የመስከረም 20/ 2014ቱን ውጤትን በተመለከተ ቦርዱ የሐረሪ፣ የሶማሌ እና የደቡብ ክልል ውጤትን የገለጸው ጥቅምት 2/ 2014 ዓ.ም ነው። በቦርዱ ሪፖርት መሠረት በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳደሮች በመራጭነት ከተመዘገቡት ዜጎች መካከል 90በመቶ የሚሆኑት በድምጽ መስጫ ዕለት ድምጽ መስጠታቸውን፤ ነገር ግን በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከተመዘገቡት መራጮች መካከል 55 በመቶ ብቻ ድምፅ እንደሰጡ የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ ገዢ ፓርቲ የሆነው የብልጽግና ፓርቲ በከፍተኛ ድምፅ ያሸነፈ ሲሆን ከአጠቃላይ 425 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎች ውስጥ በሰኔ ምርጫ 410 መቀመጫ እንደዚሁም በመስከረም ምርጫ ደግሞ ከ47 መቀመጫዎች 44ቱን እንዳሸነፈ ከቦርዱ ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል። አብን 5፣ ኢዜማ 4 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎችን በሰኔ ምርጫ ያሸነፉ ሲሆን የጌዲኦ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት በሰኔው ምርጫ 2 መቀመጫዎችን፣ እንደዚሁም በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የተወዳደሩ የግል ተወዳዳሪዎች 4 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎችን ማሸነፍ ችለዋል።
የህብረቱ ታዛቢዎች ከሰበሰቡት የድኅረ ምርጫ መረጃዎች በመነሣት በሰኔ ምርጫ ወቅት ከቀረቡት 509 (90 በመቶ) ድኅረ ምርጫ ሪፖርቶች የምርጫ ውጤቱ አስቀድሞ የተገመተው ዓይነት መሆኑን፤ 568 (92 በመቶ) ዜጎች ደግሞ በድምፅ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደቱ ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ እና ቅሬታ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ የመስከረም 20 2014 ዓ.ም ውጤትን በተመለከተ፤ አብዛኞዎቹ ዜጎች በምርጫው ሂደት የረኩ መሆናቸውን የህብረቱ ታዛቢዎች ገልጸዋል።

## የድኅረ ምርጫ ድባብ

በድኅረ ምርጫ ወቅት የአሸናፊዎች እና ተሸናፊዎች ውጤት መገለፅን ተከትሎ የፀጥታ ችግሮች መከሰት የተለመደ ነው። በዚህም መሠረት የኅብረቱ ታዛቢዎች የሰኔ እና መስከረም ምርጫዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው የተሰጉ የፀጥታ ችግሮች ወይም አመጽ እንዳልነበረ፤ ቢኖርም እንኳን በጣም አነስተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የኅብረቱ ታዛቢዎች ከሰበሰቡት መረጃ በመነሣት የሰኔ ምርጫን ተከትሎ የድኅረ ምርጫ ትዝብት በተደረገባቸው ቦታዎች ከተሰበሰቡ 568 ሪፖርቶች (99 በመቶ) በድምፅ መስጠት ሂደቱ ላይ እና ከምርጫ ውጤት መታወቅ ጋር የተያያዘ ምንም ዓይነት ረብሻ ወይንም ሁከት ያልተከሰተ ሲሆን፤ የምርጫ ውጤት ከተገለጸም በኋላ ከታዛቢዎች ከተሰበሰቡ 98% ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት የሰኔውን ምርጫ የውጤት ማሳወቅን ተከትሎ ውስጥ በፖለቲካ ፓርቲዎች የተቀሰቀሰ ረብሻ ወይንም ሁከት የሌለ መሆኑን እና የተጠራ ሰላማዊ ሰልፍ አለመኖሩ ታውቋል። በተመሳሳይ መልኩ የመስከረም 20/2014ን ምርጫ ውጤትን ተከትሎ በነበረው የምርጫ ውጤት ማሳወቅ በሐረሪ፣ ሶማሌ እና ደቡብ ክልሎች ውስጥ በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይንም ደጋፊዎቻቸው መካከል የተነሣ ረብሻ ያልነበረ እና የተጠሩ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎች ያልነበሩ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። በተጨማሪም ከሰኔው እና ከመስከረም ምርጫዎች ውጤት ጋር በተያያዘ በሰው ሕይወት እና በንብረት ላይ ጉዳት ያደርሱ ምንም ዓይነት አጋጣሚዎች እንዳልነበሩ የታዛቢዎቹ ሪፖርቶችት ያሳያሉ። በመሆኑም ኅብረቱ ምንም ዓይነት የሕዝብ ንቅናቄዎችን፣ ዐመፆችን ወይም ሰላማዊ ሰልፎችንም ሆነ ሁለቱንም ምርጫዎች ተከትሎ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አካባቢ የታየበት አጋጣሚ አለመኖሩን ታዝቧል። ሆኖም ግን፣ ኅብረት ለምርጫ እዚህ ላይ እያመላከተ ያለው ግኝት የድህረ ምርጫ ታዛቢ አሰማርቶባቸው በነበረባቸው ጥቂት የምርጫ ክልሎች ውስጥ ከምርጫ ጋር በተያያዘ የተነሡ ግጭቶችን እንጂ አጠቃላይ የአገሪቱን የፀጥታ ሁኔታ በተመለከተ እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

# በምርጫው ውጤት ላይ የህብረተሰቡ ግምት

ምንም እንኳን ቀደም ብሎ አንዳንድ ሚዲያዎች የምርጫ ውጤት ማኅበረሰቡ የጠበቀው ነው በማለት የዘገቡ ቢሆንም የህብረቱ የድህረ-ምርጫ ታዛቢዎች ያከናወኑት ትዝብት እንደሚያሳየው የምርጫው ውጤት ዜጎች ከጠበቁት ውጤት ጋር የሚጣጣም እንዳልሆነ ነው። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ የህብረቱ የድህረ-ምርጫ ታዛቢዎች ከሰበሰቡት መረጃ በመነሣት 90 በመቶ የሚሆኑት ሪፖርቶች ዜጎች  በምርጫስ ውጤት ላይ ጥርጣሬ እንደሌላቸው እና ሚዲያው የሚያሠራጨው መረጃ ውሸት እና የተጋነነ እንደነበር ገልጽዋል። ይህም እውነታ የህብረቱ ታዛቢዎች መረጃ ከሰበሰቡባቸው 91 በመቶ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ ውጤት ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት ቅሬታ አለማቅረባቸውን የሚያጠናክር ነው።

የመስከረሙን ምርጫ ተከትሎ የተሰበሰቡት ሪፖርቶች የምርጫውን ውጤት በተመለከተ ሕዝቡ ይገኛል ብሎ ይጠብቅ የነበረውን ውጤት ቦርዱ ካሳወቀው ምን እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆንም ይህም ከትክክለኛው የምርጫው ውጤት ጋር የሚስማማ ነው።   የመስከረም ምርጫ ውጤትን ተከትሎ 249 (87 በመቶ) መልስ ሰጪዎች የምርጫው ውጤት የጠበቁት ቢሆንም ነገር መሆኑን ሆኖም ግን 7 ሪፖርቶች (2 በመቶ) ደግሞ በተገለጸው የምርጫ ውጤት ላይ ዜጎች ጥርጣሬ ያላቸውን መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የመስከረም 20 የምርጫ ውጤትን ተከትሎ 97 በመቶ መልስ ሰጪዎች በምርጫ ውጤት ላይ ጥርጣሬ እንደሌላቸው የገለጹ ሲሆን ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ በ2 አጋጣሚዎች (1 በመቶ) ደግሞ የምርጫው ውጤት ቅቡል እና ፍትሐዊ ሕጋዊ እና ፍትሐዊ እንዳልሆነ ይገልጻሉ።

# የሲቪክ ምህዳር

በምርጫ ሂደት እና በዲሞክራሲ ግንባታ ሂደት ውስጥ አስቻይ የሲቪክ ምህዳር መኖሩ አስፈላጊ ነው።  ይህንን ወሳኝ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት የድህረ ምርጫው ሁኔታዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለጋዜጠኞች፣ ለምርጫ ታዛቢዎች፣ ለዜጎች እንዲሁም ለሚዲያ አስቻይ መሆናቸውን ይዳስሣል።  የኅበረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት ባደረጉት መሠረት ከምርጫው ጋር በተያያዘ የሲቪክ ማህበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ ዕጩ ተፎካካሪዎች በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ የተደረገባቸው የጐላ ገደብ እንደሌለ አመላክተዋል። ይሁን እንጂ ኅብረቱ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መታሰራቸውም የሚያስረዱ 6 ሪፖርቶች ደርሰውታል። በተመሳሳይ የሰኔ ምርጫን ተከትሎ ጥቂት ጋዜጠኞች እና ዜጎች መታሠራቸውን ለማወቅ ተችሏል። በሌላም በኩል ኅብረቱ ከደረሱት ሪፖርቶች 1 በመቶ ያህሉ በድኅረ ምርጫ ወቅት በብሮድካስት እና በኅትመት ሚዲያዎች ላይ የሳንሱር ቁጥጥር እንደነበረ ያስረዳሉ። በሌላ በኩል የመስከረም 20 ምርጫን ተከትሎ በሲቪል ማኅበራት፣ ጋዜጠኞች እና ፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ላይ የተጣለ የጎላ ገደብ አልነበረም።

# በድኅረ ምርጫ የቀረቡ ቅሬታዎች

ኅብረት ለምርጫ በድኅረ ምርጫ ወቅት ትኩረት ያደረገባቸውና የትዝብቱ አካል ካደረጋቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ  በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይንም በዕጩዎች የሚቀርቡ መደበኛ ቅሬታዎች መኖር አለመኖራቸውን ነበር። የሰኔ 14 ምርጫን ተከትሎ ኅብረቱ ከደረሱት የሚሆኑት ሪፖርቶች 91% (515 ሪፖርቶች) የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ዕጩዎች መደበኛ ቅሬታ ያላቀረቡ መሆናቸውን ሲገልፁ፤ ሲሆን በ40 ሪፖርቶች (7 በመቶ) በየፖለቲካ ፓርቲዎች እና ዕጩዎች ቅሬታ ያቀረቡ መሆናቸውን ገልፀዋል። የመስከረም 20 ምርጫን ስንመለከት፤ በ92 በመቶ የሚሆኑት ሪፖርቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ዕጩዎች ቅሬታ ያላቀረቡ መሆናቸውን ሲገልፁ፤ 2 በመቶ ሪፖርቶች ተቃውሞዎች መቅረባቸውን ገልጸዋል።

የምርጫ ቀን እና የውጤት መገለጽን ተከትሎ የቀረቡ ቅሬታዎችን በተመለከተ የህብረቱ ታዛቢዎች ባደረጉት ትዝብት ግምገማ የሰኔ ምርጫን ተከትሎ በአብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ደረጃ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያልተቋቋመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በምርጫ ክልል አካባቢ እና በክልል ደረጃ የተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በአግባቡ ሥራ ላይ ያልነበሩ መሆናቸውን ታዝቧል።  የምርጫ ቦርድ በማዕከል ደረጃ  በአዲስ አበባ በሚገኘው ስካይ ላይት ሆቴል ያደረገውን የቅሬታ አሰማም ሂደትን ኅብረቱ ታዝቧል። የኅብረት ለምርጫ

ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ ከፍተኛ የመግባቢያ ቋንቋ ችግር የነበረ መሆኑን እና በአንዳንድ ሁቤታዎች ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይንም ተፎካካሪዎች ቅሬታቸውንና ምስክሮችን እንዳያሰሙ የስልክ ኔትዎርክ ችግር እንደነበረ ታይቷል። ኮሚቴው የሚሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ ቅሬታ አቅራቢዎች የይግባኝ አቤቱታቸውን በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለመቻላቸውና በዚህም ምክንያት በርካታ ቅሬታዎቻቸው ውድቅ መደረጋቸውን ኅብረቱ ታዝቧል።




“ በደቡብ ክልል፣ በጌዲዮ ዞን ያሉ ሕብረት ለምርጫ ያሰማራቸው ታዛቢዎች የምርጫ ትዝብት ስልጠናን ከወሰዱ በኋላ




“የኢትዮጵያ ሚዲያ ማህበር አስተዳደር የበላይ ጠባቂዎች፣ የሕብረት ለምርጫ የሚዲያ ቁጥጥር ማዕከልን በመጎብኘት ላይ

# መደምደሚያና ምክረ- ሐሳቦች

## መደምደሚያ

የስድስተኛው የኢትዮጵያ አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት በሁለት ዙሮች ተከናውኗል። ሰኔ 14/ 2014 ዓ.ም የተካሄደው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤቶች ድምፅ አሰጣጥ በአፋር፣ አማራ፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግሥታት እንዲሁም በአዲስ አበባና በድሬ ዳዋ የከተማ አስተዳደሮች ተካሂዷል። ከሦስት ወራት በኋላ መስከረም 20/ 2014 ዓ.ም የተካሄደው ለለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤቶች ድምፅ አሰጣጥ በሐረሪ እና ሱማሌ ክልላዊ መንግሥታት እንዲሁም ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በከፊል ተካሂዷል። የመስከረም ወር ከተካሄዱ ምርጫዎች በተጨማሪም ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ (አዲስ አበባና ድሬ ዳዋን ጨምሮ) የተካሄደ ድምፅ አሰጣጥን እነዲሁም በደብብሕ ክልላዊ መንግሥት የተካሄደውን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕዝበ ውሳኔን ያጠቃለለ ነበሩ።

በአጠቃላይ ምርጫዎቹ ሰላማዊ እና የተሻሻሉትን የምርጫ ሕጎችን የተከተሉ ነበሩ። ሆኖም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኩል በቂ ዝግጅት አለመደረጉ፣ በአገሪቱ ውስጥ ያጋጠሙ የጸጥታ እና የደኅንነት ችግሮች፣ እና ሌሎች ክልል ተኮር እና አገር አቀፍ ችግሮች በ2013 እና 2014 ዓ.ም በተካሄዱት ምርጫዎች ላይ ጉልህ ተጽእኖ አሳድረዋል። ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በመጋቢት እና ግንቦት ወራት 2013 ዓ.ም ያካሄደውን የመራጮች ምዝገባ ተከትሎ 38,234,910 መራጮችን መመዝገቡን ሪፖርት አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪም ቦርዱ በመስከረም ወር በተካሄዱት መደበኛ ምርጫዎች ላይ 6,562,534 ዜጎች መሳተፋቸውን እነዲሁም ተጨማሪ 1,344,622 ዜጎች በተመሳሳይ ቀን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የሕዝበ ውሳኔ ላይ መሳተፋቸውን ሪፖርት አድርጓል።

እነዚህን ምርጫዎች ተከትሎ የብልጽግና ፓርቲ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን አብዛኛውን መቀመጫዎች አንዲሁም የሁሉንም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ምክር ቤቶች መቀመጫዎችን አሸንፏል። ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ሲል በደብብሕ ክልላዊ መንግሥት ሥር ይተዳደሩ በነበሩ በአምስት ዞኖች እና አንድ ልዩ ወረዳ በመስከረም ወር የተካሄደውን የሕዝበ ውሳኔ ድምፅ አሰጣጥን ተከትሎ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ዐሥራ አንደኛው የኢትዮጵያ ፌደሬሽን ክልል ሆኖ ተቋቁሟል።

## ምክረ- ሐሳቦች

የስድስተኛውን አጠቃላይ ምርጫ ሂደት በነበሩት ቅድመ ምርጫ፣ በድምፅ መስጫ ቀን እና በድኅህረ ምርጫ ወቅት የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ ዜእጎችን በምርጫ ታዛቢነት አሠልጥኖ በአገሪቱ በሚገኙ የምዝገባ ማዕከላት ፣ በድምፅ መስጫ ጣቢያዎችና በምርጫ ክልሎች አሠማርቶ የመርጫውን ሂደት ታዝቧኋል። በምርጫው በቅድመ ምርጫ፣ በድምፅ መስጫ ቀን እና በድኅረ ምርጫ ተዝብቶቹ ባገኛቸው ግኝቶች ላይ በመመስረት ህብረቱ በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ወቅት የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫ ላይ ተሳታፊ ለነበሩ ባለድርሻ አካላት የሚከተሉትን ምክረ ሐሳቦች ያቀርባል።

### ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ (ኢብምቦ)

ስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ በተከናወነበት ወቅት ከፀጥታና ደህንነት እንዱሁም ከሎጂስቲክስ ጋር የተያያዙ ችግሮች የነበሩበት ቢሆንም ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ምርጫውን ለማካሄድ ያደረገውን ያላሳለሰ ጥረት እውቅና ሳይሰጥ ህብረቱ አያልፍም። ይህ እንዳለ ሆኖ ህብረቱ ከምርጫው ጎን ለጎን ባደረጋቸው የትዝብት ስራዎች ያገኛቸውን መረጃዎች በመንተራስ የሚከተሉትን ምክረ ሀሳቦች ለምርጫ ቦርድ አቅርቧል።

#### የምርጫ አፈፃፀም:

- ምንም እንኳ በአንድ አንድ የአገሪቱ ክፍሎች የመራጮች ምዝገባን ወይም የድምፅ መስጠት ሂደቱን ለማራዘም ምርጫ ቦርድ እንደተገደደ ህብረቱ ቢረዳም ቦርዱ እነዚህን ችግሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በመፍታት ምርጫን በተመሳሳይ ቀን ማከናወን እና በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ዜጎች

በምርጫ ሂደቱ ላይ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል በመስራት የተቆራረጡ የምርጫ ሂደቶችን ሊያስቀር እንደሚገባ ያምናል፤

- በምርጫው ላይ የሚሳተፉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት (ማለትም መራጮች፣ ዕጩዎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፣ አገር-በቀልና ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ ሚዲያ ወዘተ) በምርጫ ህግጋትና ደንቦች ዙሪያ በቂ እውቀት እንዲኖራቸውና በህጉ መሰረት በምርጫ ሂደቱ ላይ እንዲሳተፉ ለማስቻል ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ህግጋትን በወቅቱ ማውጣት እንዲሁም በአግባቡ ማሰራጨና ማስረፅ ይጠበቅበታል፣

- በምርጫው ላይ የሚሳተፉ ወይም የተለያዩ ተጓዳኝ ስራዎችን የሚሰሩ እንደመራጮች፣ እጩዎችና ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በምርጫ ትዝብት ወይም በምርጫ ትምህርት ላይ የተሰማሩ የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገቢውን ዝግጅት አድርገው በሁሉም የምርጫ ኡደቶች ላይ እንዲሳተፉ ለማስቻል ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳውን ከምርጫው በቂ ጊዜ አስቀድሞ ማውጣት ይጠበቅበታል። በተጨማሪም የሚወጣው የምርጫ ሰሌዳ ይፋ ከተደረገ በኋላ በተቻለ መጠን የምርጫ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲከናወኑ የሚችለውን ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅበት ህብረቱ ያምናል፣

- በማንኛውም የምርጫ ሂደት ወቅት በምርጫ ትዝብት ወይም በምርጫ ትምህርት ዙሪያ የሚሰሩ የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች ገንቢ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ለማስቻል የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እውቅና አሰጣጥ ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። በመሆኑም በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ወቅት የተስተዋሉ ክፍተቶች እንዳይደገሙ ለማስቻልና የእውቅና አሰጣጥ ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ የበለጠ የሰው ሀይልን መመደብ እንዲሁም በክልል ፅ/ቤት ደረጃ እውቅና የሚሰጥበትን አግባብ ማጤን ይኖርበታል ብሎ ህብረቱ ያምናል። በተጨማሪም ህብረቱ የእውቅና አሰጣጥ ስርዓቱን እና የሚወስደውን ጊዜ በግልፅ ማስቀመጥ የሚገባው ሲሆን በታዛቢዎች ማንነት ዙሪያ የሚጠይቀውን ጥያቄ ለአሰራር በሚመች መልኩ ማቅለል እንደሚጠበቅበት ህብረቱ ያምናል፣

- በአገሪቱ እየጨመረ ከመጣው የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ቁጥር ጋር በተያያዘ ህብረቱ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የተፈናቃይ ማህበረሰብ አባላትን ድምፅ የመስጠት መብት ከማስከበር አንፃር በሶማሊ ክልላዊ መንግስት በሚገኘው የቆሎጂ የአገር ውስጥ ተፈናቃዎች መኖርያ ካምፕ ያደረገውን የምርጫ ሂደት እንደበጎ ጅማሬ እውቅና ሊሰጥ ይወዳል። ህብረቱ ይህን መልካም ጅማሮ ምርጫ ቦርድ በቀጣይ ምርጫዎች ላይ አብልጦ እንዲሰራበት ጥሪውን የሚያቀርብ ሲሆን በተጨማሪም ከቆሎጂ ካምፕ በተጨማሪ በተለያዩ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ዜጎችን የመምረጥ መብት ለማስከበር የምርጫ ቦርዱ ሊሰራ እንደሚገባው ያምናል። በተጨማሪም የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ጨምሮ በልዩ ሁኔታ ድምፃቸውን በሚሰጡ ዜጎች ዙሪያ የወጡ ደንቦች ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በማረም ወደፊት በሚከናወኑ ምርጫዎች ላይ ምርጫ ቦርድ ወጥ አሰራርን ሊከተል ይገባል ሲል ህብረቱ ምክረ ሀሳቡን ያቀርባል፣

## የመራጮች የምዝገባ ማእከላት እና የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ዝግጅት

- የመራጮች ምዝገባ ማእከላት እና ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው መሠረት እንደሚዋቀሩና አገልግሎት እንደሚሰጡ ለማረጋገጥ እና የምርጫ ቁሳቁሶች በወቅቱ በምርጫ ጣቢያዎች እንዲደርሱ ለማስቻል የምርጫ የሎጂስቲክስ እቅዱን አስቀድሞ ማዘጋጀትና ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፣

- የመራጮችን፣ የምርጫ አስፈፃሚዎችን፣ የታዛቢዎችን፣ የእጩዎችንና በምርጫው ላይ የሚሳተፉ ሌሎች አካላትን እንዲሁም የተለያዩ የምርጫ ቁሳቁሶችን ደህንነት ለማስጠበቅ ያስችለው ዘንድ ብሄራዊ የምርጫ ቦርዱ ከሚገባቸው የፌደራል፣ ክልላና አካባቢያዊ የመንግስት መዋቅሮች በመቀዳጀት የተለያዩ ስራዎችን መስራት ይጠበቅበታል፣

- በአንድ የአገሪቱ ክፍል ወይም ክፍሎች ሊደረግ የሚገባውን ምርጫ ላለማካሄድ/ለማራዘም የሚወሰዱ ውሳኔዎች በህግ በተደነገጉ መስፈርቶች ላይ በመመስረትና ግልፅ በሆነ መልኩ ሊደረጉ የሚገባ ሲሆን በተቻለ መጠን እነዚህ ውሳኔዎች ከግጭት ወይም የደህንነት ስጋት አልያም ከድንገተኛ አደጋዎች አማካኝነት ብቻ ሊወሰዱ ይገባል። ህብረቱ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ምርጫ ባላካሄደባቸው ቦታዎች ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመከታተል ሁኔታዎች በሚፈቅዱበት ወቅት የድምፅ መስጠት ሂደቱን በእነዚህ ስፍራዎች ማከናወን ይኖርበታል ብሎ ያምናል፡፡

- የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም የማኅበረሰብ አባላት ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። የአካል ጉዳተኞች፣ ጨቅላ ህጻናት ልጆች ያሏቸው ሴቶች እና የአረጋውያንን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማረጋገጥና ለማሳደግ ብሄራዊ የምርጫ ቦርዱ የምዝገባ ማእከላትን እና የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን ለእነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማቋቋም እንደሚገባው ሕብረቱ ያምናል፤

- ስድስተኛው የኢትዮጵያ አገር አቀፍና የክልል ምርጫ የተካሄደው በአገሪቱ ዝናባማ (ክረምት) ወቅት ነበር። በዚህም የተነሣ የምዝገባ፣ ድምፅ አሰጣጥና የድምፅ ቆጠራ ሂደቱን በተሳለጠ ሁኔታ ለማካሄድ መጠለያ ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነበር። ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለሚቀጥሉት ምርጫወች ከየአካባቢው አስተዳደረር አካላት ጋር በጋራ በመሥራት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን ከዝናብ እና ፀሐይ መጠልል በሚያሰችሉ ቦታዎች ማቋቋም ይኖርበታል፡፡

- በቅርቡ የተከናወነው ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ የተከናወነው ከፍተኛ የጤና ስጋት በፈጠረውና በ2012 ዓ.ም አጋማሽ በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ወቅት መሆኑ የሚታወቅ ነው። ምንም እንኳን በመስከረም 2013 የአገሪቱ የጤና ሚኒስቴር ምርጫዎን የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ማከናወን እንደሚቻል ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ገልፆ የነበረ ቢሆንም በምርጫው ወቅት በምርጫ ቦርድ የተከናወኑ ተግባራት እና በምርጫ ኡደቱ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተከናወኑ የቅስቀሳና የመራጮች ትምህርት ስራዎች ቫይረሱን መከላከል በሚያስችል መልኩ እንዳልተደረጉ የትዝብት ግኝቶች ያሳያሉ። ምንም እንኳን የኮሮና ቫይረስ እስከ ቀጣዩ (ሰባተኛው) ምርጫ ይቆያል ብሎ መገመት ቢያዳግትም መራጮች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ታዛቢዎችና ሌሎች በምርጫው የሚሳተፉ አካላት ከማንኛውም የጤና ስጋት እንዲጠበቁ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የምርጫ ቦርድ ቅድመ ጥንቃቄዎችን ሊያደርግ እንደሚገባ ህብረቱ ሊያስታውስ ይወዳል።

## የምርጫ ቁሳቁሶችና አስፈጻሚዎች ኀላፊዎች

- በሰኔ ወር በተካሄው የድምፅ መስጠት ሂደት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከገጠሙት ተግዳሮቶች አንዱ የሎጅስቲክስ ችግር ነበር። ቦርዱ ይህን ችግር በመስከረሙ ምርጫ ወቅት ለማስተካከል ላደረገው የተሳካ ጥረት ህብረቱ እውቅና እየሰጠ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የመራጮች ምዝገባና የምርጫ ቀንን ጨምሮ በሁሉም የምርጫ ሂደቶች ትክክለኛና በቂ የምርጫ ቁሳቁሶች መሠራጨታቸውን ለማረጋገጥ በሎጂስቲክስ ረገድ ራሱን ሊያጠናክር እንደሚገባ ህብረቱ ያምናል፣

- በመራጮች ምዝገባ ወቅት በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተላለፈውን የጊዜ ማራዘም ውሳኔ ተከትሎ በምርጫ ምዝገባ አስፈፃሚዎች ክፍያ ዙሪያ በተፈጠሩ ክፍተቶች የተነሳ ቦርዱ የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙት ሲሆን በዚህም የተነሳ በአንዳንድ አካባቢዎች የተሰማሩ አስፈፃሚዎች ክፍያ እስከሚፈፀም የምዝገባ ሂደቱን ለማከናወን ፈቃደኛ እንዳልሆኑ በመግለፅ ምዝገባውን አቋርጠው ነበር። ይህ ድርጊት በምዝገባ ሂደቱ ወጥነትና ጥራት ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር እንደመሆኑ መጠን ምርጫ ቦርድ የተሻሉ የክፍያ ስርዓቶችን በመዘርጋት አስፈፃሚዎች ስራቸውን በአግባቡ የሚሰሩበትን ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅበታል፣

- ምንም እንኳን በስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ወቅት በአብዛኛው በቂ የሚባሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች በምርጫ ጣቢያዎች የተገኙ ቢሆንም በመራጮች ምዝገባና በምርጫ ቀን የፅጥታ አካላት (በምርጫ ህጉ የተቀመጡት ሁለት የፀጥታ አካላት) እና የኮቪድ-19 ባለሙያዎች በምርጫ ጣቢያዎች አለመገኘት በቀጣይ ምርጫዎች በምርጫ ቦርድ ሊታረም የሚገባው ክፍተት እንደሆነ ህብረቱ ያምናል፣

- በስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ወቅት የምርጫ ቦርዱ የበለጠ የሴት ምርጫ አስፈጻሚዎችን በማሰማራት የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ያደረገውን ጥረት እውቅና የሚሰጠው ህብረቱ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይህን መልካም ጅማሮ በማጎልበት በቀጣይ ምርጫዎች በምዝገባ እና ምርጫ ጣቢያዎች የሚሾሙ ሴት የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎችን ቁጥር ለማሳደግ ሊሰራ እንሚገባ ሳያሳስብ አያልፍም። በተጨማሪም ምንም እንኳን ከቀደምት ምርጫዎች አንፃር በርከት ያሉ ሴት የምርጫ አስፈፃሚዎች በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ ላይ ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም (በሰኔ ወር በአማካኝ 39% እና በመስከረም ወር 36%) ቦርዱ በቀጣይ ምርጫዎች የሴት ምርጫ አስፈፃሚዎችን ቁጥር ከዚህ በላይ በመጨመር የሴቶችን ተሳትፎ ሊያጎለብት ይገባዋል፣

- የምርጫ አስፈጻሚወች አቅምና ሙያዊ ብቃት በምርጫው ሂደት ጥራት ላይ ወሳኝ ተፅዕኖ አለው። ህብረቱ

በምርጫው የተለያዩ ሂደቶች (የመራጮች ምዝገባና እና የድምፅ መስጫ ቀን) ባደረገው ትዝብት ላይ በምርጫ አስፈፃሚዎች ዘንድ በታዘበው የአቅም ማነስ ችግር ላይ በመመስረት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አስፈፃሚዎችን የሚመለምልበትን ሊከልስ እንዲሁም የምርጫ አስፈፃሚ ስልጠናዎችን ጥራት የሚያሳድግበትን መንገድ ከቀጣይ ምርጫዎች አስቀድሞ ሊያጤን እንድሚገባው ህብረቱ ያምናል። ለዚህ ክፍተትም እንደማሳያ ሊጠቀስ የሚችለው ህብረቱ በቆሎጂ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ካምፕ የታዘበው የአስፈፃሚዎች አቅም ማነስ ችግር ነው።

## የሥነ ሥርዓት ምክረ ሐሳቦች

ምንም እንኳን የህብረቱ የትዝብት ግኝቶች ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ የተከናወነው በምርጫ ህጉ በተቀመጡት የሥነ ሥርዓት ህጎች መሠረት መሰረት እንደተከናወነ የሚጠቁሙ ቢሆንም ድጋሚ ድምፅ መስጠትን ለማስቀረት የሚጠቅመውን የማይለቅ የጣት ቀለም በመራጮች ላይ የማድረግ ስርዓት ወጥነት ባለው መንገድ መተግበር በቀጣይ ምርጫዎች ቦርዱ ሊሰራበት የሚገባ አንዱ ክፍተት ነው፤፤
በተጨማሪም የምርጫ ቦርዱ በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው የሰፈረ (የተመዘገቡ) ዜጎች ለመምረጥ በሚመጡበት ወቅት ድምፅ የመስጠት መብታቸው መከበሩን ማረጋገጥ ይገባዋል ብሎ ህብረቱ የሚያምን ሲሆን በተጨማሪም በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው ያልሰፈረ (ያልተመዘገቡ) ዜጎች ድምፅ የሚሰጡባቸውን አሰራሮች በቀጣይ ምርጫዎች ማስቀረት ይጠበቅበታል፣

ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በ2013 ዓ.ም ላከናወነው ምርጫ የተጠቀመው የመራጮች መዝገብ በቀጣይ ለሚደረጉ ምርጫዎች እንደመነሻ የሚያገለግል ከሆነ ቦርዱ ቀጣይ ምርጫዎች እስከሚደርሱ ድረስ መዝገቡ ጊዜ ያለፈበት እንዳይሆን በመደበኛ መንገድ ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚያስችለውን የአሠራር ዘዴ መዘርጋት አለበት ብሎ ህብረቱ ያምናል። በቀጣይ ምርጫዎች አዲስ የመራጮች ምዝገባ የሚከናወን ከሆነ ደግሞ ብሔራዊ የምርጫ ቦርዱ የመራጮች ምዝገባ ዝግጅትና ስራዎችን አስቀድሞ በማስጀመር የዜጎች ድምፅ የመስጠት መብት እንዲከበር መስራት ይጠበቅበታል። በሁለቱም ሁኔታዎች ቦርዱ በቀጣይ ምርጫዎች ለ2013 ዓ.ም ምርጫ ድምፅ የሰጡ ዜጎችን ጨምሮ አዳዲስ መራጮች በወቅቱ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን እንዲያገኙ የምዝገባ ስራውን አስቀድሞ ሊጀምር እንደሚገባው ህብረቱ ያምናል።

## የምርጫ ቅሬታ አሰማም እና አስተዳደር

የምርጫ ቦርድ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎችና በምርጫ ጣቢያዎች መቋቋማቸውና አገልግሎት መስጠታቸው በምዝገባ ወቅትና በምርጫ የሚከሰቱ የሥነ ሥርዓት ግደፈቶችን ቀደም ብሎ ለመመዝገብና ወሳኔዎችን በወቅቱ ለመስጠት ወሳኝ ነው። ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይህን ለማረጋገጥ በምርጫ ህጉ ላይ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሰረት በቀጣይ ምርጫዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በመራጮች ምዝገባ ማዕከላትና በምርጫ ጣቢያዎች መመስረታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፣

ስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ በግልፅ ካሳያቸው ክፍተቶች መካከል በአሁኑ ወቅት የምርጫ ቅሬታዎችን ምርጫ ቦርዱ የሚያስተናግድበት የህፍ ማዕቀፍ ለቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የማያስችል መሆኑ አንዱ ነው። በቀጣይ በሚደረጉ ምርጫዎች ቦርዱ የቅሬታ አሰማም አሰራሩን መገምገም የሚጠበቅበት ሲሆን በተለይም ከ42,000 በላይ የምዝገባና የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ባሉበት አገር በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ማዋቀር ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ሊያጤን እንደሚገባው ህብረቱ ያምናል፣

በተጨማሪም ቦርዱ የቅሬታዎች አሰማምና ወሳኔ አሰጣጥ ሂደት አሠራሮችን በተለይም የቋንቋ እና/ወይም የቴክኖሎጂ መሰናክሎች ሊኖሩባቸው የሚችሉ አሠራሮችን መልሶ በመከለስ ተገቢውን ማሻሻያ ማድረግ ይጠበቅበታል።

## የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቀጣይ የምርጫ ሂደቶችን የተሻላ አሳታፊ፣ ግልጽና ተጠያቂነት የሚታይባቸው እንዲሆኑ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላል። በቀጣይ በሚደረጉ ምርጫዎች ቦርዱ ከባለድርሻ አካላት (የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ የህዝብ እንደራሴዎች ወይም የፓርላማ አባላት፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት ወዘተ..) ጋር መደበኛና ግልፅ ግንኙነቶችን በማድረግና በጋራ በመስራት ያለውን ተዓማኒነት ማሳደግ፣ ተቋማዊ ግልፅነቱን ማሳደግ፣ በምርጫ ህጉና በአሰራር ዚሪያ ሊደረጉ የሚችሉ ማሻሻያዎችን መለየት እና እንደወገንተኛ ተቋም የሚታይበትን ሁኔታ ማስቀረት ይጠበቅበታል።

# ለተወካዮች ምክር ቤትና የመንግሥት ሚኒስቴሮች

- የ2013ቱ ምርጫ ለተጨማሪ የምርጫ ሪፎርም ዕድሎችን ፈጥሯል። ህብረት-ለምርጫ የሚመለከታቸው የሕዝብ ተወካዮች ምክር-ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች እና ሚኒስቴሮች ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የምርጫ ኃላፊዎች፣ አቀንቃኞች/ የሲቪክ የመብት ተሟጋቾች፣ ታዛቢዎች የትምህርት ባለሙያዎች፣ሙያተኞችና ኤክስፐርቶች እና ዜጎች ጋር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ አካታችና ግልጽ ውይይት እንዲያካሂዱ ይመክራል፡-

- የዳበረ የዴሞክራሲ ስርአት ባላቸው አገራት ውስጥ የሚዲያ የሕግ ማዕቀፍ የሚዲያው ዘርፍ በምርጫ ሂደቶች ላይ ገንቢ ሚና መጫወት የሚችልበት አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ነው። ምንም እንኳን ከቀደሙት ምርጫዎች ጋር ሲነጻጸር በአገሪቱ የመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) ምህዳር ላይ መሻሻል የታየ ቢሆንም፤ ጋዜጠኞች ለምርጫ ሂደቱ ሽፋን በመስጠት ረገድ የተለያዩ ተግዳሮቶች እንዳጋጠሟቸው ሪፖርት አድርገዋል። ለምርጫው ሽፋን የሰጡ ጋዜጠኞች በተለያዩ አካላት ተዋናዮች ጫናየደረሰባቸው መሆኑን በመግለጽ የደኅንነት ስጋቶች እነደነበረቡባቸው አንሥተዋል። ስለሆነም የሚዲያውን ዘርፍ የሚቆጣጠረው የሕግ ማእቀፍ የጋዜጠኞችን ደኅንነትና ጥበቃ በማረጋገጥ የሚዲያውን ዘርፍ የዲሞክራሲያዊ ምርጫ አንደኛው ቋሚ ምሶሶ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ መሻሻል አለበት። ከዚህ በተጨማሪም የሚዲያውን የሚቆጣጠረው አካል በማቋቋሚያ አዋጁ የተደነገጉትን ሕጎችና ደንቦች በአግባቡ ማስፈጸም ይኖርበታል።

## የፖለቲካ ፓርቲዎች

- የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገሪቱ ዴሞክራሲን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ውስጥ በሁሉም የምርጫ ሂደት ደረጃዎች ውስጥ በሙሉ በቁርጠኝነት መሳተፍ አለባቸው፤

- የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው ምርጫዎች ይካሄዱ ዘንድ አስተዋጽኦ ለማድረግ ተወካዮቻቸውን በመራጮች ምዝገባ ቦታዎችና የድምፅ መስጫ ቦታዎች ማሠማራት አለባቸው። በተጨማሪም ህብረቱ ለፓርቲዎች ግልጽነት የሰፈነባቸው ምርጫዎች እንዲካሄዱ ለማረጋገጥና የፖለቲካ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የተሰጧቸውን መብቶች መጠቀም እንዳለባቸው እና የሕዝበ ውሳኔ ድምፅ አሰጣጥ ሂደቶችን አእንዲታዘቡ ጥሪውን ያቀርባል፤

- የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀጣይ ምርጫ ሂደቶች ላይ ገንቢ ሚና ለመጫወት እራሳቸውን ከምርጫ ሕግጋትና ደንቦች ጋር ማስተዋወቅ አለባቸው። በተለይም ቅሬታዎችን በተመለከተ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅሬታዎችን እና ይግባኞችን ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳን በአግባቡ ማወቅ አለባቸው፤
የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ የማይካሄድበትን ጊዜ (የጥሞና ጊዜ) ማክበር ወይም የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁሶችን በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አቅራቢያ ከመለጠፍ መቆጠብ አለባቸው፤

- በስድስተኛው አገር-አቀፍና የክልል ምርጫዎች ወቅት ሴቶች በእጩነት ያደረጉት ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር። የፖለቲካ ፓርቲዎች የሁሉንም ኢትዮጵያውያን ዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ የሴቶች፣ የወጣቶች ፣ የአካል ጉዳተኞችና፣ እንዲሁም የሌሎች አድሎ የሚደርስባቸው ማህበረሰቦችን ተሳትፎ በየተቋሞቻቸው ለማሳደግ መሥራት አለባቸው።

# የሲቪል ማኅበረሰብ ተዋንያን

- ምንም እንኳን ካለፉት ምርጫዎች ጋር ሲነጻጸር የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በስድስተኛው የኢትዮጵያ አጠቃላይ አገር አቀፍ ምርጫዎች እንደ መራጮች ትምህርትና የምርጫ ትዝብትን በመሳሰሉ የምርጫ ተግባራት ላይ ከፍ ያለ ሚና የተጫወቱ ቢሆንም በምርጫዎች ላይ የሲቪል ማኅበረሰቡ የሚጫወተውን ሚና ከዚህም በላይ ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

- ካለፉት ምርጫዎች ጋር ሲነጻጸር የአገር ውስጥ ታዛቢ ቡድኖች በቅርቡ በተካሄዱት ምርጫዎች ላይ በአገር-አቀፍ ደረጃ በተቀናጀ መልኩ የተሻለ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ። ሆኖም የሲቪል ማህበራቱ እንደ አማራጭ የምርጫ

የመረጃ ምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ እነዚህ ጅማሬዎች ስልታዊ እና በባለሙያዎች በታገዘ የምርጫ አሠራር ሊደገፉ ይገባቸዋል

ከ2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ ምርጫዎች ቀደም ብሎ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለ136 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በመራጮች ትምህርት እንዲሳተፉ ዕውቅና ሰጥቷቸዋል።[32] ሆኖም ዕውቅና ካገኙት መካከል የመራጮች ትምህርትን ያከናወኑት[33] 49 ያክሉ ብቻ ነበሩ። ለቀጣይ ምርጫዎች የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዕውቅና ካገኙ በኋላ በእነዚህ ተግባሮች ላይ መሠማራታቸውን ክትትል በማድረግና በማረጋገጥ የመራጮች ትምህርትን ስኬታማነትን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለጋሾችም (አጋር ድርጅቶችም) የሲቪል ማኅበረሰቡ በከፍተኛ ደረጃ በመራጮችና በስነ ዜጋ በትምህርት ላይ ተሳትፎ እንዲያደርግ የገንዘብ እና ቴኒክ ድጋፍ ቢያድርጉ መልካም ይሆናል፡፡

በቅርቡ በተካሄዱት ምርጫዎች ወቅት የተሰጠው የመራጮች ትምህርት በገጠራማው የአገሪቷ ክፍል የሚኖሩ ዜጎችን በመድረስ ረገድ ውስንነቶች ታይተውበታል፡፡ ከከዚህ በተጨማሪም አገር[illegible]በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በገጠር አካባቢዎች የመራጮች ትምህርት ፕሮጀክቶችን በመተግበር ረገድ የዐቅም ውስንነት እንዳለባቸው ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዳዲስ አቀራረቦችን በመተግበርና ከአካባቢ ማኅበረሰቦች ጋር አጋርነት በመፍጠር በአገሪቱ ገጠራማ ክፍል የሚገኙ ዜጎችን መድረስ ይኖርባቸዋል፡፡

## መገናኛ ብዙኀን

በምርጫ ሪፖርት አቀራረብና ዘገባ ላይ ጋዜጠኞችና መገናኛ ብዙኃን የሪፖርት አቀራረባቸውን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባገኙ መርሆዎች ላይ መመስረት ይኖርብታል። ይህን እንዲሆን ለማስቻልም ሁሉም የሚዲያ ተቋማት በሙያዊ የምርጫ ዘገባ አቀራረብ መመሪያዎች ላይ ተመሥርተው የኤዲቶሪያል ፖሊሲዎችና የሥነ ምግባር ደንብ ማዘጋጀት አለባቸው።

የአገሪቱ የሚዲያው ዘርፍ ገና በማደግ ላይ እንደመሆኑ መጠን የምርጫ ዘገባዎች በሚዘጋጁበት ወቅትየተለያዩ ቅርጸቶች (ፎርማቶች) አለመኖርና አሳታፊ አለመሆን የመሳሰሉ የዐቅም ውሱንነቶች ታይተውበታል። የህብረቱ የሚዲያ ክትትል ክፍል የሚዲያ ዳሰሳ ሪፖርት እንደሚያሳየው አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ከምርጫ ጋር ተያያዥን ያላቸውን ጉዳዮች በንግግርና ክርክር ፎርማቶች ቢዘጋጁ እንደሚመርጡ ያሳያል። ስለሆነም የሚዲያ ድርጅቶች የሚያገለግሉትን ማኅበረሰብ ፍላጎቶችና ምርጫዎች ለመረዳት የሚያስችል ዐቅም መፍጠር አለባቸው። ይህን ግብ ለማሳካት በሚደረገው የምርጫ ውድድር ፣ በምርጫ ዘገባ አቀራረብና የመራጭ ትምህርት ላይ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ተጽእኖ ላላቸው ለሁሉም የሚዲያ ተቋማትና የሚዲያ / መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኞች ተከታታይ የአዐቅም ግንባታ የሥልጠና መጠት አለባቸው። ለዚህም ዓላማ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ የኢትዮጵያ የብዙሀን መገናኛ ብሮድካስት ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት እና በዘርፉ ተሳታፊ የሆኑ ሌሎች ተዋናዮች እነዚህን ሙያዊ የዐቅም ግንባታ ጥረቶች ስኬታማ ለማድረግ የመሪነት ሚና መጫወት አለባቸው።

ሁሉም የምርጫ ባለድርሻ አካላት የሚዲያው ዘርፍ በምርጫ ሂደት ላይ ያለውን ገንቢ ሚና በመረዳትና በጋራ መሥራት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪም ሁሉም ተዋናዮች የፖለቲካ ከወገንተኝነት ነፃ በሆነ መልኩ ለሁሉም ዕውቅና ለተሰጣቸው የሚዲያ ተወካዮች/ጋዜጠኖች እኩል የተደራሽነት ዕድል መስጠት አለባቸው።

32 IRI-NDI joint Limited Election Observation Mission to Ethiopia (LEOME), Ethiopia June 21, 2021 National Elections Report, (5 August 2021)

33 ዝኒ ከማሁ



“የሕብረት ለምርጫ ግዚያዊ የምርጫ ማዕከልን በተለያዩ አገራት ዲፕሎማቶች እና የአለም አቀፍ ድርጅቶች ተጠሪ ሲጎበኙ

# ሕብረት ለምርጫን የተመለከተ መረጃ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ሲማድህኅም)ግንቦት 9/ 2011 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ የምዝገባ ቁጥር ....... የተመዘገበ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው። ኅብረት ለምርጫ በመተዳደሪያ ደንቡ ከዘረዘራቸው ዓላማዎቹ መካከል በምርጫ ሂደት የመራጮችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የሲቪክ እና የምርጫ ትምህርት ማካሄድ፣ አባላቱ በሁሉም የምርጫ ሂደቶች እና በህዝበ ውሳኔዎች የክትትል እና የትዝብት ሥራዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ የማንቀሳቀስ እና የመደገፍ፣ ከምርጫ ጋርየተያያዙ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የመሰነድ ፣ የማጋራት እና የማሰራጨት ጥቂቶቹ ናቸው። ኅብረት ለምርጫ የመራጮች እና የሲቪክ ትምህርት፥ ፣ የምርጫ ትዝብት እና ክትትል፤ የጥናታና አድቮኬሲ እንዲሁም የአቅም ግንባታ ፕሮገራሞችን ያካተተ ከ 2020-2022 የሚቀይ የሶሰት አመት ሰተራተጂክ ፐላነ አዘጋጅቶ በማስፈጽም ላይ ሲሆን ከተመሰረተበት ጊዜእ አንስቶ በመላ አገሪቱ ሉ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ አባል ድርጅቶችን እንዲሁም የራሱን አቀም ለማጎልበት ልዩ ልዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገናኛል።

# የሕብረት ለምርጫ ተሞክሮዎች እና ልዩ ልዩ ተግባራት

የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ህኅብረት ለምርጫ (ሲማድህኅም) ከተቋቋመበት 2011 ዓ.ም አንስቶ በርካታ ተግባሮችን እያከናወነ ይገኛል። ሁለተኛ የምሥረታ በዓሉን ከጥቂት ወራት በፊት ያከበረው ሕብረት ለምርጫ በ2012-2014 አጠቃላይ ምርጫዎች ለመሳተፍ ያሰቻለውን የስትራቴጂካዊ ዕቅድ ዝግጅቱን መጠናቀቅ ተከትሎ ከመራጮች ና የሲቪክ ትምህርት፣ የምርጫ ትዝብት ና ቁጥጥር፣ የውትወታ (አድቮኬሲ)፣ የባለድርሻ አካ፤ኣተ ተሳትፎ፣ ምርምር እና የአባላት ዐቅም ግንባታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እጅግ ጨታማ የሆኑ ተግባራትን በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ አሳክቷል። በዚህ ሪፖርት በዝርር ከተገለጡት የምርጫ ትዝበት ሥራዎች በተጨማሪ ኅብረቱ የፈጸማወው ዋና ዋና ተግባራት በጭሩ ከዚህ በታች ቀርበዋል።

## የሲዳማ የክልልነት ሕዝበ- ውሳኔ

ህበረቱ ሕብረት ለምርጫ ከሲቪል ማህኅበረሰብ ድርጅቶች መካከል በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋባዥነት ህዳር 10/2012 20/ 2019 ዓ.ም የተካሄደውን የሲዳማ ዞን ራሱን የቻለ ክልል ሆኖ ለመወጣት የሚሰችለውን ሕዝበ ውሳኔ የታዝበ የመጀመሪያው የሲቪል መሃበረሰብ ድርጅት ህኅብረት ሲሆን ነው። ሕብረት ለምርጫ ከሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ ባገኘው ልምምድና ተሞከሮ ላይ በመመስረት የቅድመ ምርጫ/ የቅድመ ሕዝበ ውሳኔውን ፤ የሕዝበ ውሳኔው ድምጽ መስጫ ቀንን እንዲሁም ድህረ የሕዝበ ውሳኔ ከባቢን ጨምሮ አጠቃላይ የሕዝበ ውሳኔውን ሂደት በመታዘብ ፋናወጊፈር ሆኗል። ሕብረት ለምርጫ የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ ተሞክሮን ሰኔ 21/ 2013 እና መስከረም 20/ 2014 ዓ.ም የተካሂዱትን ጠቅላላ ምርጫዎች ላይ ላካህደው የቀድመ ምርጫ፤ የደምጸ ምሰጫ ቀነ እንዲሁም የደህረ ምርጫ ትዝብትን ለማሄድ በግበአትንት ረተ ጠቃሚ ህድ ለመታአብ ቅም ላይ ያዋላቸውን ጠቃሚ የተጠቀመበት ተሞክሮዎች የሚያዳብርበት ለመጠቀምወ መልካም አጋጠሚን ፈጥሮለታል ልዩ ዕድል አስገኝቶለታል። ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም (NDI) ካደረገው የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ ህብረቱለሕብረት ለምርጫ የሥልጠና ቁሳቁሶችና የትዝብት ቅጾችንየመታዘቢያ ማረገገጫ ዝርዝሮችን ለሲያዘጋጅ ማዘጋጀት የቴክኒክና ሚያዊ ድጋፍ አድርጎለታል እንዲሁም ለአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች ሥልጠና ሰጥቷል።

## የህብረቱ አባል ድርጅቶችን አዐቅም መገንባት

ሕብረት ለምርጫ ከአውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል (ECES) ጋር በመተባበር ለአባላቱ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ የዐቅም ግንባታ በአጠቃላይ በተለይም ለምርጫ ባለድርሻ አካላት በአመራርነት እና የግጭት አያያዝ ክኅሎቶች፤ ከምርጫ ዑደት ንድፈ ሐሳብ ና በምርጫ ዑደትየሚከሰቱ የምርጫ ግጭቶችና አለመግባባትን የመከላከል እና/ወይም የማቅለል የአመራር ክኅሎቶቻቸውን እንዲያደብሩ ያስቻላቸውን የሦስት ቀናት የሥልጠና አዘጋጅቷል። በተመሳሳይ ሕብረት ለምርጫ ከየአውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል (ECES) ጋር በጋራ በመተባባር

በምርጫ ፖሊሲ እና አስተዳደር /Master on Electoral Policy and Administration (MEPA)/ ከ100 በላይ ለሆኑ የህበረቱ አባላት በበይነ መረብ የተለያዩ ምርጫ ነክ ኮርሶችን እንዲወስዱ በማደረግ የአባላቱን አቅም በመገነባተት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽ አደርጓል።

## በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የቀረቡ ዌቢናሮች (የበይነመረብ ቪዲዮ ውይይቶች)

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከሰትን እና ይህንነም ተከትሎ ነሐሴ 2012 ዓ.ም ሊካሄድ የነበረው የኢትዮጵያ ጠቅላላ ምርጫ ላልተወሰነ ጊዜ መተላለፉን ተከትሎ ተከትሎ ሕብረት ለምርጫ ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ ከምርጫ ጋር ተያያዥ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ በሚሉ ተያያዠ ጭብጦች ዙሪያ ተከታታይ ዌቢናሮችን (የበይነመረብ ቪዲዮ ውይይቶችን) አካሂዷል።

## የመገናኛ ብዙኀን ዳሰሳ ክትትል

ሕብረት ለምርጫ የምርጫ ትዝብት አንቅስሴ ያተኮረበት ላላው ዘርፍ የሚዲያው ምህዳር ሲሆን ከአውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል (ECES) ጋር በመተባበር መሠረቱን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በአምስት የአገር ውስጥ ቋንቋዎች እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ ክትተል የሚያደርጉ ዘጠኝ የሚዲያ ሙያተኞችን ያቀፈ የሚዲያ ክትተል ክፍል (MMU) አቋቁሞ ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል። የሚዲያ ክትትል ክፍል በሰኔ እና የመስከረም የምርጫ ዙሮች የነበረውን የቅድመ ምርጫ፣ የምርጫ ቀን እና የድኅረ ምርጫ የሚዲያ ምህዳር ክትተል እንዲሁም የተደራሽንነት ወሰንን፣ አድማጭ/ተመልካች ብዛት ግምት ወይም ሥርጭት የመሳሰሉ መስፈርቶች ላይ ተመረኩዞ ናሙና የሚዲያ ዳስሳ አካሂዷል። የሚዲያ ክትተል ክፍሉ ሚዲያው ለፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሰጠውን ፍትሐዊና ሚዛናዊ ሽፋን ፍትሐዊነና ሚዛናዊነት ደረጃንም ገምግሟል። ኸዚህ በተጨማሪ በምርጫው ሂደት እና በድኅረ ምርጫ ወቅቶች የሚዲያ ክትተል ክፈሉ በጥላቻ ንግግር ወይም ግጭት ቀስቃሽ የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ክትትል ከማድረጉም በተጨማሪ ሚዲያው ከምርጫ ጋር በተያያዙ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የትኛውንም አይነት ውጥረቶች አእነዲባባሱ አስተዋጽኦ ስለማድረግ አለማድረጉ ገምግሟል።

## የመራጮች ትምህርት

CECOE ከIRI በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እመርጣለሁ (I Vote) የተሰኘ ዲጂታል የግንዛቤ ማሳደጊያ ዘመቻን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እና የማህበራዊ ሚዲያዎችxን በመጠቀም ያካሄደ ሲሆን ይህም ዜጎች ስለምርጫው እና ሂደቶቹ በቂ ግንዛቤ እንዲያኙ አስችሏል፡፡ የዚህ ዘመቻ ዋና አላማም እንዴት ሰላማዊ በሆነ መልኩ ምርጫን ማካሄድ እንደሚቻል የዜጎችን ግንዛቤን ማሳደግ ነበር፡፡ከዚህም በተጫማሪ መራጮች እንዴት ድምፅ መስጠት እንዳለባቸውና ሌሎች ለማወቅ በሚፈልጓቸው ጉዳዮች ዙሪያ በivote አማካኝነት መረጃ ሲቀርብ ነበር። በ በivote (እመርጣለሁ) ዘመቻ አማካኝነት CECOE በምርጫው ወቅት በ32 የተለያዩ የቴሌቭዥን እና የራዲዮ ጣቢያዎች ላይ በአራት ቋንቋዎች (ሶማሊኛ፣ አማርኛ ፣ አፋርኛ እና ኦሮምኛ) 1032 የብሮድካስት የግንዛቤ ማሳደጊያ መልእቶችን አስተላልፏል ፡፡ከዚህም በተጫማሪ በተለያዩ የማኅበራዊ ትስስር ገጾችን በመጠቀም ተመሳሳይ የግንዛቤ ማሳደጊያ መልእቶችን በማሠራጨት ከ40 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያንን በመድረስ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስራ ሰርቷል።

# የምርጫ ትዝብት ሪፖርት

## የኢትዮጵያ ስድስተኛው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫዎች

**ሕብረት ለምርጫ**

**የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ**


**የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ**

**ስድስት ኪሎ፣ ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢኒስቲቲዉት ሕንጻ 2ኛ ወለል**
***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ***

+251 11 811 1455
www.cecoe.org
info@cecoe.org
twitter: @cecoeEth
facebook: CECOE21